# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

# 142ኛ ልዩ መግለጫ



**አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀ (ከመስከረም 28 2009 ዓ.ም) ጀምሮ በዜጎች ላይ የሚፈፀም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በአስቸኳይ ይቁም!**

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ * Human Rights Council

ግንቦት 21 ቀን 2009 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የምዝገባ ቁጥር 1146

# ሰመጉ

## ዋናው ጽ/ቤት፡ አዲስ አበባ

አ.አ ስታዲየም አጠገብ፣ ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ሣኅለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁጥር 19

ስልክ: (+251) 011 551-7704

ፋክስ: (+251) 011 551-7704

ኢሜይል: info1hrco@gmail.com/info@ehrco.org

ድረ ገጽ: www.ehrco.org

የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ

ስልክ: (+251) 011 558-2387

ኢሜይል: info1hrco@gmail.com /monitoringcomplaints@ehrco.org

## ቀጠና / ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

| | |
|---|---|
| ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ሐዋሳ - ስ.ቁ (+251) 046 220-4500፣ ፖ.ሳ.ቁ 360 |
| ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ባሕርዳር- ስ.ቁ (+251) 058 226-3913፣ ፖ.ሳ.ቁ 1115 |
| ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ነቀምቴ - ስ.ቁ (+251) 057 661-5014፣ ፖ.ሳ.ቁ 463 |
| ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ድሬደዋ - ስ.ቁ (+251) 025 811 9150፣ ፖ.ሳ.ቁ 2596 |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ጅማ - ስ.ቁ (+251) 147 211 5434 |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | አዲስ አበባ ስ.ቁ (+251)011 551-7704፣ ፖ.ሳ.ቁ 2432 |


የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

# ማውጫ

1. የኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ ---------- 1
2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ---------- 2
3. መግቢያ ---------- 3
   በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁና በአፈጻጸም መመሪያዎቹ ላይ የተደረገ አጭር ቅኝት ------ 3
4. የምርመራው ግብና ሥልቶች ---------- 8
   4.1 የልዩ መግለጫው ዋና ዓላማ ---------- 8
   4.2 ምርመራውና ልዩ መግለጫው የተመሠረተበት የህግ ማዕቀፍ ---------- 8
   4.3 በምርመራው የተሸፈኑ አካባቢዎችና ምርመራው የተካሄደበት ጊዜ ---------- 8
   4.4 የመረጃ ምንጮችና የማስረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ---------- 9
   4.5 የምርመራ ስራው ውሱንነትና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ---------- 10
5. አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀ በኋላ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ---------- 10
   5.1 በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ ወጥ ግድያ) ---------- 11
   5.2 እስራት ---------- 16
   - ሠንጠረዥ 1 ---------- 16
   - ሠንጠረዥ 2 ---------- 17
   - ሠንጠረዥ 3 ---------- 21
   - ሠንጠረዥ 4 ---------- 21
   - ሠንጠረዥ 5 ---------- 23
   - ሠንጠረዥ 6 ---------- 23
   - ሠንጠረዥ 7 ---------- 23
   - ሠንጠረዥ 8 ---------- 24
   - ሠንጠረዥ 9 ---------- 24
   - ሠንጠረዥ 10 ---------- 25
   - ሠንጠረዥ 11 የሠንጠረዦች ማጠቃለያ ---------- 26
   - የሰመጉ መርማሪዎች የተመለከቷቸው ማረሚያ ቤቶች ሁኔታ ---------- 26
   - የእስረኞች አያያዝ ---------- 27
   - የታሳሪዎች የምስክርነት ቃል ---------- 28
   5.3 ማቁሰል፣ ድብደባና ማሰቃየት ---------- 38
   5.4 ሌሎች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ---------- 41
   - ሠንጠረዥ 12 - 14 ---------- 42
6. ማጠቃለያ ---------- 42
7. ማሳሰቢያ ---------- 43
   አድራሻዎች ---------- 43

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

# 1. የኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ[1]




የመብት ጥሰቱ የተፈጸመባቸው አካባቢዎች

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

[1] "ኢትዮጵያ" [ካርታ]. <http://www.h2empower.org/aboutus/factsethiopia.html>. (August 11, 2015)

## 2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ)፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) በኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር አንቀጽ 1(ሀ) እና በኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር ከ404-482 በተጸፉት ድንጋጌዎች መሠረት መስከረም 29 ቀን 1984 ዓ.ም. በአባላት የተመሠረተ የመጀመሪያው መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም ነው፡፡ ሰመጉ በበጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 መሠረት "ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ማኅበር" ሆኖ በምዝገባ ቁጥር 1146 በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ድርጅት ነው፡፡ ሰመጉ ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የኃይማኖት ተቋም፣ የብሔረሰብ ቡድን፣ ማህበራዊ መደብ ወዘተ የማይወግን፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ነው፡፡ ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው፡፡ ሰመጉ ላለፉት 25 ዓመታት በቆመላቸው ዐበይት ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ፣ ሁለንተናዊ፣ ሐገራዊና ሕዝባዊ ተልዕኮ በመያዝ በነደፋቸው በርካታ የመርሐ-ግብር ተግባራት አማካኝነት ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የሕግ የበላይነት እና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲሰፍንና በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲኖር የበኩሉን አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

ዓበይት ዓላማዎቹንና ተልዕኮውን ለማሳካት ሰመጉ ፈርጀ ብዙ የሆኑ የመርሐ ግብር ተግባራትን ያከናውናል፡፡ ከነዚህም መካከል አንዱ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላትና ለሕዝብ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና መስጠት ነው፡፡ የመንግሥት አካላት በዋነኛነት የግዴታዎች ተሸካሚ፣ ሕዝብም በዋነኛነት የመብቶች ባለቤት እንደመሆናቸው መጠን፣ የመንግሥት አካላትም መብት የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታቸውን በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዘው እንዲወጡ፣ ሕዝብም እንዲሁ በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዞ መብቱን እንዲያስከብር ሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም ሰመጉ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ይሠራል፤ ውጤቶቹን በስብሰባዎችና በልዩ ልዩ የመገናኛ መንገዶች ያሠራጫል፤ የአድቮኬሲ ሥራዎችንም ያከናውናል፡፡

የሰመጉ መለያውና ግንባር ቀደም ተግባሩ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝና ሁኔታ መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ማጣራትና በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው፡፡ ሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ መሄድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና ተገቢው የፖሊሲና የአፈጻጸም እርማት እንዲደረግ ሲጮህና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁ ይቀጥላል፡፡ ከሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ክትትል ተግባራት መካከል፣ የሕግ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቃቸውን መከታተል፣ የፍርድ ቤቶችን ሂደት ፍትሐዊነት መከታተል እንዲሁም በመንግሥት የወጡና የሚወጡ ሕጎችን ይዘትና አፈጻጸማቸውን ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር መመርመር ይገኙበታል፡፡ ከነዚህ በተጓዳኝ ሰመጉ በተለይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ዜጎች የተለያየ ደረጃና መልክ ያለው የሕግ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

በእስካሁኑ ቆይታው ሰመጉ 36 መደበኛ መግለጫዎችና 141 ልዩ መግለጫዎችን በተጨማሪም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል፡፡ ሰመጉ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ቢሆን፣ ሁኔታና ዐቅም በፈቀደለት መጠን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

## 3. መግቢያ

የአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላንን በመቃወም ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት በሚገኙ የኦሮሚያ አካባቢዎች የተጀመረውና በኋላም ጥያቄውን ወደ ዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደርና የሕግ የበላይነት ጥያቄዎች አስፍቶ በመላው ኦሮሚያ የቀጠለውን የህዝብ ተቃውሞ ተከትሎ የደረሱ ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ሰመጉ በ140ኛ ልዩ መግለጫው መጋቢት 2008 ዓ.ም. ይፋ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ ሰመጉ በተጨማሪም፣ ከወልቃይት ሕዝብ የማንነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን አጣርቶ ውጤቱን በ141ኛ ልዩ መግለጫው ግንቦት ወር 2008 ዓ.ም ይፋ ማድረጉም የሚታወስ ነው፡፡ የወልቃይትን ሕዝብ የማንነት ጥያቄ በመደገፍ፣ በጎንደር ከተማና የተወሰኑ አካባቢዎች የተጀመረው የሕዝብ ተቃውሞ፣ በሐምሌ ወር 2008 ዓ.ም. ወደ መልካም አስተዳደር፣ የዴሞክራሲና የሕግ የበላይነት ጥያቄዎች ተቀይሮ፣ ተቃውሞው በአብዛኛው የአማራ ክልል በተለይም በጎንደርና በጎጃም ልዩ ልዩ ዞኖች ተስፋፍቶ መቀጠሉም ይታወሳል፡፡ በሌላ በኩል በኦሮሚያ ክልል ለጥቂት ወራት ጋብ ብሎ የቆየው የሕዝብ ተቃውሞም በድጋሚ ያገረሸውና በመላ ክልሉ ተስፋፍቶ የቀጠለው በዚሁ በሐምሌ ወር 2008 ዓ.ም. ነው፡፡ ስለሆነም ሐምሌና ነሐሴ 2008 ዓ.ም. በአብዛኞቹ የአማራና የኦሮሚያ አካባቢዎች የሕዝብ ተቃውሞ ተስፋፍቶ የታየበትና ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት ወቅት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመስከረም ወር 2009 በቢሾፍቱ በተከበረው የኢሬቻ በዓል ላይ የደረሰው የሰው ሕይወት መጥፋትና የአካል መጉደል በመላው ኦሮሚያ ከፍተኛ ቁጣም ፈጥሮ ነበር፡፡ መንግሥት እነዚህ ሁኔታዎች ስላሳሰቡት በመስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቷል፡፡

### የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁና በአፈጻጸም መመሪያዎቹ ላይ የተደረገ አጭር ቅኝት

በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች የተካሔደው ህዝባዊ ተቃውሞ መባባሱን ተከትሎ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 28 ቀን 2009 ያወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ የተከሰተውን የጸጥታ መደፍረስ በመደበኛ የህግ አስከባሪ ኃይሎች ለማስተካከል ባለመቻሉ አዋጁ መውጣቱን፣ አዋጁም በመላው ሀገሪቱ ለ6 ወራት ተፈጻሚ እንደሚሆን ከገለጸ በሁዋላ፣ ይህንኑ ለማከናወንና ህግና ጸጥታን ለማስከበር በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ እና መከላከያ ሚኒስትሩ ሴክሬታሪያት የሆኑበት፣ በዋናነት የመከላከያ እና የደህንነት ኃይሎችን ያካተተ ኮማንድ ፖስት አቋቁሟል፡፡ አዋጁ በጥቅምት 2009 በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከመጽደቁም በላይ፣ በቅርቡ ለተጨማሪ አራት ወራት (እስከ ሐምሌ 2009 መጨረሻ ድረስ) ተራዝሟል፡፡ ኮማንድ ፖስቱ አዋጁን ለማስፈም አስፈላጊ መመሪያዎችን እንዲያወጣ ስልጣን የተሰጠው ሲሆን፣ በዚህ መሠረትም ከኢሰብአዊ አያያዝ ከመጠበቅ መብት፣ በህግ ፊት እኩል ከመሆን መብት እና የራስን ዕድል በራስ ከመወሰን መብት በስተቀር በህገመንግስቱ የተዘረዘሩ ሰብዓዊ መብቶችን የመገደብ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ መሠረትም ኮማንድ ፖስቱ በተለይ የመዘዋወር ነጻነት፣ የአካል ነጻነት መብት፣ የግል ህይወት የመከበር እና የመጠበቅ መብት፣ የአመለካከት እና ሃሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት፣ የመሰብሰብ እና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት፣ በተያዙ በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት፣ የንብረት መብት እና የነጻነት መብት ላይ በግልጽ ገደብ የሚያስቀምጡ ድንጋጌዎችን ያካተተ የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ አፈጻጸም መመሪያ (መመሪያ ቁጥር 1) አውጥቷል፡፡

በመመሪያው ከተከለከሉ ተግባራት መካከል፣ ሁከትና ብጥብጥ ወይም በህዝቦች መካከል መቃቃርና መጠራጠር ሊፈጥር የሚችል ቅስቀሳ፣ ጽሑፍም ሆነ ግንኙነት ማድረግን፣ መመሪያው ጸረ ሰላም ከሚላቸው (ነገር ግን ማንነታቸው ካልተገለጹ ቡድኖች) ጋር ግንኙነት ማድረግ፣ የሽብርተኛ ድርጅቶች ናቸው የተባሉ የቴሌቪዥን ወይም የሬድዮ ፕሮግራሞች መከታተል፣ ማሳየት እና ሪፖርት ማድረግ፣ ያልተፈቀደ ሰልፍና የአደባባይ ስብሰባ ማካሔድ፣ የግልም ሆነ የመንግስት ተቋማት ለህዝብ አገልግሎት እንዳይሰጡ ማድረግ ወይም አገልግሎት አለመስጠት፣ በስፖርት ማዘውተሪያዎች እና በትምህርት ተቋማት አድማ ማድረግ፣ የተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ማወክ፣ በመሰረተ ልማቶች ላይ ጉዳት ማድረስ፣ እንዲሁም ህግ አስከባሪዎች የሚሰጡትን ማንኛውንም ትዕዛዝ አለማክበር፣ መቻቻልን፣ አንድነትን፣ የሃገርን ሉዓላዊነት፣ ደህንነትና ሕገመንግስታዊ ስርዓት ሊጎዳ የሚችል ተግባር መፈጸም፣ ከውጭ መንግስታትም ሆነ ከውጭ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሀገር ሉአላዊነት፣

ደህንነትና ህገ-መንግስታዊ ስርዓትን ሊጎዳ የሚችል ግንኙነትና የመልዕክት ልውውጥ ማድረግ፣ የሚሉት ይገኙባቸዋል።

በመመሪያው የተከለከሉ ተግባራት ተፈጽመው ሲገኙ ስለሚወሰዱ የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎች በሚዘረዝረው ክፍል የጸጥታ ኃይሎች አዋጁን ተላልፏል ብለው የሚገምቱትን ሰው የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳያስፈልግ በቁጥጥር ስር የማዋል፣ ወደ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ የአዋጁ ተፈጻሚነት እስከሚያበቃበት ጊዜ ድረስ ኮማንድ ፖስቱ በሚወስነው ቦታ እንዲቆይ የማድረግ፣ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማናቸውም ሰዓት ብርበራ የማድረግ፣ በሬድዮ፣ በቴሌቪዥን፣ ጽሁፍ፣ ምስል፣ ፎቶ ግራፍ፣ በቲያትርና ፊልም የሚተላለፉ መልዕክቶችን የመቆጣጠርና የመገደብ፣ ሰላምና ጸጥታን ሊያደፈርሱ ይችላሉ ወይም ለጉዳት ተጋላጭ ይሆናሉ ተብለው የሚጠረጠሩና የሚታሰቡ ሰዎችን ወደ ተወሰነ አካባቢ እንዳይገቡ፣ እንዳይገኙ ወይም በተወሰነ አካባቢ ብቻ እንዲቆዩ የማድረግ፣ የህግ አስከባሪዎች እራሳቸውን ለመከላከል የሚያስችላቸውን እርምጃ እንዲወስዱ ያልተገደበ ስልጣን ሰጥቷል። የህግ አስከባሪዎች የሚወስዱት እርምጃ የህይወት መጥፋትንም ሊያስከትል የሚችል መሆኑ ሲታሰብ፣ መመሪያው በሕይወት የመኖር መብት ላይም ጭምር ገደብ የማድረግ ውጤት እንዳለው ያመለክታል። ይህም በሕይወት የመኖር መብት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅትም ቢሆን ገደብ ሊደረግበት እንደማይገባ ከሚደነግገውና ኢትዮጵያ ፈርማ ከተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን አንቀጽ 4(2) ጋር የሚጣረስ ነው።

በሌላ በኩል በሦስተኛው ክፍል በኮማንድ ፖስቱ የሚደረጉ የተሃድሶ እርምጃዎችን በተመለከተ በሚደነግገው ክፍል ውስጥ ባለፈው አንድ አመት ውስጥ በተፈጸሙ "ሁከትና ብጥብጥ" በተባሉ እንቅስቃሴዎች ላይ በተለያየ መንገድ ተሳትፎ ያደረገ ሰው እንደ "ወንጀል" ተሳትፎው ታይቶ በኮማንድ ፖስቱ የተሃድሶ ትምህርት ተሰጥቶት ሊለቀቅ እንደሚችል ይደነግጋል። ይህም መመሪያው የወጣው በአዋጁ እና በራሱ በመመሪያው መግቢያ ላይ እንደተመለከተው ህግና ስርዓትን ለማስፈን ብቻ ሳይሆን፣ ወደኋላ ተመልሶ መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ዜጎች በህዝባዊ ተቃውሞው ወቅት ነበራቸው በሚባል ተሳትፎ ምክንያት የቅጣት እርምጃ ለመውሰድ ጭምር መሆኑን የሚያመለክት ነው።

የአስቸኳይ አዋጁ አፈጻጸም መመሪያ ሁለት ጊዜ የተሻሻለ ሲሆን በግልጽ የተሻሻሉትን ለይቶ ለማስቀመጥ የመመሪያዎቹን ይፋዊ (ኦፊሻል) ቅጅ ለማግኘት የተደረገው ጥረት አልተሳካም። ነገር ግን የኮማንድ ፖስቱ ሴክሬታሪያት በሚዲያ እንደገለጹት ከሆነ ከተነሱት ክልከላዎች ውስጥ በዋናነት ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ በቁጥጥር ስር ማዋል፣ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በማናቸውም ሰዓት ብርበራ ማድረግ እና በኢኮኖሚ አውታሮች፣ መሰረተ ልማትና የኢንቨስትመንት ተቋማት፣ የእርሻ ልማቶች፣ በፋብሪካዎች እና በመሰል ተቋማት አካባቢ ከቀኑ 12 ሰዓት በኋላ እስከ ንጋት 12 ሰዓት ከተፈቀደለት ሰራተኛ በስተቀር መንቀሳቀስ የሚሉት ገደቦች ይገኙባቸዋል።

በሌላ በኩል የአፈጻጸም መመሪያው ግልጽነት የሚጎድላቸው እና አሻሚ ትርጉም ሊሰጣቸው የሚችሉ አንቀጾች የያዘ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ከሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ - ሰመጉ ሥራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው እና ከብዙ በጥቂቱ ሊጠቀሱ የሚችሉ በመሆናቸው እንደሚከተለው በዝርዝር እንመለከታቸዋለን።

የመጀመሪያው ሁከትና ብጥብጥ የሚያስነሳ ቅስቀሳና ግንኙነት ማድረግ[2] የሚለው የመመሪያው ክፍል ሲሆን ይህም ሁከትና ብጥብጥን እንዲሁም በህዝቦች መካከል መጠራጠርና ጥላቻን ሊያስከትሉ የሚችሉ ማናቸውም ይፋዊም ሆነ ድብቅ ቅስቀሳዎች፣ ጽሁፎች፣ ህትመቶች፣ መልዕክቶችና ሌሎች ግንኙነቶች መከልከላቸውን ደንግጓል። ይህ አንቀጽ ክልከላውን የሚያደርገው ጽሁፎቹን/መልዕክቶቹን በታቀደላቸው አላማ ወይም ባስከተሉት ውጤት ሳይሆን ምናልባት ሊያስከትሉ ይችላሉ ተብሎ በሚታሰበው/በሚገመተው ውጤት ላይ ተመስርቶ ስለሆነ፣ ትርጉሙን አሻሚ እና ተገማች ሳልሆነ አተረጓጎም የተጋለጠ አድርጎታል። ይህም ማንም ሰው በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ጽሁፎችን ሲያትም እና ሲያሰራጭ ወይም መግለጫዎችን ሲሰጥ በራሱ ላይ ቅድመ ምርመራ

[2] የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር አንድ፣ አንቀጽ 1 ይመለከቷል

(self censorship) እንዲያደርግ ከማስገደዱም በላይ የጸጥታ አካላት ምን ብለው ይተረጉሙብኛል በሚል እንዲሰጋ እና በህግ የተፈቀዱለትን ስራዎች እንኳን በአግባቡ እንዳያከናውን መሰናክል የሚፈጥር ነው፡፡

በሌላ በኩል ስብሰባዎችና ስልጠናዎችን በተመለከተ የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ አፈጻጸም መመሪያው ያለኮማንድ ፖስቱ ፈቃድ ሰላማዊ ሰልፍና የአደባባይ ስብሰባ ማካሔድ ክልክል መሆኑን ይደነግጋል፡፡[3] ‹‹የአደባባይ ስብሰባ›› የሚለው ሐረግ በመመሪያውም ሆነ በአዋጁ ትርጉም ያልተሰጠው በመሆኑ አንቀጹን ለትርጉም የተጋለጠ እና አሻሚ ያደርገዋል፡፡ በሰመጉ ግንዛቤ ‹‹የአደባባይ ስብሰባ›› የሚለው ሀረግ በአደባባይ ወይም ለህዝብ ክፍት በሆነ እና ማንም ሰው ሊሳተፍበት በሚችል ክፍት ቦታ (ከቤት ውጭ) የሚደረግ እና በእንግሊዘኛው rally/outdoor meeting የሚባለውን ስብሰባ የሚመለከት ነው፡፡ በተግባር ግን ማናቸውም የቤት ውስጥ ስብሰባዎች ከኮማንድ ፖስቱ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው የሚል ትርጓሜ በመንግስት የጸጥታ አካላት የተሰጠበት ወቅት ነበር፡፡ በዚህ ምክንያትም ሰመጉ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ኤጀንሲ ፈቃድ ያዘጋጀው የገቢ ማሰባሰቢያ የምሳ ግብዣ ከኮማንድ ፖስቱ ፈቃድ አላገኛችሁም በሚል በጸጥታ ኃይሎች እንዲቋረጥ መደረጉን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

በተመሳሳይም የውጭ ግንኙነቶችን በተመለከተ[4]፣ የሀገርን ሉዓላዊነት፣ደህንነትና ህገመንግስታዊ ስርዓቱን ሊጎዳ የሚችል ማናቸውም ግንኙነት ከውጭ ሀገር መንግስታት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ማድረግ የተከለከለ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ይህን ድንጋጌም ከላይ እንደጠቀስናቸው ድንጋጌዎች ለትርጉም የተጋለጠ እና አሻሚ የሚያደርገው ‹‹ሊጎዳ የሚችል›› የሚለው ሰፊ እና ግልጽነት የጎደለው ሀረግ ነው፡፡ ‹‹ሊጎዳ የሚችል›› የሚለው ግንኙነቱ ጉዳት ሊያስከትል ይችል ይሆናል የሚል ጥርጣሬን ወይም ግምትን መሰረት ያደረገ እንጂ ጉዳት መድረሱን ማረጋገጥ የሚጠይቅ አይደለም፡፡ ስለሆነም የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን፣ ለጋሽ መንግስታትና አጋር ተቋማትን ጨምሮ ከውጭ ሀገራት ወይም ድርጅቶች ጋር የሚደረግ የስራ ግንኙነት ሁሉ በኮማንድ ፖስቱ አይን ሀገርን ሊጎዳ ይችላል ተብሎ ከታሰበ ይህን ድንጋጌ መተላለፍ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል፡፡

በሌላ በኩል፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የወጣው በአማራና በኦሮሚያ የነበረውን ህዝባዊ ተቃውሞ ተከትሎ ሆኖ ሳለ፣ ምንም አይነት (የጎላ) የጸጥታ መደፍረስም ሆነ የተቃውሞ ሁኔታ ያልታየባቸውን አብዛኛዎቹን የሀገሪቱ ክልሎች ጨምሮ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሰብዓዊ መብቶችን በሚገድብ ሁኔታ ተግባራዊ መደረጉ፣ አዋጁ ከወጣበት ምክንያት ወሰን ያለፈ መሆኑን ያሳያል፡፡

በዚህ በሰመጉ 142ኛ ልዩ መግለጫ ላይ እንደተመለከተው አዋጁ ከታወጀ በኋላ በአፈጻጸም ላይ በርካታ ችግሮች ማለትም የንብረት ዝርፊያ፣ ግድያ፣ ድብደባና ማቁሰል፣ እንዲሁም የጅምላ እስር የመሳሰሉት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የተፈጸሙ ሲሆን፣ ከእነዚህም ውስጥ በመንግስት ጭምር የታመኑ ግድፈቶች ይገኙባቸዋል፡፡ በየጊዜው የመብት ጥሰት የተፈጸመባቸው ዜጎች ለሰመጉ ያቀረቡት አቤቱታም ሆነ የሰመጉ የምርመራ ውጤት የሚያሳየው፣ የአዋጁን አፈጻጸም እንዲቆጣጠር የተቋቋመው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድም በሕገ መንግስቱ የተሰጠውን ስልጣን ተጠቅሞ ተገቢውን ምርመራ በማድረግ ጥሰቶቹን ለማስቀም በቂ ስራ አለመስራቱን ነው፡፡ ቦርዱ የምርመራውን ውጤት በየገዜው ይፋ እንደሚያደርግ በአዋጁ የተደነገገ ቢሆንም፣ ይህንን ኃላፊነቱን በአጥጋቢ ሁኔታ ሲወጣም ሆነ ጥሰት ፈጻሚዎችን በይፋ ተጠያቂ ሲያደርግ አልታየም፣ ለሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ምርመራው ተገቢውን መረጃ እንዲሰጠው ሰመጉ ላቀረበው ጥያቄም ከቦርዱ ቀና ምላሽ አልተገኘም፡፡

መንግሥት ከአዋጁ ጋር አያይዞ በሰጠው ማብራሪያ፣ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አፈጻጸም ወቅት ለሰብዓዊ መብቶች መጠበቅ ልዩ ጥንቃቄ ይደረጋል የሚል ቃል መግባቱም ይታወሳል፡፡ ሆኖም አዋጁን ተከትሎ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ አፈጻጸም መመሪያ ልዩ ልዩ ይዘቶች በጥንቃቄ ለተመለከተ፣ መንግሥት ለሰብዓዊ

---

[3] የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር አንድ፣ አንቀጽ 3 ይመለከቷል

[4] የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር አንድ፣ አንቀጽ 16 ይመለከቷል

መብቶች መከበር በገባው ቃልና አዋጁ በሚያዘው አፈጻጸም ረገድ ልዩነት እንደሚኖር መረዳት አይከብድም ነበር፡፡ ሰመጉም ይኸው ሥጋት ነበረበት፡፡ ሰመጉ አዋጁና አዋጁን ተከትለው የወጡ መመሪያዎችን ይዞትና መንፈስ በከፍተኛ የሕግ ባለሙያ አባሉቹና ሠራተኞቹ ጭምር ጊዜ ወስዶ በጥንቃቄ መርምሯል፡፡ በምርመራውም የአዋጁና የአፈጻጸም መመሪያዎቹ ልዩ ልዩ አንቀጾች ግልጽነት የጎደላቸውና ለተለያዩ ትርጉሞች ክፍት ሆነው አግኝቷቸዋል፡፡ ይህም በመርሐ ግብሮቹ አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ይኖረዋል ብሎ በመስጋቱና ስጋቱን ለመቀነስ እንዲሁም ባለው የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ የሰብዓዊ መብቶች ጥረቱን ለመቀጠል ከነበረው ጽኑ ፍላጎት በመነሳት ሰመጉ በወቅቱ ከመንግሥት ማብራሪያ በደብዳቤ ጠይቋል፡፡

አዋጁ መስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም. ወጥቶ፣ ሰመጉ ደብዳቤውን ለመንግሥት ያቀረበው ጥቅምት 14 ቀን 2009 ዓ.ም (በቁጥር ER3/M1/02/16) ነው፡፡ ይህ ደብዳቤ በዋናነት የተጻፈው ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት ሲሆን የኢፌዴሪ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽንና የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ግልባጭ ተደርጎላቸው ለሁሉም ደብዳቤው በእጅ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ ሰመጉ ለኮማንድ ፖስቱ ያስገባው የማብራሪያ መጠየቂያ ደብዳቤ ዋና ይዘቱ እንደሚከተለው ነበር:

1. የመመሪያው አንቀጽ አንድ: <u>ሁከትና ብጥብጥ የሚያስነሳ ግንኙነት ማድረግ</u>
   - ሰመጉ ሰብዓዊ መብቶችን በሚመለከት የሚያከናውናቸው ስራዎች፣ የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች፣ የሚሰጣቸው መረጃዎችና ይፋ የሚያደርጋቸው መግለጫዎች የኢትዮጵያ መንግሥት የሰብዓዊ መብት ይዞታውን እንዲያሻሽል የሚረዱ እንጅ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ሆነ የሀገርን ሉዓላዊነትና ደህንነት የሚጎዱ ናቸው ብሎ ባያምንም በዚህ ረገድ የኮማንድ ፖስቱ ትርጓሜ ምን እንደሆነ ቢገለጽልን፣
2. የመመሪያው አንቀጽ 3: <u>ሰላማዊ ሠልፍና የአደባባይ ስብሰባ</u> ማካሄድ
   - በዚህ አንቀጽ የተቀመጠው ገደብ ሰመጉ በመደበኛነት የሚያካሂዳቸውን የሰብዓዊ መብቶች ትምህርት መርሐግብሮች፣ የአባላትና ሠራተኞች የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች፣ ጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ የአባላት የውይይት መድረኮች ... ይመለከት እንደሆን እና
3. አንቀፅ 16: <u>የተከለከሉ የውጭ ግንኙነቶች</u>
   - ሰመጉ አንጋፋና ብቸኛ መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች አጣሪ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን፣ ሥራዎቹን በሚመለከት ከተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽነር ፅ/ቤት፣ ከአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን እንዲሁም በመላው ዓለም የሰብዓዊ መብት ሥራ ከሚያከናውኑ አጋር የውጭ ድርጅቶች ጋር ቅርብ የሥራ ግንኙነት አለው፡፡ በዓለም አቀፍ፣ በአሕጉራዊና በክልላዊ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ውስጥ አባልም ነው፡፡ ሰመጉ ሰብዓዊ መብቶችን በሚመለከት ከነዚህና መሰል አካላት ጋር የሚያደርጋቸው የውጭ ግንኙነቶች የሀገርን ሉዓላዊነትም ሆነ ደህንነት ወይም ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን ሊጎዱ የሚችሉ ናቸው ብሎ አያምንም፡፡ አንቀጽ 16 በዚህም ላይ ገደብ ይጥል እንደሆን ማብራሪያ እንዲሰጠን የሚጠይቅ ነበር፡፡

ሰመጉ አያይዞም፣ የአስቸኳይ ጊዜ ኮማንድ ፖስቱን ጨምሮ ማናቸውም የሪፐብሊኩ ሕግ አውጭ፣ ተርጓሚና አስፈጻሚ አካላት በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉትን ሰብዓዊ መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ እንዳለባቸው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13(1) በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ፣ ኮማንድ ፖስቱ ይህንኑ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ጥበቃ የማድረግና ሥራቸውንም የመደገፍ ኃላፊነት ጭምር እንዳለበት አስታውሷል፡፡ በተጨማሪም ሰመጉ *በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አፈጻጸም ወቅት፣ አዋጁ ያስቀመጣቸውን ገደቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት* የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝ በቅርብ በመከታተል፣ ጥሰቶች ሲከሰቱም ምርመራ በማድረግና ውጤቱን ለኮማንድ ፖስቱ፣ ለመርማሪ ቦርዱ እና ለሕዝብ ጭምር ይፋ በማድረግ የሰብዓዊ መብት ጥበቃው እንዲጠናከር አቅሙ በሚፈቅደው መጠን የሚተባበር መሆኑን ለአስቸኳይ ጊዜ ኮማንድ ፖስቱ ሴክሬታርያትና ግልባጭ ለተደረገላቸው አካላት ሁሉ አረጋግጧል፡፡

ሰመጉ በደብዳቤ ላቀረበው የማብራሪያ ጥያቄ መደበኛ የጽሁፍ ምላሽ አላገኘም፡፡ መከላከያ ሚኒስትሩ ከሚመሩት የዋናው ኮማንድ ፖስት ሴክሬታሪያት የተገኘው የቃል መልእክት ለጥያቄያችን ምላሽ በወቅቱ ይሰጡ ከነበሩ የኮማንድ ፖስቱ ጋዜጣዊ መግለጫዎች ማግኘት እንደምንችል የሚገልጽ ነበር፡፡ ሆኖም መግለጫዎቹ ለሰመጉ ስጋትና ጥያቄዎች ቀጥተኛና የተሟላ ምላሽ የሚሰጡ ስላልነበሩ፣ ሰመጉ በተቻለ መጠን በአዋጁ ድንጋጌዎች አተረጓጎም ልዩነት ረገድ ከሚፈጠሩ ችግሮችና አደጋዎች ድርጅቱን፣ ሠራተኞቹንና አባሎቹን ለመጠበቅ ሲል በበርካታ የመርሐ ግብር ተግባራቱ ላይ ማዕቀብ ለመጣል ተገድዷል፡፡ በዚህ መሠረት፣ ጥቂት የማይባሉ የመርሐ ግብር ክንዋኔዎቹን (የፓናል ውይይቶችን፣ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርቶችን፣ ጋዜጣዊ ጉባዔዎችንና መግለጫዎችን፣ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫዎችን እንደየሁኔታቸው ማቋረጥ፣ ወይም ለሌላ አመቺ ጊዜ ማስተላለፍ፣ ወይም መጠናቸውን ቀንሶ በጥንቃቄ መስራት ግድ ሆኖበታል፡፡ ሰመጉ ሊያካሂድ ያቀዳቸውን የውስጥ የአቅም ግንባታ የስልጠና ሥራዎችን ሳይቀር ለሚመለከታቸው (የክልል ኮማንድ ፖስት) ጽ/ቤቶች በማሳወቅ ለመሥራት ተገዷል፡፡ በዚህ አጋጣሚ በወቅቱ ጥያቄ ቀርቦላቸው ከነበሩት የደቡብና የአማራ ክልል ኮማንድ ፖስት ጽ/ቤቶች እንዲሁም ከአዲስ አበባ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ላገኘው ቀና ምላሽ ሰመጉ ዕውቅና ሊሰጥ ይወዳል፡፡ በተጨማሪም ሰመጉ የመርሐ ግብር እንቅስቃሴዎቹን ከአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር በተቻለ መጠን አጣጥሞ ማካሄድ ከቻለ በሚል የራሱን የውስጥ የሥራ መመሪያ በጽሁፍ አውጥቶ ለሠራተኞችና ለአባላቱ አሳውቆ በዚሁ መሠረት ሥራዎቹን ለማከናወን ጥረት አድርጓል፣ እያደረገም ነው፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በሰመጉ ሥራዎች ላይ ካስከተላቸው ከፍተኛ ጉዳቶች መካከል ሌላኛው፣ ሰመጉ በጥቅምት 13 ቀን በደሣለኝ ሆቴል (አዲስ አበባ) በማካሄድ ላይ የነበረው የድጋፍ ማሰባሰቢያ የምሣ ግብዣ ሥነ ሥርዓት ሳይጠናቀቅ በጸጥታ ኃይሎች ትዕዛዝ እንዲቋረጥ መደረጉ ነው፡፡ ሥነሥርዓቱ፣ ጉዳዩ በሚመለከተው የበጎ አድራጎትና ማኅበራት ኤጀንሲ የጽሁፍ ፈቃድ ተሰጥቶት የፈቃዱ ወረቀትም በአዳራሹ ውስጥ በሚታዩ ልዩ ልዩ ሥፍራዎች ተለጥፎ ይገኝ ነበር፡፡ የጸጥታ ኃይሎችም ዋናውን የፈቃድ ደብዳቤ እንዲያሳዩ የሰመጉን አመራሮች በጠየቁ ጊዜም አሳይተዋቸዋል፡፡ ሆኖም "ኮማንድ ፖስቱ ፈቃድ ያልሰጠበት ዝግጅት ስለሆነ አቋርጡ" ስለተባለ ሰመጉ ሥነሥርዓቱን ለማቋረጥ ተገዷል፡፡ በዚህ ምክንያት በሰመጉ ላይ የደረሰው ኪሣራና ወከባ ዘርፈ ብዙ ነበር፡፡ ሰመጉ ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት ሴክሬታሪያት በጻፈው ደብዳቤ ላይ የዕርዳታ ማሰባሰቢያ መርሐ ግብሩ፣ አንደኛ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ፈቃድ ተጠይቆና ተገኝቶ የተካሄደ ሕጋዊ ዝግጅት መሆኑ፣ ሁለተኛም የምሣ ግብዣ እንጂ የአደባባይ ስብሰባ አለመሆኑ እየታወቀ በፀጥታ ኃይሎች እንዲቋረጥ መደረጉ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ ቅሬታውን አቅርቧል፡፡

ሰመጉ ለኮማንድ ፖስቱ በጻፈው በዚሁ ደብዳቤ ላይ በገባው ቃልና በዕቅዱም መሠረት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አፈጻጸም ወቅት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለማጣራት ባለሙያዎቹን ወደመስክ አሰማርቶ ምርመራዎችን አካሂዷል፡፡ ሰመጉ ባለሙያዎቹን ከማሰማራቱም በፊት ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ ጽ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ (በቁጥር ER3-M41/04/17)፣ ጽ/ቤቱ በበኩሉ ባደረገው ክትትልና ማጣራት ያገኘውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መረጃና ማስረጃዎች እንዲያካፍለው ጠይቋል፡፡ ነገር ግን ይህ ልዩ መግለጫ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ከቦርዱ የተገኘ መረጃ ወይም ማስረጃ የለም፡፡ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከታወጀ በኋላ በኦሮሚያ፣ በአማራና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል (በጌዴዖ ዞን) እንዲሁም ከቂሊንጦ ማረሚያ ቤት ቃጠሎ ጋር በተያያዘ ስለነበረው ሁኔታ የምርመራ ሥራዎችን በመሥራት ሪፖርቶቹን ለተወካዮች ምክር ቤት ማቅረቡ ይታወሳል፡፡ ይህ የኮሚሽኑ እርምጃና የተወካዮች ምክር ቤትም ሪፖርቱን ማስተናገዱም ለሰመጉ የማይናቅ መልእክት ሰጥቶታል፡፡ ይኸውም የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ - ሰመጉም የራሱን ሪፖርት በዚህ ጊዜ ይፋ ቢያደርግ ወቅታዊና ምናልባትም ከወትሮው በተሻለ ሁኔታ የመንግሥትን ተገቢና ገንቢ ትኩረት ሊያገኝ እንደሚችልም ጠቋሚ ሆኖታል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትን ዕውነታዎች ሁሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔም ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በኋላ የተፈጸሙትን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በሚመለከት ይህን 142ኛ ልዩ መግለጫ አውጥቷል፡፡

## 4. የምርመራው ግብና ሥልቶች

### 4.1 የልዩ መግለጫው ዋና ዓላማ

ቀደም ብሎ እንደተመለከተው ሰመጉ በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች በተመሳሳይ ጊዜ በተካሄዱት የሕዝብ ተቃውሞዎች ወቅት የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለማጣራት፣ በየክልሎቹ ልዩ ልዩ አካባቢዎች በተደጋጋሚ በመገኘት የመስክ ምርመራ አካሂዷል።

የዚህ ልዩ መግለጫ ዓቢይ ዓላማ መስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከወጣ በኋላ የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሕጋዊ መፍትሔ እንዲሰጣቸው፣ ጥሰቶች እንዲቆሙና ሌሎች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችንም የመከላከል እርምጃ እንዲወሰድ ለማሳሰብ ነው። በተለይም ከአዋጁ በፊትና በአዋጁ ወቅትም የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ብዛትና አይነት እንዲሁም ምክንያትና ውጤት በስፋትና በጥልቀት ተጣርቶ እስካሁን ከተገኘው በላይ አጥጋቢ መረጃና ማስረጃዎች ማግኘት እንዲቻል፣ መንግሥት በተለይም ሰመጉን በነጻነትና በስፋት ለመሥራት የሚያስችለውን የአቅምና የፖለቲካ ሁኔታ እንዲያመቻች፣ ለተቋሙ ተገቢውንና ከሥራ ፈቃድ መስጠት የዘለለ ዕውቅናና ድጋፍ እንዲሰጥና ለሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች (ለሰመጉ ሠራተኞችና አባላት) ጥበቃ እንዲያደርግ ለመጠየቅ ነው። በተጨማሪም ለአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን፣ ለተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽ/ቤትና ለሌሎችም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማት ነጻና ገለልተኛ ምርመራ እንዲያደርጉ ፈቃድ እንዲሰጥ ለማሳሰብም ነው። የነዚሁ ሁሉ ጥረቶች ከፍተኛ ግብ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ፈፃሚዎች በህግ እንዲጠየቁ፣ ጥሰት ፈጽሞ ሳይጠየቁ መቅረት እንዲቆም፣ ተጎጂዎች ተገቢውን ዓይነትና መጠን ካሳ እንዲካሱ፣ ሰብዓዊና ስነልቦናዊ ድጋፍ እንዲደረግላቸውና ተመሳሳይ የመብት ጥሰቶች በድጋሚ የማይፈጸሙበት የፖሊሲና የአሰራር ማስተካከያዎችና እርማቶች ከወዲሁ በተጨባጭ እንዲደረጉ መጠየቅ ነው።

### 4.2 ምርመራውና ልዩ መግለጫው የተመሠረተበት የህግ ማዕቀፍ

በዚህ ልዩ መግለጫ ውስጥ ይፋ የተደረጉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ዓይነትና ዘርፍ ለመረዳትና ለማሳየት በዋና መሠረትነት የሚያገለግሉት፣ የኢ.ፌዴሪ ህገ መንግስት፣ የአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብቶች ቻርተር እና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውና ግዴታም የገባችባቸው የተለያዩ የዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ናቸው። የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በየዘርፋቸው በተገለጹበት ቦታ ሁሉ እነዚህ የሕግ ማዕቀፎች በመነሻነትና በማመሳከሪያነት ተጠቅሰዋል።

### 4.3 በምርመራው የተሸፈኑ አካባቢዎችና ምርመራው የተካሄደበት ጊዜ

ይህ መግለጫ የሚመለከተው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከወጣበት ከመስከረም 28 እስከ ግንቦት 2009 ድረስ በኦሮሚያ በአማራና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ነው። ሰመጉ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አፈጻጸም ወቅት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለማጣራት የመስክ ምርመራውን ያካሄደው በየካቲት 2009 ነው።

ነገር ግን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከመታወጁ (ከመስከረም 28 2009) በፊትና የሰመጉ የመጨረሻ ሪፖርቶች ማለትም 140ኛ (መጋቢት 2008) እና 141ኛ (ግንቦት 2008) ከወጡ በኋላ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ ክልል በኮንሶና ብጌዴዖ እንዲሁም በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ሰመጉ በየአካባቢዎቹ የሰብዓዊ መብቶች ምርመራ ባለሙያዎቹን በማሰማራት አጣርቷል። ሰመጉ 140ኛ ልዩ መግለጫውን ካወጣበት ከመጋቢት 2008 እስከ መስከረም 2009 አጋማሽ ድረስ በኦሮሚያ ክልል የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በሐምሌ 2008 ዓ.ም. የምርመራ ስምሪቱ አጣርቷል። 141ኛ ልዩ መግለጫውን ካወጣበት ከግንቦት 2008 እስከ መስከረም 2009 አጋማሽ ድረስ በአማራ ክልል የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ደግሞ በነሐሴ 2008 ዓ.ም. የምርመራ ስምሪቱ አጣርቷል። በተመሣሣይ ሁኔታ ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በፊት በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል በሰገን ሕዝቦች ዞን (በኮንሶ) እና በጌዴዖ ዞን በዜጎች ላይ የተፈጸሙ የሰብዓዊ

መብቶች ጥሰቶችንም አጣርቷል፡፡ ስለዚህ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከመታወጁ በፊት የደረሱት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በዚህ በ142ኛ ልዩ መግለጫ ውስጥ አልተካተቱም፡፡ የነዚህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ምርመራዎች ውጤት በቅርብ ጊዜ ይፋ ይሆናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በዚህ 142ኛ ልዩ መግለጫ የተካተተው ግን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ተግባራዊ መሆን ከጀመረበት ከመስከረም 28 2009 ጀምሮ የደረሰ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ነው፡፡ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ተፈጻሚ እየሆነ ባለበት ወቅት ሰመጉ ምርመራ ያካሄደባቸው ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ተመልክተዋል፡

ሠንጠረዥ ሀ፡ በዚህ ምርመራ የተሸፈኑ ዞኖችና ወረዳዎች[5]

| | የክልሉ ስም | ዞን | ወረዳ | | የክልሉ ስም | ዞን | ወረዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኦሮሚያ ክልል | 1.1 ምሥራቅ ሐረርጌ | 1.1.1 ደደር<br>1.1.2 ሜታ | 2 | አማራ ክልል | 2.1 አዊ ዞን | 2.1.1 ዳንግላ |
| | | 1.2 ምዕራብ ሐረርጌ | 1.2.1 ጭሮ<br>1.2.2 አሰቦት<br>1.2.3 ሚኤሶ | | | 2.2 ምዕራብ ጎጃም | 2.2.1 ቡሬ<br>2.2.2 ጃቢ ጣህና (ፍኖተ ሰላም)<br>2.2.3 ባሕርዳር ዙሪያ (ጢስ አባይ) |
| | | 1.3 ምሥራቅ ወለጋ | 1.3.1 ጉደያ ቢላ | | | 2.3 ሰሜን ጎንደር | 2.3.1 ጎንደር |
| | | 1.4 ምዕራብ ወለጋ | 1.4.1 ነጆ<br>1.4.2 ቢላ<br>1.4.3 ወረጅሩ<br>1.4.4 ቦጂ<br>1.4.5 ዩብዶ<br>1.4.6 ቤጊ | | | 2.4 ደቡብ ጎንደር | 2.4.1 ደብረታቦር |
| | | 1.5 ቄለም ወለጋ | 1.5.1 ነሸን<br>1.5.2 እምቢልታና ሰማሮ<br>1.5.3 ታቦር | 3 | ደቡብ ክልል | 3.1 ሰገን ሕዘቦች | 3.1.1 ኮንሶ ደራሼ |
| | | 1.6 ሆሮ ጉድሩ ወለጋ | 1.6.1 ጉድሩ ፊዬ | | | 3.2 ከምባታ ጠምባሮ | 3.2.1 ጠምባሮ ወረዳ |
| | | 1.7 ምዕራብ አርሲ | 1.7.1 አሳሳ | 4 | አዲስ አበባ መስተዳድር | የካ፣ ቦሌ፣ ቂርቆስ፣ አራዳ፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ ልደታ፣ ኮልፌ ቀራንዮ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ እና አዲስ ከተማ ክፍለከተሞች | |
| | | 1.8 አርሲ | 1.8.1 ሽርካ | | | | |
| | | 1.9 ምሥራቅ ሸዋ | 1.9.1 ባቱ (ዝዋይ)<br>1.9.2 ቢሾፍቱ | | | | |
| | | 1.10 ምዕራብ ሸዋ | 1.10.1 ጀልዱ<br>1.10.2 አምቦ<br>1.10.3 ጌዶ<br>1.10.4 ጉደር | | | | |

## 4.4 የመረጃ ምንጮችና የማስረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) ይህንን ምርመራ በሚያካሂድበት ወቅት ግኝቶቹን ለማረጋገጥና ለማጠናከር በቀጥታ ከተጎጂዎችና ከተጎጂ ቤተሰቦች አቤቱታና ማስረጃ፣ ከምስክሮች የምስክርነት ቃል፣ ድርጊቱ በተፈፀመባቸው አካባቢዎች በአካል በመገኘት ሁኔታውን በማየትና በማጥናት፣ ከአካባቢው ነዋሪዎች በመረዳት እንዲሁም በተቻለበት ጊዜ ሁሉ ከመንግስት አካላት መረጃና ማስረጃ ተሰባስቧል፡፡

[5] በሠንጠረዡውስጥ የተዘረዘሩት ቦታዎች የሰመጉ ባለሞያዎች በአካል ተገኝተውምርመራ ያካሄዱባቸውናቸው ከነ ዚህ በተጨማሪ ከጉጂ ዞን አራጋ ወረዳ፣ ከቦረና ዞን ገላና ወረዳ፣ እንዲሁምከጠላይና ከአዋሽ አርባ ተጎጂዎች ሰመጉ ዋና ጽ/ቤት ድረስ በአካል ቀርበው[illegible]ተካትቷል፡ ፡



የሰብዓዊ መብቶች ጉባ...

### 4.5 የምርመራ ስራው ውሱንነትና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) አሁን የሚገኝበት ውሱን የሰው ኃይል፣ የገንዘብና የምርመራ ቁሳቁስ አቅም የሰብዓዊ መብቶች ቀውሶቹ በሚጠይቁት መጠንና ስፋት በሁሉም አካባቢዎች ለመስራት አላስቻለውም፣ ተጎጂዎችና ቤተሰቦች እንዲሁም ምስክሮች በተለይ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ምክንያት በከፍተኛ ፍርሀት ውስጥ መሆንና በሚፈለገው መጠን ትብብር አለማድረግ፣ ከሚመለከታቸው የተለያዩ የመንግት አካላት ቀና እና በቂ ትብብርና እገዛ አለማግኘት በዚህ የምርመራ ስራ ሂደት ወቅት ትልቅ ተግዳሮት ፈጥረዋል። በዚህ ልዩ መግለጫ ውስጥ ማንነታቸው ይፋ የተደረገ እስረኞች ብዛታቸው ከፍተኛ የሚባል ነው። ስለነዚህ እስረኞች በተለያየ መንገድ ያገኘናቸውን መረጃዎች ለማረጋገጥና ለማነፃፀር ያስችለን ዘንድ በአዲስ አበባ የሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎችን ለመጎብኘት እንዲፈቀድልን ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በመጋቢት 21/2009 ዓ.ም በቁጥር ER3-M41/05/17 ጠይቀን ነበር። እንዲሁም የፌዴራል ማረሚያ ቤቶችን መጎብኘት እንድንችል ለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በሚያዝያ 02/2009 ዓ.ም በቁጥር ER3-M41/5/17 በፃፍነው ደብዳቤ ጠይቀናል። ሆኖም ወደ ጽ/ቤቶቹ በተደጋጋሚ ብንመላለስና ብንጠይቅም ይህ ልዩ መግለጫ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ምላሽ አላገኘንም። እንዲሁም ሰመጉ ለተለያዩ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በቀን ጥር 16/2009 ዓ.ም ቁጥር ER3-M41/03/17 በተጻፈ ደብዳቤ ፓርቲዎቹ ስለታሰሩባቸው አመራሮች፣ አባላትና ደጋፊዎች ሁኔታ መረጃ እንዲሰጡ የጠየቀ ቢሆንም ከአብዛኞቹ ፓርቲዎች ምላሽ አልተገኘም። ዘግይተውም ቢሆን ምላሽ የሰጡት መኢአድ፣ ሰማያዊ ፓርቲና ኦፌኮ ብቻ ናቸው። ይሁንና ከላይ እንደተገለጸው ከመንግሥት አካላት ምላሽም ሆነ ትብብር ባለመገኘቱ ከፓርቲዎቹ የተገኘውን መረጃ በእስር ቤት ተገኝቶም ሆነ ከመንግስት በኩል ያለውን መረጃ በማነጻጸር ለማጣራት አልተቻለም። በመሆኑም ከተጠቀሱት የፖለቲካ ፓርቲዎች (በማሕተም) እና ከአቤቱታ አቅራቢዎችና ከምስክሮች የተቀበለውን መረጃ ባለበት ሁኔታ ሪፖርት ለማድረግ ተገዷል። በሌላ በኩል የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ - ሰመጉ፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በቅርቡ ለተወካዮች ምክር ቤት ያቀረባቸውን ዘገባዎች ቅጂ እንዲሰጠው ኮሚሽኑን በደብዳቤ ቁጥር ER3-M43/01/17 በቀን ሚያዝያ 18 2009 ዓ.ም ጠይቆ ነበር። ያገኘው ምላሽ፣ ሪፖርቱ በማተሚያ ቤት ታትሞ የሚሠራጨው በየዓመቱ በሰኔ ወር ላይ ስለሆነ በሚቀጥለው ሰኔ ወር 2010 ዓ.ም. ጠብቁ የሚል ነው። ወደፊትም ሰፊና ዝርዝር ጥናት ለማድረግ እንዲችል ሰመጉ የሚመለከታቸውን የመንግሥት አካላት ትብብር በድጋሚ ይጠይቃል።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ፣ ማረሚያ ቤቶችን መጎብኘት በህግ የተፈቀደለት የመርሐ ግብር ተግባሩ ነው። በዚህ መሠረት በቅርቡ ለመፈጸም ከያዘው ዕቅዱ አንጻር፣ በየአካባቢው የሚገኙ ማረሚያ ቤቶችና ፖሊስ ጣቢያዎችን ለመጎብኘት ሰመጉ ለተወሰኑ መንግሥታዊ ተቋማት በደብዳቤ ጥያቄ አቅርቧል፣ ከነዚህ አካላት መካከልም አንዳንዶቹ አዎንታዊ ምላሽ በደብዳቤ መስጠታቸውን በዚህ አጋጣሚ መግለጽ ተገቢ ይሆናል። እነዚህ የመንግሥት አካላት ሰመጉ በሕግ ለተፈቀደለት ሥራ ዕውቅና ሰጥተውና ሕጉን አክብረው ላሳዩት አበረታች ትብብር ሰመጉ ምሥጋናውን ያቀርባል።

## 5. አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀ በኋላ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 "እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት" እንዳለው ያረጋግጣል። ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳንም በአንቀጽ 6 (1) እና 9 (1) ላይ ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል ኪዳኑ የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸዉ የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም አንቀጽ 2(1) እና (2) ይደነግጋል።

የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 4 "ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት ሊከበርለትና ሊጠበቅለት ይገባል። ማንም እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፍገው አይገባም" ይላል። የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 14 "ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው" ሲል ይደነግጋል። የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 20(1) ሁሉም ሕዝቦች የራሳቸውን የፖለቲካ ዐቋም ይወስናሉ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማታቸውን ራሳቸው በነጻነት በመረጡት ፖሊሲ መሠረት ያካሄዳሉ በማለት ይደነግጋል። ኢትዮጵያም ይህንን ቻርተር የተቀበለች ሀገር እንደመሆኗ እነዚህን ሰብዓዊ መብቶች የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ ተጥሎባታል።

በመላው ሀገሪቱ እየተባባሰና መልኩን እየቀየረ የመጣው ሕዝባዊ ተቃውሞ ያሳሰበው የኢትዮጵያ መንግሥት የሚኒስትሮች ም/ቤት መስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 1/2009 አውጇል፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ዜጎች ከሕግ አግባብ ውጭ ተገድለዋል፣ ቆስለዋል፣ ተደብድበዋል፣ በመደበኛ እሥር ቤቶችና ከመደበኛ እሥር ቤቶች ውጭ በርካታ ሰዎች ለእስር ተዳርገዋል፣ የደረሱበት የማይታወቅም በርካታ ናቸው፡፡

## 5.1 አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀ በኋላ የተፈጸመ በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ ወጥ ግድያ)

1. ሟች ደገፉ ሽፈራው፤ ዕድሜ 29፣ ሥራ ገበሬ፣ በምዕራብ ወለጋ ዞን፣ በላሎ ወንጅ ላሎ አሳቢ ወረዳ በመስከረም 28 2009 ዓ.ም ከቤቱ ሲወጣ በቤቱ በር ላይ በመከላከያ ሠራዊት አባላት በጥይት ቀኝ ጉኑ ላይ ተመቶ ወደቀ፤ ቤተሰቦቹ ጊምቢ ሆስፒታል ወስደውት መስከረም 29 ቀን 2009 ዓ.ም ከምሽቱ 3 ሰዓት ላይ በሆስፒታል እንዳለ ሕይወቱ አልፏል፡፡ ግድያው የተፈጸመው፣ ቀደም ብሎ በላሎ ወንጅ የኢሬቻን ቀውስ ተከትሎ ከተካሄደና ከዚያም በፊት ከነበሩት የተቃውሞ ሠልፎች ጋር በተያያዘ መሆኑን ምስክሮች ለሰመጉ ገልጸዋል፡፡ አስከሬኑን ከሆስፒታል በማውጣት በመስከረም 30 2009 ዓ.ም በጃርሶ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ተፈጽሟል፡፡



2. ሟች መገርሳ በድሉ ዕድሜ 28፣ በቄለም ወለጋ ዞን፣ በሰዮ ወረዳ በሳማድ ቀበሌ በመከላከያ ሠራዊት አባላት በመስከረም 28 2009 ዓ.ም በጥይት ተገድሏል፡፡



3. ሟች ንጋቱ እምሩ ዕድሜ 26፣ በምዕራብ ወለጋ ዞን፣ በላሎ ወንጅ በመከላከያ ሠራዊት አባላት በመስከረም 28 2009 ዓ.ም በጥይት ተገድሏል፡፡ ግድያው የተፈጸመው፣ ቀደም ብሎ በላሎ ወንጅ የኢሬቻን ቀውስ ተከትሎ ከተካሄደና ከዚያም በፊት ከነበሩት የተቃውሞ ሠልፎች ጋር በተያያዘ መሆኑን ምስክሮች ለሰመጉ ገልጸዋል፡፡
4. ሟች ጌቱ ታምሩ ዕድሜ 33፣ በምዕራብ ወለጋ ዞን፣ በላሎ ወንጅ በመከላከያ ሠራዊት አባላት በመስከረም 28 2009 ዓ.ም በጥይት ተገድሏል፡፡ ግድያው የተፈጸመው፣ ቀደም ብሎ በላሎ ወንጅ የኢሬቻን ቀውስ ተከትሎ ከተካሄደና ከዚያም በፊት ከነበሩት የተቃውሞ ሠልፎች ጋር በተያያዘ መሆኑን ምስክሮች ለሰመጉ ገልጸዋል፡፡



5. ሟች ኢፋ ደንገታ ዕድሜ 19፣ በቄለም ወለጋ ዞን፣ ደምቢ ዶሎ ከተማ ታቦር ቀበሌ በጥቅምት 02 2009 ዓ.ም ከምሽቱ 1 ሰዓት ላይ ከጓደኞቹ ጋር በመንገድ ላይ እየሄዱ ሳሉ በመከላከያ ሠራዊት አባላት በጥይት ተገድሏል። የቀብር ሥነ ሥርዓቱ በጥቅምት 03 2009 በገረኩስ ሰጠ ሙሉ ወንጌል ተፈጽሟል።



6. ሟች ለታ ሊካሳ ዕድሜ 30፣ በቄለም ወለጋ ዞን፣ ደምቢ ዶሎ ከተማ 06 ቀበሌ በ ጥቅምት 18 2009 ዓ.ም በመከላከያ ሠራዊት አባላት በጥይት ተገድሏል።



7. ሟች ኮኒሳ ሊካሳ ዕድሜ 26፣ በቄለም ወለጋ ዞን፣ ደምቢ ዶሎ ከተማ ኦዶ ቀበሌ፣ በጥቅምት 18 2009 ዓ.ም ከምሽቱ 2:30 በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች በጥይት ተገድሏል። የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ሸጎ ሙሉ ወንጌል የቀብር ሥፍራ ተፈጽሟል።
8. ሟች ኢብሳ ቤከታ ቀንዓ ዕድሜ 30፣ ሥራ የመንግሥት፣ ምሥራቅ ወለጋ፣ ዲጋ ወረዳ፣ አርጆ ጉደቱ ከተማ በጥቅምት 16 2009 ዓ.ም ከጠዋቱ 1 ሰዓት በመከላከያ ሠራዊት አባላት ቀኝ ታፋውና ቀኝ ጐኑ ላይ በጥይት ተመቶ ነቀምቴ ሆስፒታል ከገባ በኋላ ሕይወቱ አልፏል። በጥቅምት 17 2009 ላይ ነቀምቴ ጠለለቂ መካነ ኢየሱስ የቀብር ቦታ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ተፈጽሟል።



9. ሟች ደረጀ ተስፋዬ ዕድሜ 18፣ ሥራ ተማሪ፣ ቄለም ወለጋ፣ ደምቢ ዶሎ ሰዬ ወረዳ፣ ታቦር ቀበሌ በጥቅምት 02 2009 ዓ.ም አመሻሽ ላይ በመከላከያ ሠራዊት አባላት በመኖሪያ ቤቱ ደጃፍ ላይ በጥይት ተመቶ ደምቢ ዶሎ ሆስፒታል ሲታከም ቆይቶ በጥቅምት 07 2009 ዓ.ም ህይወቱ አልፎአል። በጥቅምት 08 2009 በዳሌ መካነ ኢየሱሱ ቤተ ክርስቲያን የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ተፈጽሟል።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

10. ሟች ደሳለኝ ጋሪ ዕድሜ 28፣ ሥራ የመንግሥት ሠራተኛ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ቦጂ ወረዳ በጥቅምት 25 2009 ዓ.ም በመንግሥት ሠራተኞች ስብሰባ ላይ ሃሳብ ሲያቀርብ ነበር፡፡ በጥቅምት 26 2009 ዓ.ም በመኖሪያ ቤቱ እንዳለ ፖሊሶች የመኖሪያ ቤቱን በር ሰብረው ገብተው እየደበደቡ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወስደውታል፡፡ ቦጂ ፖሊስ ጣቢያ ፖሊሶች ሲደበድቡት ቆይተው ሕይወቱ በድብደባ አልፏል፡፡



11. ሟች ማዕረጉ ጀማሎ፡ ዕድሜ 25፣ ሥራ ነጋዴ፣ ነዋሪነቱ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ጎቤሳ 01 ቀበሌ ሲሆን መስከረም 30 ቀን 2009 ዓ.ም. ከቀኑ 10 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ከሁለት ወንድሞቹ ጋር በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንዳሉ፣ የመከላከያ ሰራዊት አባላት የሆኑ ወታደሮች የቤታቸውን በር በመስበርና ከቤት በማስወጣት በቤቱ በራፍ ላይ ከሁለት ወንድሞቹ ጋር (ተ.ቁ 12፣13) በመከላከያ ሰራዊቶች በጥይት ተገድሏል፡፡
12. ሟች አብዲሳ ጀማሎ : ዕድሜ 18፣ ሥራ ከነጋዴ ወንድሙ (ማዕረጉ ጀማሎ) ጋር አብሮ የንግድ ስራ ይሰራ የነበረ፣ ነዋሪነቱ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ጎቤሳ 01 ቀበሌ ሲሆን መስከረም 30 ቀን 2009 ዓ.ም. ከቀኑ 10 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ከሁለት ወንድሞቹ ጋር በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንዳሉ፣ የመከላከያ ሰራዊት አባላት የቤታቸውን በር በመስበርና ከቤት በማስወጣት በቤቱ በራፍ ላይ ከሁለት ወንድሞቹ ጋር (ተ.ቁ 11፣13) በመከላከያ ሰራዊቶች በጥይት ተገድሏል፡፡
13. ሟች ቶላ ጀማሎ፡ ዕድሜ 22፣ ሥራ ገበሬ፣ ነዋሪነቱ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ጎቤሳ 01 ቀበሌ ሲሆን መስከረም 30 ቀን 2009 ዓ.ም. ከቀኑ 10 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ከሁለት ወንድሞቹ ጋር በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንዳሉ፣ የመከላከያ ሰራዊት አባላት የሆኑ ወታደሮች የቤታቸውን በር በመስበርና ከቤት በማስወጣት በቤቱ በራፍ ላይ ከሁለት ወንድሞቹ ጋር (ተ.ቁ 11፣12) በመከላከያ ሰራዊት አባላት በጥይት ተገድሏል፡፡ ሦስቱ ወንድማማቾችና መሐመድ በያኖ (ተራ ቁጥር 15) በጥቅምት 1 2009 ዓ.ም አንፎቴ የሙስሊሞች የቀብር ሥፍራ ሁለት ጉድጓድ ተቆፍሮ በአንዱ ጉድጓድ ሁለቱ ወንድማማቾች ሲቀበሩ አንዱ ጉድጓድ ላይ ደግሞ መሐመድና አንደኛው ወንድማቸው ተቀብረዋል፡፡
የሦስቱ ሟቾቹ እናት በመኖሪያ ግቢያቸው የተፈጸመውን ግድያ ከተመለከቱ በኋላ የታመሙ ሲሆን የሟቾቹ አንዷ እህታቸውም ወንድሞቿ ሲገደሉ ከአየች በኋላ የአእምሮ መታወክ ደርሶባት ምርመራው በሚካሄድበት ወቅት በህመም ላይ ትገኝ ነበር፡፡
14. ሟች መሀመድ በያኖ፡- ዕድሜ 23፣ ሥራ ገበሬ፣ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ሶሬ ፈረንቀላ ቀበሌ ላይ በመስከረም 3 2009 ዓ.ም. ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ በመከላከያ ሰራዊት አባላት ተገድሏል፡፡ በጥቅምት 1 2009 ዓ.ም. ኦንፎቴ የሙስሊሞች የቀብር ሥፍራ ከሦስቱ ወንድማማቾች ጋር ተቀብሯል፡፡
15. ሟች ቦጃ (መኮንን) በቀለ ምስራቅ ወለጋ፣ ዲጋ ወረዳ፣ ገመቺሳ ቀበሌ ከአጎቶቹ ጋር እየኖረ በመማር ላይ ነበር፡፡ ጉዳዩን በቅርብ የሚያውቁ የአይን እማኝ ለሰመጉ እንደገለጹት "ትምህርት ቤት ለሁለት ሳምንት ስለተዘጋ የፋሲካ በአልን ከቤተሰቦቹ ጋር ለማሳለፍ ወደ ወሬ አካባቢ መጣ፡፡ በሚያዝያ 5 2009 ዓ.ም. ማምሻውን ጓደኞቹ ጋር ለማደር እራት በልቶ ወጣ፡፡" እንደ ምስክሮቹ ገለጻ፣ በዚሁ ቀን ከሌሊቱ 7 ሰኣት ላይ በዲጋ ወረዳ ቢቂላ ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ ባልታወቀ ሰው በጥይት ተገድሏል፡፡ "ሲነጋ ወደቤት ሳይመጣ ሲቀር ጓደኞቹን ጠየቅን፡ ጓደኞቹም ፖሊስ ጣቢያ ጠይቁ ባሉት መሠረት፣ የአክስቱ ልጅ ፖሊስ ጣቢያ ሄዳ ስትጠይቅ ፖሊሶች ፎቶውን አሳዩአት፤ እርሷም ወንድሟ መሆኑን ገልጻላቸው፣ ቤት ደርሳ ለቤተሰቦቹና ለዘመዶቹ እስከምትነገር ድረስ ፖሊሶቹ አስከሬኑን በቀን ሰራተኞች አማካኝነት፣ በሚያዝያ 6 2009 ዓ.ም. በጂካ መካነየሱስ ቤተክርስቲያን፣ ጥልቀቱ ከአንድ ሜትር በማይበልጥ ጉድጓድ ውስጥ በሽራ

ጠቅልለው እንዲቀበር አድርገዋል። "የሟች ቤተሰቦች ፖሊሶችን ጠይቀው ማን እንደገደለውና ለምን ከቤተሰብ ተደብቆ እንደተቀበረ ጠይቀዋል። በኂላም በፖሊስ የተቀበረውን አስከሬን በማውጣት በሚያዝያ 7 2009 ዓ.ም. ወላጆቹና ዘመዶቹ በተገኙበት በሙሉ ወንጌል ቤተክተርስቲያን የቀብር ሥነ ሥርአቱ እንደተፈፀመ የሟች አባት ለሰመጉ አመልክተዋል።

ከቀብሩ በኂላ የሟች አባት ፖሊስ ጣቢያ ሲያመለክቱ፣ "ማመልከት አያስፈልጋችሁም እኛው (ፖሊሶች) እናጣራለን፣ ሦስት ወርም ስድስት ወርም ሊወስድ ይችላል፤ በእለቱ የነበሩ የሟች ጓደኞች ተይዘው በቁጥጥር ስር ይገኛሉ" የሚል መልስ ተሰጣቸው። የሟች ቤተሰብ ጉዳያቸውን ለመከታተል ፖሊስ ጣቢያ ቀርበው ሲጠይቁ፣ "እናንተ አትመላለሱ፣ እኛ ስንጠራችሁ ብቻ ትመጣላችሁ" በማለት ጉዳያቸውን እንዳይከታተሉ ተከልክለዋል። "ፖሊስ ጣቢያውም በእለቱ የተመደቡ ፓትሮል ፖሊስ አባላትን ማንነት እያወቀ ምርመራው በአግባቡ እንዲጣራ አላደረገም፤ የወረዳው አስተዳደር ጋ ሄደን ብናመለክትም ጉዳዩ እንዲጣራ ያደረገው አስተዋጽኦ የለም። ሟች የአካባቢው ሰው መሆኑን ፖሊሶች እያወቁ እንዲሁም የአክስቱ ልጅ በፖሊስ እጅ ያየችው ፎቶግራፍ የወንድሟ መሆኑን ገልጻላቸው ሳለ፣ ለቤተሰብ ሳያሳውቁ በቀን ሰራተኞች ለመቅበር የተጣደፉበት ምክንያት እንቆቅልሽ ሆኖብናል" ሲሉ የሟች አባት አቶ በቀለ ዋቅጅራ ለሰመጉ በሚያዝያ 26 2009 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ ገልጸዋል።



16. ሟች መ/ር ካሳታ ኞኬ ግዳያ ፆታ ወንድ፣ ዕድሜ 32፣ የት/ት ደረጃ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ኮንሶ ወረዳ፤ መጨሎ ቀበሌ ነዋሪ ነበር። ታሕሳስ 05 ቀን 2009 ዓ.ም. ኮንሶ ወረዳ ዶከቱ አካባቢ ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት አካባቢ ዩኒፎርም የለበሰ የመከላከያ ሠራዊት አባል ሟች መ/ር ካሳታን እና ሌሎች ሁለት ሰዎችን ከኂላቸው ሲያባርራቸው መ/ር ካሳታ ተደናቅፎ መውደቁን፤ ከወደቀበት ለመነሳት ሲሞክር በተተኮሰበት ጥይት ጭንቅላቱ ላይ ተመትቶ መገደሉን በስፍራው የነበሩ የዓይን ምስክሮች ለሰመጉ አረጋግጠዋል። በነጋታው ታሕሳስ 06 ቀን 2009 ዓ.ም. ከቀኑ 5፡00 ሰዓት አካባቢ የመከላከያ ሠራዊት አባላት የመ/ር ካሳታ ኞኬን አስከሬን በመከላከያ ሠራዊት መኪና አምጥተው መጭሎ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት በራፍ ላይ የጣሉት ሲሆን በዕለቱ በቤተሰቡ ባሕላዊ የቀብር ሥፍራ የቀብር ስርዓቱ ተፈፅሟል። መ/ር ካሳታ ባለትዳርና የሶስት (3) ልጆች አባት ነበር። መምሕር ካሳታ የቤተሰቡ ብቸኛ ደጋፊ ከመሆንም አልፎ በእድሜ የገፉ አባቱንም ጠዋሪ ነበር።



መ/ር ካሳታ ኞኬ


የመ/ር ካሳታ ኞኪ ባለቤት ወ/ሮ ካሰች ገልገሎ እና ሶስት ልጆቻቸው

17. ሟች አይላኖ ግዳያ ፆታ ወንድ፣ እድሜ 55፣ በኮንሶ ወረዳ፤ መጨሎ ቀበሌ አባሮባ መንደር ነዋሪ የነበሩ፤ አቶ አይላኖ በግብርና ሥራ ይተዳደሩ የነበሩ ሲሆን ባለትዳርና የስምንት (8) ልጆች አባት ነበሩ። ሟች ሕዳር 27 ቀን 2009 ዓ.ም. ከምሽቱ 5 ሰዓት አካባቢ በመጨሎ ቀበሌ አባሮባ መንደር በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው እያሉ በተተኮሰባቸው የጅምላ ተኩስ አንገታቸው ላይ በጥይት ተመትተው ተገድለዋል። የሟች ቤተሠቦች ለሰመጉ እንደገለጹት የድርጊቱ ፈጻሚዎች በአካባቢው ሰፍረው ከነበሩት የመከላከያ ሠራዊት፤ የፌዴራል

ፖሊስ እና የደቡብ ክልል ልዩ ኃይል መካከል ናቸው። አቶ አይላኖ ግዳያ ታሕሳስ 05 ቀን 2009 ዓ.ም. ኮንሶ ወረዳ፤ መጨሎ ቀበሌ ዶከቱ አካባቢ በመከላከያ ሠራዊት የተገደለው መ/ር ካሳታ ኖኬ ግዳያ (ተራ ቁ. 17) አጐት ነበሩ።

18. ሟች ዋና ሳጅን ገመዳ ሮባ ፆታ ወንድ፣ እድሜ 49፤ በኮንሶ ወረዳ የካራት አካባቢ ነዋሪና የፖሊስ ሠራዊት አባል ነበሩ። ዋና ሳጅን ገመዳ ሮባ ከኮንሶ ሕዝብ የዞን ይገባኛል ጥያቄ ጋር ተያይዞ ሠራተኞች ስራ በማቆማቸውና (የፖሊሶችን ጨምሮ) የሁሉም መንግሥት ሠራተኞች ደሞዝ በመቋረጡ ምክንያት ቤተሰባቸውን ለማስተዳደር ብለው የፖሊስነት ሥራቸውን በመተው ወደ ግብርና ሥራ ገብተው ነበረ። ዋና ሳጅን ገመዳ ሮባ ጥቅምት 12 ቀን 2009 ዓ.ም. ከረፋዱ 4:00 ሰዓት አካባቢ በሰገን ጨራቅሌ (ቡርጂ ድንበር) አካባቢ በእርሻ ስራ ላይ እያሉ በታጠቀ የፖሊስ አባል በተተኮሰባቸው ጥይት ኩላሊታቸው ላይ ተመትተው ተገድለዋል። ከግድያው ጋር በተያያዘ ሁለት ሰዎች በኮንሶ ፖሊስ ጣቢያ ታስረው የሚገኙ ሲሆን እስከ ሚያዝያ 18 ቀን 2009 ዓ.ም. ድረስ ክስ አልተመሰረተባቸውም። ዋና ሳጅን ገመዳ ባለትዳርና የአስር (10) ልጆች አባት ነበሩ።



19. ሟች አቶ ምክሩ ቸኮል እድሜ 64፣ በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ጢስ ዓባይ ቀበሌ 01፤ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ ባለትዳርና የስድስት ልጆች አባት ነበሩ። "ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ተሳትፈሀል" በሚል ምክንያት ጥቅምት 22 ቀን 2009 ዓ.ም ከቀኑ 6 ሰዓት ላይ የፀጥታ ሀይሎች ደጋግመው በተኮሱባቸው ጥይት ሽንጣቸውንና አናታቸውን ተመትተው ተገድለዋል። አቶ ምክሩ ጢስ ዓባይ ባዕታ ማርያም ቤተክርስቲያን የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል። ሟች አቶ ምክሩ ቤተሰቦቻቸውን በሚሰሩት የግብርና ስራ በብቸኝነት የሚያስተዳድሩ ነበሩ። በመሆኑም ቤተሰቡ የሚያግዛቸው ባለመኖሩ ምክንያት በከፍተኛ ችግር ላይ መውደቃቸውንና የቤተሰብ አባላትም በችግር ምክንያት መበተናቸውን በመግለፅ የሟች ባለቤት ለሰመጉ አመልክተዋል።



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

## 5.2 እስራት

የኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀፅ 17(2) እና የዓለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ድንጋጌ አንቀፅ 9 ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጪ በዘፈቀደ ሊያዝ እንደማይችል፤ እንዲሁም ክስ ሳይቀርብበት ወይም ለፍርድ ሳይቀርብና ሳይፈረድበት አይታሰርም በማለት ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 9 ይህንኑ መብት ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪም በኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀፅ 18(1) ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ኢሰብዓዊ አያያዝ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ በአንቀፅ 19(3) ላይ ደግሞ የተያዙ ሰዎች በ48 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ፍርድ ቤት መቅረብ እንዳለባቸው በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም የአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብት ቻርተር አንቀፅ 6 ማንኛውም ሰው ነፃነቱና አካላዊ ደህንነቱ ተጠብቆለት የመኖር መብት አለው በተለይም ማንም ሰው በዘፈቀደ ሊታሰር ወይም ሊያዝ አይችልም በማለት ደንግጓል፡፡ ኢትዮጵያም ይህንን ቻርተር ፈርማ የተቀበለች ሀገር በመሆኗ በዚህ ቻርተር ውስጥ የተደነገጉትን መብቶች፣ ግዴታዎችና ነፃነቶች አውቃ ለተግባራዊነታቸውም እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ አለባት፡፡

ከዚህ በላይ የተደነገጉትን ህገመንግስታዊና ዓለማቀፋዊ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በመደበኛና ከመደበኛ እስር ቤቶች ውጭ በቀበሌ አዳራሾች፣ በገበሬ ማህበር ፅ/ቤቶች፣ በመንግስት የመምህራን ኮሌጆች፣ በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ በጦር ማሰልጠኛ ካምፖች… በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ለጤንነት በማይመች ሁኔታ ታስረዋል፡፡ ሰመጉ ያለው ውሱን አቅምና እጅግ አስቸጋሪና አስፈሪው የፖለቲካ ድባብ በፈቀደው መጠን ባደረገው ማጣራት ያገኘው የምርመራ ውጤት እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

**ሠንጠረዥ 1፡ በመጀመሪያው ዙር ከመስከረም 29 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 12 ቀን 2009 ዓ.ም የታሰሩ ዜጎች[6]፡**

| ተ ቁ | የታሠሩ ሰዎች ብዛት | የታሣሪዎች ማንነት/ የመጡበት ሥፍራ | የታሰሩበትጊዜ | የታሠሩበት ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 37 | የኮንሶ ተወላጆች[7] | ከ25/02/2009 ጀምሮ | በኮንሶ ኢንዱስትሪያል ኮሌጅ | የዞን ይገባኛል ጥያቄ አንስታችኋል ተብለው |
| 2 | 572 | የኮንሶ ተወላጆች | | አቦስቶ ፖሊስ ኮሌጅ | |
| 3 | 440 | የኮንሶ ተወላጆች | | ኮንሶ ቴክኒክና ሞያ ት/ት | |
| 4 | 75 | በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን ከአጄና ሰንበቴ ሻላ ወረዳዎች | ከ09/03/2009 ጀምሮ | አላጌ ግብርና ኮሌጅ | |
| 5 | 2600 | የጌዴኦ ተወላጆች | 29/01/2009 | በዲላ መምህራን ኮሌጅ | |
| 6 | 33 | በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን | ከ22/02/2009 ጀምሮ | በአላጌ ግብርና ኮሌጅ | |
| 7 | 6 | በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ጉጂ ዞን ዱግዳ ዳዋ ወረዳ አርበኞ ቀበሌ | | ለቴሌቪዥርን ጣቢያነት በተሰራ ሥፍራ | |
| 8 | 1174 | ከአዲስ አበባ ዙሪያ፣ ከሰሜንና ምስራቅ ሸዋ | | በአዋሽ ወታደራዊ ካምፕና በይርጋለም ፖሊስ ማሠልጠኛ | |
| 9 | 4329 | ከወለጋ፣ አርሲና ምስራቅ ሸዋ | | በጦላይ ጦር ካምፕ | |
| 10 | 3048 | ከጉጂ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሀረርጌ | | ዝዋይ ዞን ማረሚያ ቤት | |
| 11 | 2114 | ከጌድኦ | | በዲላና ይርጋለም ማቆያ | |
| 12 | 532 | ከሰሜንና ደቡብ ጎንደር ተይዘው የታሰሩ | | ባህርዳር ማቆያ | |
| 13 | 410 | ከአዲስ አበባ ከተማ ከተለያዩ ክፍለ ከተሞች | | በአዲስ አበባ ልዩ ልዩ ፖሊስ ጣቢያዎች | |
| **በመጀመሪያው ዙር ታስረው የነበሩ ሰዎች ድምር** | | | 15,370 | | |

6 በመጀመሪያው ዙር የታሰሩ፣ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስትም መግለጫ መሠረት መፈታታቸው ይፋ ከተደረገው እስረኞች መካከል ከፊሎቹ ናቸው፤ በህዳር 4 ቀን 2009 ዓ.ም በወጣው ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ይፋ እንደተደረገው፡፡

7 በዕድሜ ለዐቅመ አዳምና ሔዋን የደረሱ የኮንሶ ተወላጆች በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች የሚደርስባቸውን እሥራት፣ ድብደባና ግድያ በመሸሽ ጫካ ውስጥ ተደብቀው ነው የሚኖሩት፡፡

| በሁለተኛው ከታህሳስ 13 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ጥር 26 ቀን 2009 ዓ.ም ዙር ታስረው የነበሩ[8] | | | |
|---|---|---|---|
| ተ ቁ | የታሠሩ ሰዎች ብዛት | የታሰሩበት ጊዜ | የታሠሩበት ቦታ |
| 1 | 1180 | ከታህሳስ 13 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥር 26 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ | በአዋሽ ሰባት ኪሎ የጦር ማሰልጠኛ ካምፕ |
| 2 | 5643 | | ጦላይ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ጣቢያ |
| በመጀመሪያው ዙር ታስረው የነበሩ ሰዎች ድምር | | 6,823 | |
| በሁለቱ ዙሮች የታሰሩት ሰዎች ጠቅላላ ድምር | | 22,193 | |

## ሰንጠረዥ 2፡ በምዕራብ አርሲ ዞን ውስጥ ከተለያዩ አካባቢዎች የታሰሩ ዜጎች ስም ዝርዝር

| ተ. ቁ | የታሣሪው ሙሉ ስም | የመኖሪያ አድራሻ | መተዳደሪያ ሙያ | የታሠረበት ምክንያት | የታሠረበት ቀን | የታሠረበት እሥር ቤት | አሁን ያለበት ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ሸኩር ሀጂ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 02/02/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 2 | አቶ አራርሶ ዋቁሼ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 02/02/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 3 | አቶ በሪሶ አሳሳ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 02/02/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 4 | አብድሮ በሪሶ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 3/02/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 5 | ተማም ጂሎ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 7/3/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 6 | አብዱል ጃቢር | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 7/3/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 7 | ሼህ ቃሲም ሻሌ ደቀበ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርገዋል በሚል | 4/3/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስረው ይገኛሉ |
| 8 | አቶ ጀዋሮ ሻሌ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 4/3/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 9 | አቶ ጀዋሮ ሁሴን | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 4/3/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 10 | አቶ ሁሴን ደማ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 02//02/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 11 | አብሹ ዋዩ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 03/03/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 12 | ዘውዱ በላይ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 03/03/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 13 | አቶ ሁሴን ዋለቻ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 02/02/09 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 14 | ሙሣ ሣይድ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 6/3/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 15 | አቶ ሙሀመድ ወልዱ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 4/03/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 16 | ሳፋዮ በደሠ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 3/3/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛ |
| 17 | ቃሲሞ ንያ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 3/3/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖስ ጣቢያ ታስሮ ገኛል |

[8] ይህ ቁጥር ከተለያዩ የሐገሪቱ ክፍሎች ተይዘው በአዋሽ ሰባት እና በጦላይ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ብቻ የታሰሩ ዜጐች ብዛት ሲሆን በሌሎች እስር ቤቶች የታሰሩ ዜጐችን ቁጥር አያካትትም

| ተ.ቁ | የታሣሪው ሙሉ ስም | የመኖሪያ አድራሻ | መተዳደሪያ ሙያ | የታሠረበት ምክንያት | የታሠረበት ቀን | የታሠረበት እሥር ቤት | አሁን ያለበት ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 18 | አቡ ሣይድ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 3/3/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 19 | ወ/ሮ ፋጡማ ፍቃዱ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጋለች በሚል | 2/2/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስራ ትገኛለች |
| 20 | ሼህ ከድር አራርሶ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርገዋል በሚል | 2/2/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስረው ይገኛሉ |
| 21 | አቶ ሀጅ ኬሲሳ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 10/3/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 22 | አቶ ከድሮ ፉራ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 10/3/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 23 | ሱልጣን ፉራ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 6/3/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 24 | ሙዛይን ሰይድ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 1/4/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 25 | አቶ አልይ ወዩ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 9/03/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 26 | ነጌሶ ጎሌ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 1/4/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 27 | ዳውድ ኤብሶ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 1/4/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 28 | ኤዳሶ ኤብሶ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 1/4/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 29 | አቶ ሐሶ ቱኬ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 7/3/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 30 | ጉታ ኬሲሶ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 1/4/2009 | አሳሳ ፖሊስ ጣቢያ | ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል |
| 31 | አዳም ራሽድ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 1/4/2009 | መረጃ አልተገኘም | መረጃ አልተገኘም |
| 32 | አማን አብደኔ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 6/3/2009 | መረጃ አልተገኘም | መረጃ አልተገኘም |
| 33 | በዳሶ ሂኮ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 6/3/2009 | መረጃ አልተገኘም | መረጃ አልተገኘም |
| 34 | ሙክተር አብደላ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 3/3/2009 | መረጃ አልተገኘም | መረጃ አልተገኘም |
| 35 | ሙሀመድ ሁሴን | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 3/3/2009 | መረጃ አልተገኘም | መረጃ አልተገኘም |
| 36 | ሙሳ ዋቤ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 1/4/2009 | መረጃ አልተገኘም | መረጃ አልተገኘም |
| 37 | ወ/ሮ ሽምሲያ ዋትቻ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጋለች በሚል | 2/2/2009 | መረጃ አልተገኘም | መረጃ አልተገኘም |
| 38 | ወ/ሮ ማድና አቦሴ | | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጋለች በሚል | 2/2/2009 | ጦላይ | ከእስርቤት ተፈታለች |
| 39 | አቶ ኤደኦ ቡርቃ | ቡጂ ቀበሌ ገ/ማህበር | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 7/3/2009 | ጦላይ | ከእስር ቤት ተፈቷል |
| 40 | አቶ አበሺ ከድር | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 4/3/2009 | ጦላይ | በ 25/5/09 ተተፈቷል |
| 41 | አቶ አደም ሄቦ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 6/3/2009 | ጦላይ | በ 25/5/09 ተፈቷል |
| 42 | አቶ ከድር አምቱ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 6/3/2009 | ጦላይ | በ 25/5/09 ተፈቷል |

| ተ.ቁ | የታሣሪው ሙሉ ስም | የመኖሪያ አድራሻ | መተዳደሪያ ሙያ | የታሠረበት ምክንያት | የታሠረበት ቀን | የታሠረበት እሥር ቤት | አሁን ያለበት ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 43 | አቶ አብዱላሂ መሀመድ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 7/3/2009 | ጦላይ | በ 25/5/09 ተፈቷል |
| 44 | አቶ ሀሙ ደናቦ | ኬላ ቀበሌ ገ/ማ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 4/3/2009 | ጦላይ | በ 25/5/09 ተፈቷል |
| 45 | ወጣት ሙስጠፋ ኤደኦ | ኬላ ቀበሌ ገ/ማ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 3/3/2009 | ጦላይ | በ 25/5/09 ተፈቷል |
| 46 | ወጣት ኢሳ ሀጂ ስልጣን | ኬላ ቀበሌ ገ/ማ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 3/3/2009 | ጦላይ | በ 25/5/09 ተፈቷል |
| 47 | ወጣት ሙሳ ሀጂ | ኬላ ቀበሌ ገ/ማ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 3/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 48 | ሼህ አደም ሐምዳ ቀበቶ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርገዋል በሚል | 3/2/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈተዋል |
| 49 | ሐምዳ ደንበባ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 3/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 50 | አርባ ዋቤ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 7/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 51 | ቃሲም ጀርሦ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 4/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 52 | አበድላ ሾና | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 4/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 53 | ቃሲም ኡርፋሳ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 3/2/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 54 | አብደላ በሪሶ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 3/2/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 55 | ሀጂ ወሰይ | አሣሣ | ገበሬ | ›› ›› | 6/3/2009 | ጦላይ | በ25/5/09 ተፈቷል |
| 56 | ፋትያ ሀ/ሄቦ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጋለች በሚል | 9/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈታለች |
| 57 | ቃሲም ሄባኖ | አሣሣ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 7/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 58 | ከማል በዳሶ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 4/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 59 | ከዲጃ አብደላ | አሣሣ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጋለች በሚል | 4/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈታለች |
| 60 | ኢማን ሀጂ | አሣሣ(ሰርቦ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጋለች በሚል | 3/2/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈታለች |
| 61 | ቶንሳ ኑሬ | አሣሣ(ሰርቦ | ገበሬ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 7/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 62 | ሻኖ ሀጂ | አሣሣ(ሰርቦ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 7/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 63 | አልይ ሙስጠፋ | አሣሣ(ሰርቦ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 10/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 64 | ቃሲም ማሙ | አሣሣ(ሰርቦ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 4/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 65 | ጣህር ፉጮ | አሣሣ(ሰርቦ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 2/2/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 66 | ከድር ዱቤ | አሣሣ(ሰርቦ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 4/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 67 | አብዱራይማን ደምሴ | አሣሣ(ሰርቦ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 9/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |

| ተ.ቁ | የታሣሪው ሙሉ ስም | የመኖሪያ አድራሻ | መተዳደሪያ ሙያ | የታሠረበት ምክንያት | የታሠረበት ቀን | የታሠረበት እሥር ቤት | አሁን ያለበት ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 68 | አቦስ ሀጂ | አሣሣ(ሰርቦ | ተማሪ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 7/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 69 | ሀጂ ዋሪዮ | አሣሣ(ሰርቦ | ገበሬ | መንግስትን ተቃውመዋል በሚል | 6/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 70 | አቦድ ሀጂ | አሣሣ(ሰርቦ | ገበሬ | መንግስትን ተቃውመዋል በሚል | 7/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 71 | ሀጂ እርቦ ሰፋዊ | አሣሣ | ነጋዴ | ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል በሚል | 7/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈተዋል |
| 72 | ሀጂ ፉራ ነገዎ | ›› | ገበሬ | ›› | 02/02/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈተዋል |
| 73 | አብዲ ተኪሶ | ›› | ገበሬ | ›› | 02/02/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈተዋል |
| 74 | አብድላ ኪንሶ | ›› | ነጋዴ | ›› | 04/02/2009 | ጦላይ | በ 04/04/2009 ተፈተዋል |
| 75 | ጀይላን ካዲ | ›› | ነጋዴ | ›› | 04/02/2009 | ጦላይ | በ 04/04/2009 ተፈተዋል |
| 76 | ካዱ ጋናሞ | ›› | ነጋዴ | ›› | 04/02/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈተዋል |
| 77 | ሙሀመድ ጋናሞ | ›› | ነጋዴ | ›› | 04/03/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈተዋል |
| 78 | አደም ታፋ | ›› | ነጋዴ | ›› | 03/03/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈተዋል |
| 79 | ጣሀር ሀሙ | ›› | ነጋዴ | ›› | 03/03/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 80 | ተስፋዬ ዲዳ | ›› | ተማሪ | ›› | 03/03/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 81 | ራሰቂ አብዱራማን | ›› | ተማሪ | ›› | 05/03/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 82 | ሳፊ ሀጂ ሚሚ | ›› | ገበሬ | ›› | 06/03/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 83 | ሙባረክ ብርማጂ | ›› | ገበሬ | ›› | 7/03/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 84 | ባራካት ብርካ | ›› | ተማሪ | ›› | 10/03/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 85 | ሀጂ ሹብሳ | ›› | ገበሬ | ›› | 10/03/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 86 | አማን ካዮ | ›› | ገበሬ | ›› | 09/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 87 | አብዱራማን ሽጉጤ | ›› | ገበሬ | ›› | 08/3/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 88 | ጀማል ጉደታ | ›› | ገበሬ | ›› | 01/03/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 89 | ሁሴን ኮፋ | ›› | ገበሬ | ›› | 02/03/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 90 | ከማል ኮፋ | ›› | ገበሬ | ›› | 02/03/2009 | ጦላይ | በ 25/05/09 ተፈቷል |
| 91 | አቢቾ ኡርጌሳ | ›› | ገበሬ | ›› | 01/04/2009 | ጦላይ | መረጃ አልተገኘም |
| 92 | ሙሀመድ አማና | ›› | ነጋዴ | ›› | 01/04/2009 | ጦላይ | መረጃ አልተገኘም |
| 93 | አማን ሄቦ ሹራ | ›› | ገበሬ | ›› | 01/04/2009 | ጦላይ | መረጃ አልተገኘም |
| 94 | አብቲ ሄቦ ነጌሶ | ›› | ተማሪ | ›› | 01/04/2009 | ጦላይ | መረጃ አልተገኘም |

ማስታወሻ ፡ ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ ውስጥ የተዘረዘሩት የታሳሪዎች ሁኔታ የሚያሳየው እስከ የካቲት አጋማሽ ያሉበትን ሁኔታ ብቻ ነው።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

ከዚህ በታች በሠንጠረዥ 3፣ 4 እና 5 በስም የተጠቀሱት ሰዎች መታሰራቸውን የሚያረጋግጡ ከፓርቲዎቹ የተገኙ ደብዳቤዎች በሰመጉ እጅ ይገኛሉ፡፡

## ሰንጠረዥ 3፡ በእስር ላይ የሚገኙ የሰማያዊ ፓርቲ አባላት ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ. | የታሳሪው ሙሉ ስም | ጾታ | የተያዘበት ቦታ | በእስር ላይ የሚገኝበት ቦታ | በፓርቲው ውስጥ ያላቸው ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ በረከት ተገኔ | ወ | አርባምንጭ | ቂሊንጦ | የወላይታ ዞን ሰብሰቢ |
| 2 | አቶ አለም ክንፈ | ወ | አርባምንጭ | ቂሊንጦ | በወላይታ ዞን አባል |
| 3 | አቶ ጌታሁን ካተሳ | ወ | አርባምንጭ | ቂሊንጦ | በወላይታ ዞን አባል |
| 4 | አቶ በጋሻው ዱንጋ | ወ | አርባምንጭ | ቂሊንጦ | በወላይታ ዞን አባል |
| 5 | አቶ ሲሳይ አምባው | ወ | አርባምንጭ | ቂሊንጦ | በወላይታ ዞን አባል |
| 6 | አቶ አጥናፉ አበራ | ወ | | ቂሊንጦ | አባል |
| 7 | አቶ መኳንንት ካሳሁን | ወ | ደቡብ ወሎ | ማዕከላዊ | በደሴ የወጣቶች ጉዳይ ሀላፊ |
| 8 | አቶ ብስራት አቢ | ወ | ደቡብ ወሎ ደሴ | ማዕከላዊ | በደሴ የድርጅት ጉዳይ ሀላፊ |
| 9 | ሀምሳ አለቃ ንጉሴ ዳጀው | ወ | ምዕራብ ጎጃም | ባህርዳር | የምዕራብ ጎጃም ምክትል ሰብሳቢ |
| 10 | አቶ አዱኛ ካሳው | ወ | ምዕራብ ጎጃም | ባህር ዳር | በምዕራብ ጎጃም አካባቢ አባል |
| 11 | አቶ በድሉ መንግስቱ | ወ | ምዕራብ ጉጂ | ገላና ቶሬ ፖሊስ ጣቢያ | የምዕራብ ጉጂ ዞን ሰብሳቢ |
| 12 | አቶ ጌቱ ጎንፋ | ወ | ምዕራብ ጉጂ | ገላና ቶሬ ፖሊስ ጣቢያ | በምዕራብ ጉጂ ዞን አካባቢ አባል |
| 13 | አቶ ገላኖ ጊሎ | ወ | ምዕራብ ጉጂ | ገላና ቶሬ ፖሊስ ጣቢያ | በምዕራብ ጉጂ ዞን አካባቢ አባል |
| 14 | አቶ አራርስ ጌዶ | ወ | ምዕራብ ጉጂ | ገላና ቶሬ ፖሊስ ጣቢያ | በምዕራብ ጉጂ ዞን አካባቢ አባል |
| 15 | አቶ ጎዳና ሽንሩ | ወ | ምዕራብ ጉጂ | ገላና ቶሬ ፖሊስ ጣቢያ | በምዕራብ ጉጂ ዞን አካባቢ አባል |

## ሰንጠረዥ 4፡ በተለያዩ አካባቢዎች ታስረው የሚገኙ የኦሮሞ ፌደራላዊ ኮንግሬስ (ኦፌኮ) አመራር፣ አባላትና ደጋፊዎች ስም ዝርዝር በከፊል[9]

| ተ.ቁ. | የታሳሪው ሙሉ ሥም | ጾታ | ተ.ቁ | የታሳሪው ሙሉ ሥም | ጾታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዶ/ር መረራ ጉዲና | ወንድ | 18 | አቶ አጥናፉ ብራሳ | ወንድ |
| 2 | አቶ መርጋ ደበሎ | ወንድ | 19 | አቶ አጥናፉ ታደሰ | ወንድ |
| 3 | አቶ አሚን ዮዮ | ወንድ | 20 | አቶ ዋዩ ቤካ | ወንድ |
| 4 | አቶ አብዲ ዮሱፍ | ወንድ | 21 | አቶ አብደታ ባትሪ | ወንድ |
| 5 | አቶ አብዱልዋሴ ኢብራሂም | ወንድ | 22 | አቶ አብዱልዋህድ ሐጂ ጉሬ | ወንድ |
| 6 | አቶ አብዱቃድር ኢብራሂም | ወንድ | 23 | አቶ አዩብ ሐጂ ጉሬ | ወንድ |
| 7 | አቶ አብዱልቃድር መሀመድ | ወንድ | 24 | አቶ አብዲ ዋቤ | ወንድ |
| 8 | አቶ ሸምሰዲን አህመድ | ወንድ | 25 | አቶ በከሪ ኦርማማና | ወንድ |
| 9 | አቶ መሀመድ አሊዩ | ወንድ | 26 | አቶ ዳውድ ዴኮ | ወንድ |
| 10 | አቶ መሀመድ ሶፊያን | ወንድ | 27 | አቶ አሼ ብሪካ | ወንድ |
| 11 | አቶ አብዲ መሀመድ | ወንድ | 28 | አቶ ቀኖ አስቻለው | ወንድ |
| 12 | አቶ ጀማል ቶፊቅ | ወንድ | 29 | አቶ ሀብታሙ ሐጫሉ | ወንድ |
| 13 | አቶ ፍሮምሳ ሀምሶ | ወንድ | 30 | አቶ ቶኩማ ሙሊሳ | ወንድ |
| 14 | አቶ ሐሩን አዩቦ | ወንድ | 31 | አቶ ደጋጋ ብርሃኑ | ወንድ |
| 15 | አቶ ጀማል አዩቦ | ወንድ | 32 | አቶ ዮሐንስ ኡርጌሳ | ወንድ |
| 16 | አቶ አህመድ ከሊፋ | ወንድ | 33 | አቶ ዴቢሳ ባሊና | ወንድ |
| 17 | አቶ ከሊፋ መሀመድ | ወንድ | 34 | አቶ አብዱራሂም አደም | ወንድ |

[9] ከነዚህ ግለሰቦች መካከል በርካታዎቹ በሽብር ተከሰሰው ጉዳያቸው በፍርድ ቤት በማየት ላይ ይገኛል፡፡

| ተ.ቁ. | የታሳሪው ሙሉ ሥም | ጾታ | ተ.ቁ. | የታሳሪው ሙሉ ሥም | ጾታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 35 | አቶ ብሩ ገለቱ | ወንድ | 69 | አቶ ዮሴፍ ዲዳ | ወንድ |
| 36 | አቶ ያሲን መሀመድ | ወንድ | 70 | አቶ ተስፋዬ በቀለ | ወንድ |
| 37 | አቶ ተሾመ ረጋሳ | ወንድ | 71 | አቶ ደባላ ፌቱ | ወንድ |
| 38 | አቶ ጫላ ዴያስ | ወንድ | 72 | አቶ ናአል ሻምሮ | ወንድ |
| 39 | አቶ ብሉስማ ኩማ | ወንድ | 73 | አቶ ለታ አህመድ | ወንድ |
| 40 | አቶ ኒሞና ለሜሳ | ወንድ | 74 | አቶ አብዲ ያሲን | ወንድ |
| 41 | አቶ ከበደ ጨማዳ | ወንድ | 75 | አቶ ሐጂ ጣሃ | ወንድ |
| 42 | አቶ ደበላ በየነ | ወንድ | 76 | አቶ መሀመድ እስማኤል | ወንድ |
| 43 | አቶ ምህረቱ ጉልማ | ወንድ | 77 | አቶ ከማል አብርሃም | ወንድ |
| 44 | አቶ ጌታሁን ደስታ | ወንድ | 78 | አቶ ማማ አሊ | ወንድ |
| 45 | አቶ መንግስቱ ጉዲሳ | ወንድ | 79 | አቶ ሽፋ ጣሃ | ወንድ |
| 46 | አቶ ተሰማ ሁንዴ | ወንድ | 80 | አቶ ከድር አህመድ | ወንድ |
| 47 | አቶ ቦንሳ ሀይሉ | ወንድ | 81 | አቶ አሽረፉ ቡሮ | ወንድ |
| 48 | አቶ አሸብር ኦንቾ | ወንድ | 82 | አቶ አሽረፈዲን መሀመድ | ወንድ |
| 49 | አቶ ጅራ ኦብሳ | ወንድ | 83 | አቶ አዲናን አሊ | ወንድ |
| 50 | አቶ ፋፋ ያደሳ | ወንድ | 84 | አቶ ሶሬሳ ዳሜ | ወንድ |
| 51 | አቶ ጉታ ባይሳ | ወንድ | 85 | አቶ ግርማ ባይሳ | ወንድ |
| 52 | አቶ ገመቹ ከበደ | ወንድ | 86 | አቶ ግርማ ሀይሌ | ወንድ |
| 53 | አቶ እንሳርሙ ቦጋለ | ወንድ | 87 | አቶ አበራ መኮንን | ወንድ |
| 54 | አቶ ደበላ ፈይሳ | ወንድ | 88 | አቶ ባይሳ ኞሪሳ | ወንድ |
| 55 | አቶ አህመድ መሀመድ | ወንድ | 89 | አቶ ገመቹ ቴሶ | ወንድ |
| 56 | አቶ ብርሃኑ በዳዳ | ወንድ | 90 | አቶ አዱኛ ተሾመ | ወንድ |
| 57 | አቶ እጅጉ ቃበታ | ወንድ | 91 | አቶ ሁንዴ ፍቃዱ | ወንድ |
| 58 | አቶ ጉዲና ተስፋዬ | ወንድ | 92 | አቶ አንዷለም ታደለ | ወንድ |
| 59 | አቶ ተስፋዬ መኮንን | ወንድ | 93 | አቶ አብዲሳ ፋፋ | ወንድ |
| 60 | አቶ ታሬሳ አስናቀ | ወንድ | 94 | አቶ ጌሲሳ ዳባ | ወንድ |
| 61 | አቶ ሙሉጌታ ዳዲ | ወንድ | 95 | አቶ ጀማል አህመድ | ወንድ |
| 62 | አቶ አለሙ ኦላኒ | ወንድ | 96 | አቶ ገመቹ ብርሃኑ | ወንድ |
| 63 | አቶ ቤተ ለሚ | ወንድ | 97 | አቶ መጫ ጅራታ | ወንድ |
| 64 | አቶ ዳንኤል አብዲሳ | ወንድ | 98 | አቶ ኢፋ ዓለማየሁ | ወንድ |
| 65 | አቶ ተስፋ ጌቱ | ወንድ | 99 | አቶ ወርቁ ጉዲሳ | ወንድ |
| 66 | አቶ እሸቱ ደጀኔ | ወንድ | 100 | አቶ ኡመር ጣህር | ወንድ |
| 67 | አቶ ብሉስማ አብርሃም | ወንድ | 101 | አቶ ዋሬ ሎሎ | ወንድ |
| 68 | አቶ መርሻ ባይሳ | ወንድ | 102 | አቶ ደረጀ ታደሰ | ወንድ |

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

## ሰንጠረዥ 5፡ በእስር ላይ የሚገኙ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) አባላት ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | የታሳሪው ሙሉ ስም | ጾታ | የታሰረበት ቦታ | በእስር ላይ የሚገኙበት ቦታ | በፓርቲው ውስጥ ያላቸው ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሻምበል ንጉሴ ደርሶ | ወ | ጎንደር | ማእከላዊ | የሰሜን ጎንደር ሰብሳቢ. |
| 2 | አቶ ስመኘው ገሰሰ | ወ | ምስራቅጎጃም | ባህርዳር | የይልማና ዴነሳ ወረዳ ሰብሳቢ. |
| 3 | መምህር ባዩ ደሴ | ወ | ምስራቅ ጎጃም | ቂሊንጦ | አባል |
| 4 | አቶ ሰመሽ | ወ | ምስራቅ ጎጃም | ቂሊንጦ | አባል |
| 5 | አቶ መሳይ | ወ | ሰሜን ወሎ | ወልዲያ (የእድሜ ልክ እስረኛ) | በመቂት ወረዳ ዋና ጸሀፊ |
| 6 | አቶ ጎዳኝ ፈጠነ | ወ | ምስራቅ ጎጃም (ደምበጫ) | በአልታወቀ ስፍራ | አባል |
| 7 | አቶ መንግስቴ | ወ | ምስራቅ ጎጃም (አማኑኤል) | ደብረ ማርቆስ | አባል |
| 8 | አቶ በላቸው አወቀ | ወ | አዊ ዞን | ባህር ዳር | በአዊ ዞን ሰብሳቢ. |
| 9 | አቶ ደግአርጌ አይናአለም | ወ | ምስራቅ ጎጃም | ማዕከላዊ | አባል |
| 10 | አቶ ጌታቸው አዱኛ | ወ | ደቡብ ጎንደር (ደብረ ታቦር) | ማዕከላዊ | አባል |
| 11 | አቶ ክብር አለምአየሁ | ወ | ደቡብ ጎንደር (ደብረታቦር) | ማዕከላዊ | አባል |

## ሰንጠረዥ 6፡ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተከትሎ ታስረው የተፈቱ የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ስም ዝርዝር

| ተቁ | የታሳሪው ስም | የታሰረበት ቀን | የተፈታበት ቀን | የታሰረበት ምክንያት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዋለልኝ ማሬ አሰፋ | 29/3/09 | 14/7/09 | ህዳር 29 የሚከበረውን የብሄረሰቦች በዓል በዩንቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ይከበር አይከበር በሚል በተፈጠረ አለመግባባት |
| 2 | ካሳሁን ዳኘው | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |
| 3 | አድኖ አበበ | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |
| 4 | ስለአባት ታዘበው | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |
| 5 | ወንድም መንገሻ | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |
| 6 | ዳንኤል ዋሴ | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |
| 7 | ሳሙኤል ገብረ ማርያም | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |
| 8 | ሞቲ ዴብሳ | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |
| 9 | መብራቱ ወርቁ | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |
| 10 | ብርሃኑ ብርሃኔ | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |
| 11 | ኪዳነ ማርያም ጥንፌ | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |
| 12 | ጀጀው አዳነ | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |
| 13 | መልካሙ እንግዳየሁ | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |
| 14 | ቴዎድሮስ ምህረት | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |
| 15 | ተካልኝ መኩ | 29/3/09 | 14/7/09 | << << |

## ሰንጠረዥ 7፡ ታስረው የተፈቱ የጅማ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች

| ተ.ቁ. | የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የተፈጸመበት ሰው | የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የተፈጸመበት ቦታ | የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የተፈጸመበት ጊዜ | የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ዓይነት | አጭር ማብራሪያና ጉዳዩ አሁን ያለበት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቤኩማ ተስፋዬ ኡመታ | ጅማ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ | ከ10/03/09 - 30/07/09 | ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ይዞ ማሰርና ማቆየት | ግለሰቦቹ የጅማ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሲሆኑ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ታስረው በፖሊስ ጣቢያ ሲሰቃዩ ቆይተው በመጋቢት 30 2009 ከእስር ተፈተዋል |
| 2 | ሁሴን አ/ከድር በንቲ | ጅማ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ | 14/03/09 - 30/07/09 | ›› ›› | |
| 3 | ገደፋ መንገሻ በያን | ጅማ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ | ከ10/05/09 - 30/07/09 | ›› ›› | |

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ

## ሰንጠረዥ 8፡ በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም በመምህራን ደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ ምክንያት ታስረው የተፈቱ

| ተ.ቁ | የታሳሪው ስም | የታሰረበት ቀን | የታሰረበት ምክንያት | የተፈታበት ቀን | ተቁ | የታሳሪው ስም | የታሰረበት ቀን | የታሰረበት ምክንያት | የተፈታበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መ/ር ሐብታሙ አስራት | 27/6/09 | መንግስት ለሰራተኞች ባደረገው የደመወዝ እርከን ማስተካከያ መምህራንን ያላካተተ በመሆኑ የስራ ማቆም አድማ ላይ ተዋናይ ነበራችሁ በሚል የታሰሩ | 13/7/09 | 16 | ጎጃም | 27/6/09 | መንግስት ለሰራተኞች ባደረገው የደመወዝ እርከን ማስተካከያ መምህራንን ያላካተተ በመሆኑ የስራ ማቆም አድማ ላይ ተዋናይ ነበራችሁ በሚል የታሰሩ | 13/7/09 |
| 2 | መ/ር ማስተዋል ሻረ | 27/6/09 | | 13/7/09 | 17 | አስማረ | 27/6/09 | | 13/7/09 |
| 3 | መ/ር አየለ የኔ አካል | 27/6/09 | | 13/7/09 | 18 | ጌታቸው አድማሱ | 27/6/09 | | 13/7/09 |
| 4 | መ/ር ዳዊት ግዳሙ | 27/6/09 | | 13/7/09 | 19 | ሙላት | 27/6/09 | | 13/7/09 |
| 5 | ገደፋው አያሌው | 27/6/09 | | 13/7/09 | 20 | ተመስገን | 27/6/09 | | 13/7/09 |
| 6 | እንደሳ አቤ | 27/6/09 | | 13/7/09 | 21 | ሹምየ አያሌው | 27/6/09 | | 13/7/09 |
| 7 | ተሸለ ወንዳለ | 27/6/09 | | 13/7/09 | 22 | ጌታቸው አለልኝ | 27/6/09 | | 13/7/09 |
| 8 | መሰረት ፀጋ | 27/6/09 | | 13/7/09 | 23 | ደባልቄ | 27/6/09 | | 13/7/09 |
| 9 | አለሙ | 27/6/09 | | 13/7/09 | 24 | ዋለ ጅንን | 27/6/09 | | 13/7/09 |
| 10 | አዳነ ታደለ | 27/6/09 | | 13/7/09 | 25 | አብዮት | 27/6/09 | | 13/7/09 |
| 11 | ታደሰ አያሌው | 27/6/09 | | 13/7/09 | 26 | ወንድ ወሰን ደምሌ | 27/6/09 | | 13/7/09 |
| 12 | ጥሩ ሰው ከተማ | 27/6/09 | | 13/7/09 | 27 | አህመድ ኑር | 27/6/09 | | 13/7/09 |
| 13 | ተሸመ ጥላሁን | 27/6/09 | | 13/7/09 | 28 | ማኪያስ ካሳ | 27/6/09 | | 13/7/09 |
| 14 | እንዳሻው አቤ | 27/6/09 | | 13/7/09 | 29 | ሲሳይ አስፋው | 27/6/09 | | 13/7/09 |
| 15 | ተሸለ ወንዳለ | 27/6/09 | | 13/7/09 | 30 | በእምነት በለጠ | 27/6/09 | | 13/7/09 |

## ሰንጠረዥ 9፡ በጀልዱ ከተማ ታስረው የተፈቱ እና ከምዕራብ ወለጋ ታስረው በማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ የሚገኙ ታሳሪዎች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ. | የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የተፈጸመበት ሠው | የታሰረበትና የተፈታበት ቀን | የታሰረበት ቦታ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ በቀለ አጀማ ገመቹ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | በጀልዱ ፖሊስ ጣቢያ ለሰባት ወራት ክስ ሳይመሰረትባቸው የቆዩ ሲሆን፣ ግንቦት 1 ቀን 2009 ዓ.ም. ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቀርበው በዋስ ተፈተዋል |
| 2 | አቶ ኡልፋታ እሬንሶ ደሜ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 3 | አቶ ጉተማ በቀለ አያኔ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም.ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 4 | አቶ ከቤ ገመዳ ደበሌ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም.- ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 5 | አቶ ድሪባ እቤሳ ቢቂላ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም.- ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 6 | አቶ ረጋሳ ጫላ ቢቂላ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም.- ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 7 | አቶ ጫላ ኡርጌሳ ደበሊ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም.- ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 8 | አቶ ፍቃዱ ለማ አያኒ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም.- ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 9 | አቶ በቀለ አጀማ መገርሳ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም.- ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 10 | አቶ ከተማ ጎንፋ ኮርሳ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም.- ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 11 | አቶ ብሩ በየሳ በንቲ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም.- ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 12 | አቶ ግርማ ጣፋ ደቻሳ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም.- ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 13 | አቶ ታሪኩ ረጋሳ ደሜ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም.- ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 14 | አቶ ደረጄ ነጋሳ ቆሪቻ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም.- ሚያዚያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 15 | አቶ ሽብሩ ጣባ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም. ሚያዝያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 16 | አቶ ዝና ዳኜ ደበሊ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም ሚያዝያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |

| ተ.ቁ. | የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የተፈጸመበት ሠው | የታሰረበትና የተፈታበት ቀን | የታሰረበት ቦታ |
|---|---|---|---|
| 17 | አቶ ጉተማ በቀለ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም.ሚያዝያ 30/ 2009 ዓ.ም. | በጀልዱ ፖሊስ ጣቢያ ለሰባት ወራት ክስ ሳይመሰረትባቸው የቆዩ ሲሆን፣ ግንቦት 1 ቀን 2009 ዓ.ም. ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቀርበው በዋስ ተፈተዋል |
| 18 | አቶ ፈይሳ በየነ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም ሚያዝያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 19 | አቶ ቶሎሳ ኢማና | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም ሚያዝያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 20 | አቶ አዱኛ (ሁንዴ)ወርዶፋ | ከጥቅምት 3/2009 ዓ.ም ሚያዝያ 30/ 2009 ዓ.ም. | |
| 21 | አቶ ኤቢሳ ራቲሳ | ከየካቲት 2/2009 ጀምሮ | ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ በእስር ላይ ይገኛል |
| 22 | አቶ ጉታ ራጋ | ከጥቅምት 23/ 2009 ጀምሮ | ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ በእስር ላይ ይገኛል |
| 23 | አቶ ሱሌይማን ከድር | ከጥቅምት 23/ 2009 ጀምሮ | ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ በእስር ላይ ይገኛል |
| 24 | ተማሪ ዱላ ደንገታ | ከጥቅምት 21/ 2009 ጀምሮ | ቄለም ወለጋ ሰዮ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ በእስር ላይ ይገኛል |

## ሠንጠረዥ 10፡ በአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የታሰሩና የደረሱበት የማይታወቅ ሰዎች ሥም ዝርዝር

| ተ.ቁ. | የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የተፈጸመበት ሰው | የታሰሩበት ቦታ | የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቱ የተፈጸመበት ጊዜ | አጭር ማብራሪያና ጉዳዩ አሁን ያለበት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ሰለሞን ፈይሳ | ቀበሌ 20 | በጥቅምት /2009 | በታህሳስ ወር 2009 ዓ.ም. የተፈታ |
| 2 | አቶ ነጻነት ሽፈራው | ቀበሌ 20 | በጥቅምት /2009 | በታህሳስ ወር 2009 ዓ.ም. የተፈታ |
| 3 | ቅድዕም ይቻላል ዋጋው | ቀበሌ 20 (ከስራ ቦታው) | በጥቅምት /2009 | በጐንደር ማረሚያ ቤት ታስሯል |
| 4 | አቶ አባቡ ሠ/አረጋው | ቀበሌ 20 (ከስራ ቦታው) | በጥቅምት /2009 | በጐንደር ማረሚያ ቤት ታስሯል |
| 5 | አቶ መላክ ቀላቴ | ቀበሌ 19 | በጥቅምት /2009 | የደረሱበት የማይታወቅ |
| 6 | መቶ አለቃ ሙላት ቦጋለ | ቀበሌ 20 | በጥቅምት /2009 | የደረሱበት የማይታወቅ |
| 7 | አቶ ካሳሁን ሙጩ | አይራ ጓራ | 17/4/2009 | በመጀመሪያ 5ኛ ፖሊስ ጣቢያ አሁን ጎንደር ማረሚያ ቤት ታስረው ይገኛሉ |
| 8 | አቶ ይላቅ ይግዛው | አይራ ጓራ | 17/4/2009 | በመጀመሪያ 5ኛ ፖሊስ ጣቢያ አሁን ጎንደር ማረሚያ ቤት ታስረው ይገኛሉ |
| 9 | አቶ ተቀባ ጫኔ | ብርሸለቆ እስር ቤት | በህዳር ወር/2009 ዓ.ም. | ከብርሸለቆ እስር ቤት ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተወስደው የታሰሩ |
| 10 | አባ አይናአለም አይጠገብ | አይራ ጓራ | 30/04/09 | 5ኛ ፖሊስ ጣቢያ ከ3 ልጆቻቸው ጋር ታስረው የተፈቱ |
| 11 | አቶ ይርጋ አለሙ | ቀበሌ 19 | 27/05/09 | ወደ ጦር ሰፈር ከተወሰዱ በኋላ ይህ ምርመራ በተካሄደበት ጊዜ 6ኛ ፖሊስ ጣቢያ ያሉ |
| 12 | አቶ ታደለ ቢያድግልኝ | ቀበሌ 20 | 27/5/09 | ወደ ጦር ሰፈር ተወስደው የታሰሩ |
| 13 | አልታሰብ (ማርከሻው) መክብብ | ደብረታቦር | 12/5/09 | መረጃው አልተገኘም |
| 14 | እያያ ይታየው | ደብረታቦር | 13/05/09 | >> >> |
| 15 | ጌታቸው ሞላ | ደብረታቦር | 13/05/09 | >> >> |
| 16 | እያሱ አዲስ | ደብረታቦር | 12/5/09 | >> >> |
| 17 | ታደሰ አስርደው | ደብረታቦር | 12/5/09 | >> >> |
| 18 | አቶ ጌቴ ጌትነት | ብርሸለቆ ወታደራዊ ካምፕ | 14/03/09 | በእርሳቸውና በባለቤታቸው ላይ ድብደባ የተፈጸመባቸው ሲሆን አቶ ጌቴ በ25/5/2009 ዓ.ም. ከእስር ተፈተዋል፡፡ |
| 19 | አቶ ወንዳለህ ያየህይራድ | ከታህሳስ 5 / 2009 እስከ ጥር 26/2009 | | በብር ሸለቆ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ታስሮ ቆይቷል |
| 20 | አቶ አቻምየለህ ዘውዴ | ከታህሳስ 1/ 2009 ጀምሮ | | በፍኖተሠላም ማረሚያ ቤት ታስሮ ይገኛል |

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

ሠንጠረዥ 11፡ የሠንጠረዦች ማጠቃለያ

| የሠንጠረዥ ቁጥር | መግለጫ | የታሳሪዎች ድምር |
|---|---|---|
| 1 | 1ኛ እና 2ኛ ዙር | 22193 |
| 2 | ምዕራብ አርሲ | 94 |
| 3 | ሰማያዊ ፓርቲ | 15 |
| 4 | አፈኮ | 102 |
| 5 | መኢአድ | 11 |
| 6 | ደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ | 15 |
| 7 | ጅማ ዩኒቨርሲቲ | 3 |
| 8 | ምሥ.ና ምዕ. ጎጃም መምሕራን ደሞዝ ጭማሪ | 30 |
| 9 | ጀልዱ | 24 |
| 10 | አማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች | 20 |
| ጠቅላላ ድምር | | 22,507 |

## የሰመጉ መርማሪዎች የካቲት 5 እና 6 ቀን 2009 ዓ.ም. በጥቂት ማረሚያ ቤቶች ባደረጉት ጉብኝት የተመለከቷቸው ሁኔታዎች

### ሀ. የደብረታቦር ማረሚያ ቤት፡

1. እጅግ ከፍተኛ የውሃ አቅርቦት ችግር በመኖሩ ለመጠጥም ሆነ ለመታጠቢያ ውኃ ማግኘት እንደማይችሉ፣ በሳምንት አንድ ቀን ብቻ የተወሰነ ውሃ እንደሚሰጣቸውና ቤተሰብ ያላቸው እስረኞች ቤተሰቦቻቸው በየቀኑ ውሃ እያመላለሱ እንደሚጠቀሙ፣ በዚህም የተነሳ በንጽህና ችግር ምክንያት ለሚከሰቱ ውሃ ወለድ ተላላፊ በሽታዎች እንደተጋለጡ ሰመጉ ካሰባሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፣
2. በአንድ ክፍል ማለትም 10x4 በሆነ ክፍል ውስጥ ከ 80-100 የሚደርሱ እስረኞች የሚተኙ ሲሆን ከፍተኛ መተፋፈግና መጨናነቅ እንዳለ የሰመጉ መርማሪዎች ካደረጉት የእስር ቤት ጉብኝት አረጋግጠዋል፣
3. አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀ ወዲህ በማረሚያ ቤቱ ውስጥ የታሰሩ እስረኞች ምንም ክስ ሳይቀርብባቸውና ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ማረሚያ ቤቱ በአደራ እንዲያቆያቸው በሚል በኮማንድ ፖስት የቃል ትእዛዝ ብቻ ያሉ መሆኑን የተለያዩ መጠይቆች በማቅረብ ለመረዳት ተችሏል፡፡

### ለ. የፍኖተሰላም ማረሚያ ቤት፡

የሰመጉ መርማሪዎች በፍኖተ ሰላም ማረሚያ ቤት የሚገኙ እስረኞችን ባነጋገሩበት ወቅት እንደተረዱት ህዝባዊ እንቅስቃሴው ከተጀመረ ወዲህ እና አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከታወጀ በኋላ ከ250 በላይ ወጣቶች በማረሚያ ቤቱ ይገኙ ነበር፡፡ ሁሉም እስረኞች ምንም አይነት ክስ ያልተመሠረተባቸውና ፍርድ ቤት ያልቀረቡ መሆኑን ለሰመጉ የገለጹ ሲሆን የማረሚያ ቤቱን አያያዝ በሚመለከለት እንደሚከተለው ለሰመጉ ባለሙያዎች አስረድተዋል፡፡

1. **ህክምና በሚመለከት፡-** በማረሚያ ቤቱ ውስጥ እስረኞች በሚታመሙበት ጊዜ ከሰኞ እስከ አርብ ብቻ የህክምና አገልግሎት የሚያገኙ ሲሆን ቅዳሜና እሁድ ማረሚያ ቤቱ ውስጥ ያለው የህክምና መስጫ ተቋም መዘጋቱ፤ ቅዳሜና እሁድ ድንገተኛ ህመም ቢያጋጥማቸው ህክምና አለማግኘታቸና እና ከማረሚያ ቤቱ ውጭ ወዳሉ የጤና ተቋማትም እንደማይወሰዱ ሰመጉ ያነጋገራቸው እስረኞች ገልጸዋል፣
2. በተጨማሪ በጣም አሰቃቂው ነገር በማረሚያ ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የአሳማ መንከሪያ የሚባል ማሰቀያ ቦታ መኖሩን እስረኞች ገልጸዋል፡፡ ቦታው የማረሚያ ቤቱ ሽንት ማጠራቀሚያ ጉድጓድ

ሲሆን አንዳንድ እስረኞችን እየወሰዱ ሽንት ውስጥ እየዘፈዘፉ እንደሚያሰቃዩ እና እንደሚደበድቡ ከእስረኞች መካከል የሰመጉ መርማሪዎች ያነጋገሯቸው ገልጸዋል።

3. ታሳሪዎች የታሰሩባቸው ቦታዎችና አካባቢዎች ንፅህናው የተሟላ የመጠጥና የመታጠቢያ ውሀ፣ የመፀዳጃ ቦታ የሌላቸው እንዲሁም ታሳሪዎችንም መጠየቅ እንደማይቻል ታስረው የተለቀቁ ሰዎች ለሰመጉ ገልፀዋል። ታሳሪዎቹ በእስር ላይ በቆዩበት ወቅትም "አይደገምም፣ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንዳንድ ጉዳዮች፣ የመጪው ዘመን የኢትዮጵያ የህዳሴ ጉዞ፣ በሀገር ግንባታ ላይ የወጣቱ ሚና፣ የቀለም አብዮትና ዲሞክራሲያዊ ፌዴራሊዝም" በሚሉ ጉዳዮች ላይ ስልጠና ተሰጥቷቸው እንደተለቀቁ ለሰመጉ አስረድተዋል።

## የእስረኞች አያያዝ ሁኔታን የሚመለከት ማጠቃለያ

በዚህ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ውስጥ ሰመጉ ክትትልና ምርመራ ያካሄደባቸው የእስረኛ ማቆያ ቦታዎች ሁኔታና የእስረኛ አያያዛቸውን በሚመለከት የሚከተሉት ዓበይት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችና ችግሮች መታየታቸውን የምርመራ ውጤቱ ያመለክታል። በአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጊዎችና መመሪያዎች የእስረኛ ማቆያ ቦታዎች በቂ ምግብ፣ ሕክምና እና መኝታ እንዲሁም የመጸዳጃ አገልግሎቶች እንዲኖሯቸው፣ ታሳሪዎች ሰብዓዊ ክብራቸው እንዲጠበቅ እና በቤተሰቦቻቸው፣ በሐይማኖት አባቶቻቸው እና በጠበቆቻቸው እንዲጎበኙ የሚደነግጉ ሲሆን፣ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት የነበረው የታሳሪዎች አያያዝ ግን እነዚህን ድንጋጌዎች የማያሟላ ወይም የጣሰ እንደነበር ሰመጉ ያካሔደው ምርመራ ውጤት ያመለክታል። ስለሆነም፣

- ጥቂት በማይባሉት የእስረኛ ማቆያ ቦታዎች፣በተለይም በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ኢሰብዓዊ አያያዝና ድብደባ ይፈጸም እንደነበር ታሳሪዎች ገልጸዋል። ለምሳሌ በጦላይ ማሰልጠኛ ጣቢያ ባዶ እግር ግርፋት፣ እጅን በጆሮ አስይዞ ማኮብኮብና ምግብ መከልከል እንደነበር አመልክተዋል። በጣቢያው እስረኞች እግራቸው ወደላይ ተሰቅሎ ወይም መሬት ላይ በደረታቸው ተኝተው እየተደበደቡ የስቃይ ምርመራ ይደረግባቸው እንደነበር ለሰመጉ ምስክርነት የሰጡ ታሳሪዎች ገልጸዋል። በተመሳሳይም በአዋሽ አርባ የእስረኞች ማቆያ ጣቢያ ታሳሪዎች ጫማቸውን እንዲያወልቁ ተደርጎ 3 ቀን ሙሉ እስረኞችን በባዶ እግር ጸሐይ ላይ እንዲቀመጡ ይደረግ እንደነበር ተጎጂዎች ለሰመጉ አስረድተዋል። በተመሳሳይ ሁኔታም፣ በተለይ በአዲስ አበባ፣ በጦላይና አዋሽ አርባ አካባቢ ታሳሪዎችን በሚያዋርድ እና ሰብዓዊነት በጎደለው ሁኔታ በመፀዳጃ ሰዓትም 114 ሰው አንድ ላይ ወጥቶ ሜዳ ላይ ወይም በአንድ ጉድጓድ እንዲጸዳዱ ተገድደዋል።
- ታሳሪዎች ቤተሰብና ወዳጅ ዘመድ ሊጠይቋቸውና ስንቅ ሊያቀብሏቸው በማይችሉበት በጣም ሩቅ በሆኑ አካባቢዎች በመገኘታቸው የታሳሪዎችን አያያዝ ለመከታተል እና የቤተሰብ ዕርዳታም ለማግኘት አስቸጋሪ አድርጎታል፣ ይህም የታሳሪዎችን ህገመንግስታዊ መብት ከመገደቡም በላይ በጸጥታ ኃይሎች በጣቢያዎቹ የሚፈጸሙ የመብት ጥሰቶች ሳይታወቁ ተዳፍነው እንዲቀሩ ጭምር አድርጓል።
- አብዛኞቹ የእስረኛ ማቆያ ቦታዎች በሁኔታዎች አስገዳጅነት እንጂ ለእስረኛ ማቆያ ተብሎ የተቋቋሙ ባለመሆናቸው በቂ ሥፍራ፣ ተገቢው አደረጃጀትና የአገልግሎት አቅርቦት የሌላቸውና እስረኞች ከመጠን በላይ የተጨናነቁባቸው መሆናቸው፣ መያዝ ከሚችሉት የሰው ብዛት ከ 5 እስከ 10 እጥፍ እስረኛ የያዙ ይገኙባቸዋል፤ ለምሳሌ በጦላይ የእስረኞች ማቆያ በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ 115 ሴት እስረኞች እንዲታሰሩ መደረጉን ለሰመጉ ምስክርነታቸውን የሰጡ ታሳሪዎች ገልጸዋል። አዋሽ አርባ የእስረኞች ማቆያ ውስጥም በአንድ መኝታ ክፍል 114 ታሳሪዎች እንደሚኖሩ፣ ከመኝታ ክፍል ውስጥ መውጣት እንደማይቻል፤ የጥሰቱ ሰለባዎች ለሰመጉ አስረድተዋል። በተለይ በነዚህ ማቆያዎች በአካባቢው በነበረው ከፍተኛ ሙቀት ምክንያት ታሳሪዎች ይሰቃዩ እና አንዳንዶችም ራሳቸውን እየሳቱ ይወድቁ እንደነበር ተገልጿል።
- ጥቂት በማይባሉት የእስረኛ ማቆያ ቦታዎች በቂ የምግብ አቅርቦት አለመኖሩ፣ ጽዳት የጎደላቸውና ለጤና ጎጂ መሆናቸውን የምርመራው ውጤት የሚያሳይ ሲሆን፣ በበርካታዎቹ ቦታዎች (ለምሳሌ አዋሽ አርባ፣ ጦላይ ወዘተ) ታሳሪዎች በቀን አንድ ወይም ሁለት ዳቦ ብቻ እያገኙ በረሐብ እንዲንገላቱ ተደርጓል፡

➢ በርካታዎቹ የእስረኛ ማቆያዎች፣ ለዚሁ ተብለው የተሰሩ ሳይሆኑ ቀድሞ መደበኛ ት/ቤቶችና ኮሌጆች እንዲሁም ሌሎች የሕብረተሰብ አገልግሎት መስጫዎች በመሆናቸው መደበኛ አገልግሎታቸውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል አቋርጠዋል፡፡

## የታሳሪዎች የምስክርነት ቃል

ከተሞችን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት ከታሰሩት ዜጎች ውስጥ ጥቂቱ እንዲሁም ቤተሰቦቻቸው ለሰመጉ የሰጡት አቤቱታና ምስክርነት ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡ እነዚህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሰለባዎች ያሰሙት አቤቱታና ምስክሮችም የሰጡት የእማኝነት ቃል በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት በበርካታ እስር ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎችና የማቆያ ቦታዎች ውስጥ ያለው የእስር ቤቶች ሁኔታና የእስረኞች አያያዝ በጣም አሳሳቢና አፋጣኝ ማስተካከያም ሊደረግበት እንደሚገባ ያመለክታል፡፡

1. **አቶ መኮንን ኪቲላ** የሰመጉ አባል ሲሆኑ በነቀምት ከተማ ቀበሌ 03 ነዋሪ ናቸው፡፡ አቶ መኮንን ኪቲላ የ48 ዓመት ጎልማሳ እና በግል ስራ የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ ሕዝባዊ ተቃውሞ እንዲነሳ ትቀሰቅሳለህ በሚል ምክንያት ከመጋቢት 8/2008 ዓ.ም. እስከ መጋቢት 13/2008 ዓ.ም. ነቀምቴ ወረዳ 2 ቀበሌ 07 በሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ታስረዋል፡፡ ከመጋቢት 13/2008 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 1/2008 ዓ.ም. ደግሞ በጦላይ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ታስረው ተፈተዋል፡፡ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከታወጀ በኋላ "በነቀምት ከተማ ሰልፍ በድጋሚ አንዲነሳ እየቀሰቀስክ ነው" በሚል ዛቻ እና ማስፈራሪያ እየተፈፀመባቸው በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት በነፃነት መውጣትና መግባት ባለመቻላቸው ህይወታቸውን በስጋት ለመምራት እንደተገደዱ በመግለፅ ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡
2. **አቶ ጫላ ሶፊያን ኡመር** ፡ እድሜያቸው 30 ባለትዳርና በቀን ስራ የሚተዳደሩ ሲሆኑ ነዋሪነታቸው ምስራቅ ሀረርጌ በደደር ከተማ ቀበሌ 02 ነው፡፡ በጥቅምት 13 2009 ዓ.ም ከንጋቱ 12 ሰዓት አካባቢ ፖሊሶችና ታጣቂዎች ወደ መኖሪያ ቤታቸው በመምጣት ትፈለጋለህ ብለው እንደወሰዷቸውና በደደር መዋዕለ ህፃናት ት/ቤት 72 ከሚጠጉ ሌሎች ከተያዙ እስረኞች ጋር እንደቀላቀሉዋቸው ገልጸዋል፡፡ በጥቅምት 25 2009 ዓ.ም ወደ ኮምቦልቻ እርሻ ልማት እንደተወሰዱና በዚያም የርሳቸውንና የሌሎች የተያዙት ሰዎችን መታወቂያ ተቀብለው እንዳቃጠሉት፣ ድብደባም እንደተፈፀመባቸው፣ ባለቤታቸውም በሚደርስባቸው ዛቻ ምክንያት ከቤት ወጥተው የት እንደደረሱ እንደማያውቁ ለሰመጉ ጨምረው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡
3. **አቶ ስንታየሁ አንበሴ ማሙዮ** እድሜው 23፣ ነዋሪነቱ ምስራቅ ሀረርጌ በደደር ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ ሲሆን የታሰረ ጓደኛውን ለመጠየቅ በሄደበት ድንጋይ ስትወረውር ነበር በማለት ፖሊሶችና ታጣቂዎች ይዘውት ደደር ፖሊስ ጣቢያ እንዳስገቡትና ከዚያም ለወጣቶች መዝናኛ ስፍራ ተብሎ ወደተሰራው ቦታ ወስደው እንዳሰሩት፣ በዚያም "72 የሚሆኑ ሰዎች ታስረዋል፣ ከነዚህም ውስጥ 10 የሚሆኑት ሴቶች እንደነበሩ አይቻለሁ፣ በመጨረሻም በታህሣሥ 15 2009 ዓ.ም በጣቢያ ዋስ ተለቅቄያለሁ" በማለት ለሰመጉ አስረድቷል፡፡
4. **አቶ ናስር ጀማል** ዕድሜው 25፣ በንግድ ስራ የሚተዳደር፣ ነዋሪነቱ ምዕራብ ሀረርጌ በጭሮ ወረዳ ቀበሌ 01 ውስጥ ሲሆን በጥቅምት 16 2009 ዓ.ም ከጠዋቱ 4 ሰዓት አካባቢ የምሰራበት ሱቅ ድረስ ፖሊሶች በመምጣት "ሰላማዊ ሰልፍ ነው እያልክ የአካባቢው ሰው ተረጋግቶ እንዳይኖርና እንዳይሰራ ለዓመፅና ለብጥብጥ እያነሳሳህ ነው በማለት እየደበደቡ ወደ ጭሮ 1ኛ ፖሊስ ጣቢያ ወስደው ለዘጠኝ ቀናት እንዳሰሩትና ከዚያም "በጥቅምት 24 2009 ዓ.ም ከአካባቢውና ከተለያዩ ወረዳዎች ከተያዙ በርካታ ወጣቶች ጋር ወደ ጦላይ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ማዕከል ተወስደን ታስረናል፣ በመጨረሻም የተለያዩ ስልጠናዎችን ከሰጡን በኋላ በታህሣሥ 24 2009 ዓ.ም ተለቅቄያለሁ፤ በዚሁ ሁሉ የእስራት ወቅት ስራ ፈትቼ በመቀመጤ ለተለያዩ ጉዳቶች ተዳርጌያለሁ" በማለት ለሰመጉ አመልክቷል፡፡
5. **አቶ መሀዴ አሜ ኢብሮ** ነዋሪነታቸው በሀሮማያ ከተማ እድሜያቸው 50 ባለትዳርና የ12 ልጆች አባት ናቸው፡፡ በጥቅምት 05 2009 ዓ.ም ከጠዋቱ 4 ሰዓት አካባቢ የከተማው ፖሊሶችና ታጣቂዎች የኦኤምኤን (ኦሮሞ ሚዲያ ኔትዎርክ) አይተሀል በማለት ሀሮማያ ፖሊስ ጣቢያ አንድ ወር ከአስራ ሰባት ቀን ካሰሩኝ



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ

በኋላ ወደ አደሌ የጦር ካምፕ ወሰዱኝ ከጥቂትም ቀናት በኋላም 660 ከሚጠጉ ከተለያዩ አካባቢዎች ከመጡ ታሳሪዎች ጋር ወደ ጦላይ እንደተወሰዱና በመጨረሻም በጥቅምት 24 2009 ዓ.ም እንደተለቀቁ፣ በተጨማሪም ባለቤታቸው በፖሊሶች እንደተደበደቡና ልጃቸውም በወቅቱ ቤተሰቡ ላይ በደረሰው አስቸጋሪና አስደንጋጭ ሁኔታ በመደናገጥ እስካሁን የደረሰበት እንደማይታወቅ በመግለፅ ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡

6. አቶ መሀመድ አልይ ዩሱፍ ነዋሪነቱ በምዕራብ ሐረርጌ በአሰቦት ከተማ ሲሆን እድሜ 32፣ ባለትዳርና በሙያ መምህር ነው፡፡ በጥቅምት 18 2009 ዓ.ም በግምት ማምሻው 12:30 ላይ የአካባቢው ሚሊሻዎች መኖሪያ ቤቱ ድረስ በመምጣት "አካባቢው በዓመፅና በሁከት እንዲሸበር ወጣቶችን እያደራጀህ እንዲያምፁ የምታደርገው አንተ ነህ" በማለት እየደበደቡ ወስደው አሰቦት ፖሊስ ጣቢያ ለ5 ቀናት እንደታሰረ፣ ጥቅምት 24 2009 ዓ.ም ወደ ጦላይ የጦር ካምፕ ከምሥራቅና ምዕራብ ሐረርጌ ከመጡ 60 ከሚሆኑ ታሳሪዎች ጋር እንደተወሰደና በመጨረሻም ተሀድሶ ወስደሀል በማለት በታህሣሥ 24 2009 ዓ.ም እንደተለቀቀና በእስር በቆየበት ወቅት ቤተሰቦቹ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ወድቀው እንደነበር በመግለፅ ለሰመጉ አመልክቷል፡፡

7. ወጣት ሀሩን መሀመድ ሳሊ እድሜው 18፣ ነዋሪነቱ ሀረማያ ከተማ ሲሆን በቀን ሥራ ገቢ የሚተዳደር ወጣት ነው፡፡ በጥቅምት 13 2009 ዓ.ም ከቀኑ 10 ሰዓት ላይ የከተማው ፖሊሶችና ታጣቂዎች ከመኖሪያ ቤቱ እየደበደቡ ወደ ሀሮማያ ፖሊስ ጣቢያ እንደወሰዱትና በዚያም ለ1 ወር ከ15 ቀን ከታሰረ በኋላ ከሌሎች አካባቢዎች ተይዘው ከመጡ ታሳሪዎች ጋር ወደ ጦላይ የጦር ማሰልጠኛ ተወስዶ እንደታሰረ፣ በመጨረሻም በታህሣሥ 24 2009 ዓ.ም እንደተለቀቀ በመግለፅ ለሰመጉ አመልክቷል፡፡

8. አቶ ኢብራሂም ኡመር ሀሰን እድሜ 46፣ በንግድ ስራ የሚተዳደሩ የሐሮማያ ከተማ ነዋሪ ባለትዳርና የ8 ልጆች አባት ናቸው፡፡ አቶ ኢብራሒም ለሰመጉ ባቀረቡት አቤቱታ፡ "በሐሮማያ ከተማ ውስጥ የሚነሱትን ተቃውሞዎች ቀስቃሽ ነህ እየተባልኩ በተለያዩ ጊዜያት ስታሰር ስፈታ ቆይቻለሁ፤ በኋላም በጥቅምት 13 2009 ዓ.ም ከቀኑ 10 ሰዓት ላይ የከተማው ከንቲባና ታጣቂ ፖሊሶች የመኖሪያ ቤቴን በር በመገንጠል እየደበደቡኝ ወደ ሐሮማያ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱኝ፣ ከዚያም በነጋታው ወደ አደሬ ካምፕ ወስደውኝ ከሌሎች 60 ከሚሆኑ የተያዙ ሰዎች ጋር ወደ ጦላይ ወስደው በእስር ላይ አቆይተውኝ በታህሣሥ 24 2009 ዓ.ም ከእስር ተለቅቄያለሁ" በማለት ገልጸዋል፡፡

9. አቶ ኢብራሂም ኡመር በከር እድሜ 50፣ ነዋሪነታቸው ሐሮማያ ከተማ ቀበሌ 01 ሲሆን ባለትዳርና የ5 ልጆች አባት ናቸው፡፡ "በከተማው በተቀሰቀሰው የህዝብ ተቃውሞ ወቅት አንተም ቀስቃሽ ነበርክ በማለት በጥቅምት 13 2009 ዓ.ም ከቀኑ 10:30 የከተማው ከንቲባና ፖሊሶች በመሆን የቤቴን በር በመገንጠል እየደበደቡ ወደ ሀረማያ ፖሊስ ጣቢያ አስገቡኝ በማግስቱ ወደ አደሬ ጦር ካምፕ ከ600 ከማያንሱ ታሳሪዎች ጋር ቀላቀሉኝ፣ ከዚያም ወደ ጦላይ ተወሰድን፣ በጦላይ በታሰርንበት ወቅትም በባዶ እግራችን ጭምOOር ወታደራዊ ቅጣት ስንቀጣ ቆይተን በታህሣሥ 24 2009 ዓ.ም ተለቅቄያለሁ" በማለት ለሰመጉ አቤታቸውO3O OአቅርበዋልⲤ

10. አቶ አበበ ውቤ ዕድሜ 38 አዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 04 የሚኖሩ፣ "ጥቅምት 8 ቀን 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ላይ 6 ደህንነቶች ከመኖሪያ ቤታቸው ይዘው ፎቶ ካነሱዋቸው በኋላ በቤት መኪና ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንደወሰዷቸው፣ ቀጥሎም ከፖሊስ ጣቢያ አውጥተው ወደቦሌ ፖሊስ መምሪያ እንደወሰዷቸው፤ ከጥቂት ሰዓታት በኋላም 2 ፖሊሶችና 2 ሲቪል የለበሱ ሰዎች ከፖሊስ መምሪያው አውጥተው ወደ መኖሪያ ቤታቸው ይዘዋቸው እንደሄዱ፣ መኖሪያ ቤታቸውን ሙሉ ፍተሻ አድርገው ሙሉቀን ተስፋው የተባለ የቀድሞ "የቀለም ቀንድ" ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የጻፋቸው "የጥፋት ዘመን" እና "ምጽአተ አማራ" የሚሉ በ2008 ዓ.ም. የታተሙና በገበያ ላይ አሁንም የሚሸጡ መጽሐፍትን ከያዙ በኋላ ሁለት ሰዎች አምጥተው መጽሐፍቶች ለመገኘታቸው በእማኝነት እንዲፈርሙ እንዳደረጉ፣ እሳቸውም "ምርጫ ስለሌለኝ እንድፈርም ተደርጌአለሁ" ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ አቶ አበበ ለአንድ ወር በአምቼ ፖሊስ ጣቢያ ከቆዩ በኋላ ኅዳር 8 ቀን 2009 ዓ.ም. ከምሽቱ 12:00 ሰዓት ላይ "የለበስነውን ልብስ እንደለበስን ድንገት ውጡ ተብለን መኪና ውስጥ አስገብተውን እስከሚኒጋ ስንጓዝ አድረን አዋሽ አርባ



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ

አስገቡን፣ ጫማችንን እንድናወልቅ ተደርገን 3 ቀን ሙሉ እስረኞችን በባዶ እግር ጸሐይ ላይ ያስቀምጡን ነበር"፡፡ በተጨማሪም በቂ ምግብ እንደማይቀርብ፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃም እንደሌለ፣ ምሳ ሰዓት ላይ አንድ ዳቦ እና አንድ ኩባያ ውሃ እንደሚቀርብላቸው፣ በአንድ መኝታ ክፍል ውስጥ 114 ታሳሪዎች እንደሚኖሩ፣ ከመኝታ ክፍል ውስጥ መውጣት እንደማይቻል፤ በመፀዳጃ ሰዓትም 114 ሰው አንድ ላይ ወጥቶ ሜዳ ላይ እንደሚጸዳዳ ይገልጻሉ፡፡

"የተሃድሶ ትምህርት" በ6 ርእሶች እንደወሰዱና ታስረው በነበሩበት ጊዜ የመልካም አስተዳደር ችግር እንዳለ በግልጽ መነገሩን፣ በታህሣሥ 12 2009 ዓ.ም. ስልጣኞች ናችሁ ተብለው የምስክር ወረቀት እንደተሰጣቸው፣ በታህሣሥ 13 2009 ዓ.ም. አዲስ አበባ ማዕከላዊ የወንጀል ምርመራ ቢሮ ወስደው ከዚያ እንደፈቷቸውና በዚያም አንድ ላይ የነበሩት እሰረኞች 1180 እንደነበሩ ይገልጻሉ፡፡ ቀደም ብሎ በፖሊስ ጣቢያ በታሰሩበት ወቅት፣ ፍርድቤት የብር 3000 ዋስ ገንዘብ አስይዘው እንዲወጡ ፈቅዶላቸው ነበር፣ ነገር ግን ገንዘቡን ቢያስይዙም አልተፈቱም ነበር፤ ከአዋሽ አርባ ከተፈቱ በኋላ ያስያዙት ገንዘብ እንዲመለስላቸው ቢጠይቁ ወደፊት ክስ ይመሰረታል፤ አሁን አይመለስም እንደተባሉ፤ ከእስር ከተፈቱ በኋላም በደህንነት ሃይሎች ክትትል እየተደረገባቸው እንደሆነና ሥራም መስራት እንዳልቻሉ ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡

11. **አቶ ሰለሞን ስዩም** ዕድሜ 31፣ *ሥራ ደራሲ*፣ አድራሻ አዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 1 የካ ቀበሌ 01፣ የደረሰባቸውን ሲገልጹ ጥቅምት 17 ቀን 2009 ዓ.ም. ሌሊት 10 ሰዓት የመኖሪያ ቤቱ ተንኳኳኩቶ፤ በሩ ሲከፈት 10 የሚሆኑ የታጠቁና ያልታጠቁ ፖሊሶች ነበሩ፡፡ እስከ ጠዋቱ 3 ሰዓት ድረስ ቤታቸው እንደተፈተሸ፤ አጀንዳዎቻቸው፤ መጻሕፍት፤ ደብዳቤዎች፤ በርካታ ሲዲዎች እንደተወሰዱባቸውና እንዲመለሱላቸውም ጠይቀው ተመርምረው የሚያስጠይቅም ከሆነ ገና ትጠየቃለህ እንደተባሉና እቃዎቹንና እሳቸውንም ፈረንሳይ ለጋሲዮን ፖሊስ ጣቢያ እንደወሰዷቸው፤ ኮማንደሩ ምርመራ ካደረገ በኋላ ወደ የካ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ እንደተወሰዱ ይገልጻሉ፡፡ "በምን ምክንያት ታሰረ" ብሎ ቤተሰባቸው ሲጠይቅ "ፌስቡክ ላይ በሚጽፋቸው ጽሁፎችና በጻፋቸው መጽሐፍት ክትትል ስናደርግ ቆይተን ነው ያሰርነው" የሚል መልስ እንደሰተሰጣቸው ቤተሰብ ገልጧል፡፡ ከየካ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ወደ ቤላ ፖሊስ ጣቢያ ተዛውረው ለ26 ቀናት እንደታሰሩና ህዳር 8 ቀን 2009 ዓ.ም. ሌሊቱን ተጭነው ወደ አዋሽ 7 ኪሎ እንደተወሰዱ፤ ከደረሱ በኋላም የያዙትን ፍራሽ መጠቀም እንደማይችሉ ተገልጾ ፍራሹ እንደተወሰደባቸውና ጫማም እንዲያወልቁ መደረጋቸውን፤ ሽንት ቤት ተብሎ ሜዳ ላይ እንደምሽግ በተቆፈረ ሥፍራ ላይ በአንድ ጊዜ 116 ሰው እንደሚቀመጥ፣ ዋርድያው ተነስ ሲል መነሳት ግድ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በማግስቱ 5 ሰዓት ላይ ምደባና ማደሪያ እንደተደለደሉ፤ ከእነርሱ በፊት የታሰሩና ከአንድ ወር በላይ የቆዩ ከኦሮሚያ የተለያዩ አካባቢዎች የሄዱ እስረኞች ከፍተኛ ስቃይ ውስጥ እንደነበሩም ገልጧል፣ ምግብ ጠዋት 2 ዳቦ፣ ማታ 2 ዳቦ እየተሰጣቸው እንደቆዩና በጠቅላላው 1180 ሰዎች አብረዋቸው እንደታሰሩ ይገልጻል፡፡

አቶ ሰለሞን በመጨረሻም እንደገለጸው፣ የተሰጣቸው "የተሀድሶ ትምህርት" አይደገምም፣ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንዳንድ ጉዳዮች፣ መጭው ዘመን የኢትዮጵያ ህዳሴ ጉዞ፣ የወጣቱ ሚና በሐገር ግንባታ፣ የቀለም አብዮትና ዲሞክራሲያዊ ፌዴራሊዝም በሚሉ ርዕሶች ላይ ያተኮረ ሲሆን ስልጠናውን የሰጡት ከፌዴራል ፖሊስና ከመከላከያ የተውጣጡ ሰዎች ነበሩ፡፡

ታህሳስ 12 ቀን 2009 ዓ.ም. ተሐድሶ ወስደው ጨርሰዋል የሚል የምስክር ወረቀት እንደተሰጣቸው፣ በታህሣሥ 13 2009 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከሌሎች ጋር ተመልሶ እንደተፈታና ወደ ሥራው እንደተመለሰ፣ የተወሰዱበት አጀንዳዎች፣ መጻሕፍትና ሲዲዎች እንዲመለሱለት ጠይቆ "ተመርምሮ የሚያስጠይቅ ከሆነ ትጠየቃለህ፣ የማያስጠይቅ ከሆነ ይመለስልሃል" እንደተባለ ለሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በታሕሣሥ 27 ቀን 2009 ዓ.ም. አመልክቷል፡፡

12. **አቶ ፈቃዱ ነገሪ** እድሜ 54፣ በመምህርነት ሙያ የሚተዳደሩና በነቀምቴ ከተማ ቀበሌ 02 የሚኖሩ የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ አባል ናቸው፡፡ ጥቅምት 15 ቀን 2009 ዓ.ም. ከምሽቱ 2:30 በሚሆንበት ጊዜ

ብዛታቸው 11 የሚሆኑ ከፖሊስና ከመከላከያ የተቀላቀሉ አባላት መኖሪያ ቤታቸውን አስከፍተው ገቡ፤ "ቤቱን ሙሉ ፍተሻ ካደረጉ በኋላ ይዘውኝ ነቀምቴ ከተማ 1ኛ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱኝ፡፡ የያዙኝን ሰዎች መታወቂያቸውን እንዲያሳዩኝ ብጠይቃቸውም መታወቂያ እንደማያሳዩኝና በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የፈለግነውን ማድረግ እንችላለን ብለው መልስ ሰጡኝ" ብለዋል አቶ ፈቃዱ፡፡ በነቀምቴ 1ኛ ፖሊስ ጣቢያ ሁለት ወር ከአንድ ሳምንት እንደታሰሩ፣ ፍርድ ቤትና ፖሊስ ጣቢያም ቀርበው እንዳልተጠየቁ በኮማንድ ፖስቱም እንዳልተጠየቁ ገልጸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ከቤተሰብ ጋር መገናኘት እንዳልተከለከሉ ገልጸው ነገር ግን አንድ ታሳሪ ማግኘት የሚገባውን የምግብና የህክምና እርዳታ እንዳላገኙ፣ ታህሳስ 13 ቀን 2009 ዓ.ም. ወደ ጦላይ ወታደራዊ ማሰልጠኛ እንደተወሰዱና እስከ ጥር 26 ቀን 2009 ዓ.ም. ድረስ ቆይተው እንደተፈቱ ይገልጻሉ፡፡ አቶ ፈቃዱ እንደገለጹት በጦላይ ማሰልጠኛ በሁለተኛው ዙር 5643 ታሳሪዎች ነበሩ፡፡ በቆይታቸው ወቅት ዳቦ፣ ሽሮና ሻይ ብቻ ሲቀርብላቸው እንደነበርና ለአንድ ታሳሪ የሚቀርበው ምግብ በዓይነቱም ሆነ በመጠኑ አነስተኛ እንደነበረም ገልጸዋል፡፡ በጠባቂዎቻቸው ስብዕናቸውን የሚነኩ ድርጊቶች ሲፈጽሙባቸው እንደቆዩ፤ የመጸዳጃ ቤት የተባለውም የተቆፈረ ጉድጓድ ከላይ በላስቲክ ሸራ የተሸፈነ፣ የእንጨት ርብራብ ተደርጎበት አፈር የተመለሰበት እንደነበር፣ በአጠቃላይ ምንም ንጽህና በሌለበት ቦታ ሲጸዳዱ እንደቆዩ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ንጽህናውን ያልጠበቀ ውሃ ሲጠቀሙ እንደቆዩና ለገላ መታጠቢያ የተከለለ ሥፍራ (ሻወር) ባለመኖሩ በግቢው ውስጥ አግባብ ባልሆነ ቦታ እንደ ፖሊሶች ፍላጎትና ፈቃደኝነት ሲታጠቡ እንደነበር ገልጸዋል፡፡ ቦታው በረሃማ በመሆኑ በከፍተኛ ሙቀት አለመስማማት ሳቢያ ብዙ ሰዎች ጸሀይ ውስጥ መቆምና መቀመጥ እያቃታቸው ሲወድቁ መመልከታቸውን መስክረዋል፡፡

"ወታደራዊ ካምፕ በመሆኑ አድርግ አታድርግ ትእዛዝ ከመስጠት ውጭ ለማንኛውም ዓይነት ጥያቄ መልስ አልነበረም፡፡ ስልጠና እንሰጣለን በሚል ምክንያት በበረሃ ቦታ ላይ በቡድን ተከፋፍለን (አንድ ቡድን ውስጥ 25 እስረኛ ይገኛል) በአውላላ ሜዳ ላይ እንጨት ላይ ተቀምጠን ቆይተን በሰልፍ ወደ ምሳ እንሄዳለን፣ ከሰዓት በኋላ 8 ሰዓት ተሰልፈን ወደ ሜዳ እንሄዳለን እዛም ባዶ ሜዳ እንጨት ላይ ተቀምጠን ቆይተን ሲመሽ ተሰልፈን ወደ ማደሪያ እንመለሳለን"፡፡ የህክምና አገልግሎትን በተመለከተ ሐኪሞች የተመደቡ ቢሆንም

1. በቂ መድሀኒቶች አልነበሩም
2. እስረኛ በሚታመምበት ቀንና ጊዜ ወዲያውኑ ሕክምና አያገኝም
3. የላብራቶሪ ምርመራ አልነበረም

እንዲሁም ጦላይ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ከገባነው ታሳሪዎች ውስጥ 5619 "ተሀድሶ" ወስደን ወደ ቤተሰቦቻችን ስንመለስ ቀሪዎች ግን ወዴት እንደተወሰዱ አላውቅም" በማለት ለሰመጉ አብራርተው ገልጸዋል፡፡

13. ጋዜጠኛ አናኒያ ሶሪ እድሜ 33፣ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5፣ ቀበሌ 19/20 በቤት ቁጥር 377 ነዋሪ ነው፡፡ የ"ነገረ ኢትዮጵያ" ጋዜጣ፣ የ"ፍኖተ ነጻነት" ጋዜጣ እና የ"ሚሊዮኖች ድምጽ" ጋዜጣ አዘጋጅ ሆኖ አገልግሏል፡፡ በ"አውራ አምባ ታይምስ" ጋዜጣ ላይ ሪፖርተር የነበረ ሲሆን በ"አዲስ ገጽ" መጽሄት ላይ ደግሞ ማኔጂንግ ደይሬክተር ሆኖ ሰርቷል፡፡ ጋዜጠኛው ለሰመጉ እንደገለጸው፣ በሙያው ሃሳቡን በነጻነት በመግለጹ ብቻ በየጊዜው በጸጥታ ሃይሎች ክትትል ይደረግበትና ዛቻ ይደርስበት የነበረ ሲሆን፤ ህዳር 8 2009 ዓ.ም. ከቀኑ 11 ሰአት ላይ ከሚኖርበት አዲስ ከተማ በታክሲ ተሳፍሮ በአዲስ አበባ የዩኤስ አሜሪካ ኤምባሲ በር ላይ እንደወረደ ሁለት ሲቪል በለበሱ የደህንነት ሃይሎች ተይዞ ቦሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ታስሯል፡፡ ግለሰቡ የተያዘበት ምክንያት እስካሁን ባይታወቅም በወቅቱ ቤተሰቡ ባቀረበው አቤቱታ ላይ በገለጸው መሰረት እና ጋዜጠኛውን በተለያዩ ጊዜያት እስር ቤት ሄደው የጎበኙት የሰመጉ መርማሪዎች ከታሳሪው ባገኙት መረጃ መሰረት የታሰረው በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ኮማንድ ፖስት ትእዛዝ ነው ተብሏል፡፡ እስከሚፈታበት ጊዜ ድረስ ፍርድ ቤት አልቀረበም፤ የታሰረበት ቦታ ለጤንነት ጎጂ የሆነ ቦታ ነው፡፡ መጽሃፍም፣ መጽሃፍ ቅዱስ እንዳይገባለት ተከልክሏል፡፡ በእስር ላይ እያለ የጤንነት ችግር ገጥሞት ነበር፡፡ ቤተሰቡንም ሆነ ወላጆቹን

የሚያስተዳድረው እርሱ ነው፣ በመታሰሩ ቤተሰቡ በችግር ላይ ወድቆ ቆይቷል። ጋዜጠኛ አናኒያ ሶሪ ቀድሞ ከታሰረበት ቦሌ ክፍለ ከተማ ወደ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ተዘዋውሮ በአደራ እስረኝነት ከቆየ በኋላ መጋቢት 4 2009 ዓ.ም ከእስር ተፈቷል።



14. ጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩ እድሜ 34፣ ቦሌ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ነው። ጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩ ከመታሰሩ በፊት በ"የሚሊዮኖች ድምጽ" ጋዜጣ፤ "እንቁ" መጽሄትና በ"አዲስ ገጽ" መጽሄት ላይ ዋና አዘጋጅ ሆኖ ሰርቷል። በ"አውራ አምባ ታይምስ" ጋዜጣ ላይ ደግሞ በአዘጋጅነት አገልግሏል። የሰመጉ መርማሪዎች ጋዜጠኛውን በታሰረበት ቦታ በተደጋጋሚ በጎበኙበት ወቅት እንደተረዱት፣ ጋዜጠኛው የጋዜጠኝነት ተግባሩን በሚፈጽምበት ጊዜ ሥራውን እንዲያቆም በመንግስት የጸጥታ ሃይሎች ከፍተኛ ማስፈራራት ይደርስበት ነበር። የጋዜጠኝነት ግዴታውን ሲወጣ በተደጋጋሚ ጊዜ ታስሮ ተፈቷል። ህዳር 8 2009 ዓ.ም. ከምሽቱ 1:00 ሰአት አካባቢ ካሳንቺስ በሚገኘው ሮሚና ካፌ ውስጥ እንዳለ ሲቪል የለበሱ የጸጥታ ሀይሎች እየደበደቡት በመጀመሪያ ወደ ገርጂ ፖሊስ ጣቢያ ወስደው ለሶስት ቀናት ካቆዩት በኋላ ወደ ቦሌ ፖሊስ መምሪያ ወስደው አስረውታል። ጋዜጠኛው የታሰረው በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የኮማንድ ፖስት ትእዛዝ መሆኑም ለማወቅ ተችሏል። የጋዜጠኛው ቤተሰብ በአካል ሰመጉ ቢሮ ተገኝቶ ባመለከተው መሰረት እና የሰመጉ መርማሪዎች ጋዜጠኛውን በእስር ቤት በጎበኙበት ወቅት ባገኙት መረጃ መሰረት ጋዜጠኛ ኤልያስ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ ይህ መግለጫ ይፋ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ ፍርድ ቤት አልቀረበም፤ መጻሕፍት፤ ጋዜጦች እና መጽሃፍ ቅዱስ እንዲያነብ ቤተሰቡ የታሰረበት ፖሊስ ጣቢያ ድረስ ቢወስድለትም ፖሊስ በመከልከሉ ሊደርሰው አልቻለም። በመሆኑም የማንበብና የኃይማኖት ነጻነቱ ተገፏል። የጋዜጠኛ ኤልያስ ቤተሰቦች ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ ነዋሪ በመሆናቸው በየጊዜው ሊጠይቁት አልቻሉም። ጋዜጠኛው ይህ ልዩ መግለጫ በሚጠናቀርበት ሰአት በቦሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ በእስር ላይ ይገኛል።



15. ጋዜጠኛ ዮሀንስ ገ/እግዚአብሄር ታረቀ፦ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ነዋሪ የሆኑ የ41 ዓመት ጎልማሳና በጀርመን ድምጽ የአማርኛው ራዲዮ ፕሮግራም ዝግጅት ክፍል የአዲስ አበባ ዘጋቢ ናቸው። በሚሰሩበት የጋዜጠኝነት ሥራ በደረሳቸው መረጃ መሰረት የካቲት 2 ቀን 2009 ዓ.ም. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰመራ ከተማ ተገኝተው የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት መታሰርን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት የዩኒቨርሲቲው የውጭ ጉዳይና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ሀላፊ የሆኑትን አቶ

አቡበክር ያሲንን በማነጋገር ላይ እንዳሉ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ የክልሉ ልዩ ሀይል አዛዥ ኮማንደር ዲኖ ሦስት ወታደሮችን አስከትለው ለአምስት(5) ሰአታት (ከረፋዱ 4 ሰዓት እስከ ቀኑ 9 ሠዓት) ድረስ በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን እስርቤት አስረው ምርመራ አድርገውብኛል ሲሉ ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡ በምርመራው ወቅትም ስለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት መታሰር ያደረከውን ቃለመጠይቅ አምጣ፣ የቀረጽከውን ድምጽ አምጣ ተብለው መጉላላት ደርሶባቸዋል፡፡ በእጅ የሚያዝ ኮምፒውተራቸው (ላፕቶፕ) ተመርምሯል፤ በመጨረሻም "ስለ ልማት፤ ስለድርቅ መዘገብ ትችላለህ፤ ስለፕሬዚዳንቱ መታሰር እንድትዘግብ አንፈቅድልህም" ብለው "ህገመንግስታዊ መብቴን ገፈው ለቀውኛል፤ ከፍተኛ የስነልቦና ጫና ፈጽመውብኛል፤ በብዙሃን መገናኛ አዋጅ መሰረት የጋዜጠኝነት ሥራዬን እንዳልሠራና እንዳልዘግብ አድርገውኛል፤ ከእንግዲህ ወደ አፋር ክልል ሄጄ ለመዘገብም ዋስትና የለኝም፤ እዚህ እያለሁም ዋስትና አጥቻለሁ" በማለት ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡ ጋዜጠኛ ዮሐንስ የደረሰባቸውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት በተመለከተ የሰመጉ መርማሪዎች የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር ለሆኑት ኮማንደር ዲኖ ስልክ ደውለው ሲጠይቁ የተሰጣቸው መልስ ጋዜጠኛ ዮሀንስ ገብረእግዚአብሄር እንደልታሰረ፣ ሆኖም ግን ቃለምልልስ ያደረገው ባልተፈቀደ ቦታ ስለሆነ በቢሮ ውስጥ ለሰዓታት አነጋግረነዋል ሲሉ ቃላቸውን ሰጥዋል፡፡

16. **ጦማሪ በፍቃዱ ሀይሉ** በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ነው፡፡ በጦማሪነቱና በተለይም የዞን ዘጠኝ ጦማሪዎች አባል በመሆኑ እንዲሁም በተለያዩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳች ዙሪያ በሚፅፋቸው ጽሁፎቹና በሚሰጣቸው አስተያየቶቹ ይታወቃል ፡፡

የ"ውይይት" መጽሄት ዋና አዘጋጅ የነበረው ጋዜጠኛ በፍቃዱ ሀይሉ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ላይ ሀሳቡን በነጻነት በመግለጽም ይታወቃል፡፡ በሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ላይ የሚያተኩሩ በርካታ ጽሁፎችን አዘጋጅቶ በተለያዩ የግል መጽሄቶች ላይ የሚጽፍ ጋዜጠኛ ሲሆን በማህበራዊ ድረ ገጾችም ላይ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ በስፋት ይጽፋል፡፡

ጋዜጠኛ በፍቃዱ ሀይሉ በጥቅምት 22 2009 ዓ.ም. ከአሜሪካ ድምጽ የአማርኛ ዝግጅት ክፍል ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ ላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አጥላልተሃል በሚል ምክንያት ህዳር 2 2009 ዓ.ም. ከንጋቱ 12:30 ላይ ከመኖሪያ ቤቱ ሲቪል በለበሱ አምስት ሰዎች ከተወሰደ በኋላ በመጀመያ የካ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ፤ በመቀጠልም "መሪ" አካባቢ በሚገኝ ማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ጣቢያ ታስሯል፡፡ ከህዳር 9 2009 ዓ.ም ጀምሮ በአዋሽ ሰባት የፖሊስ ማሰልጠኛ ውስጥ ከአንድ ወር በላይ ከታሰረ በኋላ ታህሳስ 13 2009 ዓ.ም. ከእስር ተለቋል፡፡



17. **ወ/ት ወይንሸት ሞላ** ዕድሜ 27፣ አዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ነዋሪ የሆነች እና በትምህርት ላይ የምትገኝ፤ ወይንሸት የደረሰባትን የመብት ጥሰት ለሰመጉ እንደሚከተለው ገልጻለች: "የሰማያዊ ፓርቲ አባል በመሆኔ በተለያዩ ጊዜያት ከሰባት (7) ጊዜ በላይ ታስሬአለሁ፡፡ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት ቦሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ አንድ ወር ታሰርኩ፡፡ ቦሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ በታሰርኩበት ጊዜ ሲቪል የለበሱ ደህንነቶች እየመጡ ማስፈራራት አድርሰውብኛል፡፡ ያለኝን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለምን አትተይም በሚል ማስፈራሪያ አድርሰውብኛል፡፡ ከዚያ በኋላ 2ኛ ዙር ጦላይ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ታስሬአለሁ፤ ወደ ጦላይ የተወሰድነው በድንገት ነበር፤ ወዴት እንደሚወስዱንም አልነገሩንም፡፡ ጦላይ አንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን አቆይተውናል፡፡ ጦላይ 5543 ታሳሪዎች ነበርን፤ ከእነዚህ ውስጥ 113 ሴቶች ነበርን፤ ሁላችንም የምናድረው በአንድ አዳራሽ ነበር፡፡ ከፍተኛ ሙቀት ባለበት 15 ቀን ሙሉ በአዳራሹ የታሰርነው 113 ሴቶች አዳራሹ ተዘግቶብን በከፍተኛ ሙቀት ስንሰቃይ ነበር፤ አንዳንድ ሴቶች

እራሳቸውን እየሳቱ ይወድቁ ነበር፡፡ ምግብ፣ ጠዋት ዳቦና ሻይ፤ ምሳና ራት ሰዓት ዳቦ በሽሮ ወጥ ይሰጠን ነበር፤ ወር ከአስራ አምስት ቀን በሙሉ ምግቡ ይህ ነበር፡፡ በሳምንት አንድ ቀን እንድንታጠብ ይፈቅዱልናል፤ የመጸዳጃ ቤት በግልጽ ሜዳ ላይ ነበር የምንጠቀመው፤ ጦላይ እንዳለን በቤተሰብና በዘመድ መጠየቅ አይፈቀድም ነበር፤ ቤተሰብም ያለንበትን ቦታ አያውቅም ነበር"፡፡ ወ/ት ወይንሸት ለሰመጉ በተጨማሪ እንዳብራራችው፤ "በጦላይ ትምህርት ሲሰጥ የአመለካከት ልዩነት የሚያቀርቡ ታሳሪዎችን እውጭ ከዛፍ ጋር አስረው ያሳድሯቸው ነበር"፡፡ ወ/ት ወይንሸት የታሰረችው ህዳር 13 ቀን 2009 ዓ.ም ሲሆን የተፈታችው ደግሞ ጥር 26 ቀን 2009 ዓ.ም. መሆኑን ለሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ ግንቦት 2 ቀን 2009 ዓ.ም ገልጻለች፡፡

18. **አቶ በድሉ መንግስቱ** ዕድሜ 40፣ ገላና ወረዳ ቶሬ ከተማ ነዋሪ የነበሩ፤ አቶ በድሉ ስለደረሰባቸው የመብት ጥሰት ለሰመጉ በሚከተለው አኳኋን ገልጸዋል፡ "ለሰማያዊ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አዲስ አበባ መስከረም 24 ቀን 2009 ዓ.ም. መጣሁ፡፡ ጠቅላላ ጉባዔውን ጨርሼ ወደ ቤቴ ለመመለስ ስዘጋጅ ባለቤቴ ስልክ ደውላ፣ የተወሰኑ የወረዳው ባላስልጣኖችና የአካባቢው ታጣቂዎች መኖሪያ ቤታችንን በጓሮ በኩል በሩን ሰብረው እንደገቡና ከቤት አስወጥተው ለሶስት ቀናት አስረው እንዳቆዩዋት፤ ቤቱንም እናቃጥለዋለን እንዳሏት ገለጸችልኝ፡፡ ባለቤቴ መምህርት ምስራቅ አሰፋን ከሁለት ህጻናት ልጆቻችን ጋር ከቤታችን ስላስወጧቸው በሌሎች ሰዎች ቤት ለመጠለል ተገድደው ነበር፡፡ የወረዳው ባለሥልጣናት ለባለቤቴ እንደገለጹት፣ ከቤት ያስወጧቸው ‹‹ቤቱን የሠማያዊ ፓርቲ አባላት ስለሚሰበሰቡበት›› በሚል ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ቤቴንና ቤተሰቤን ጥዬ በችግር ላይ ቆይቻለሁ" ብለዋል፡፡ አቶ በድሉ በተጨማሪም፣ ባለቤታቸው መ/ርት ምስራቅ አሰፋ ጦላይ ወታደራዊ ማሰልጠኛ በ2ኛ ዙር በእስር ላይ እንደቆዩና "የተሃድሶ ስልጠና" ሰርተፍኬት ተሰጥቷቸው እንደተፈቱ፤ ሆኖም ወደ ቤታቸው እንዳይገቡ በወረዳው አስተዳደር እንደተከለከሉና ቤቱም ይህ መግለጫ ይፋ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ እንደተዘጋ ገልፀዋል፡፡ "በቤተሰቤ በተለይም በባለቤቴ ላይ የደረሰውን ችግር ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ በታህሳስ ወር 2009 ዓ.ም. ባመለክትም አጣሪ ቦርዱ ‹‹እኛ ምንም ልንረዳህ አንችልም ኮማንድ ፖስቱ ጋር ሄደህ አመልክት የሚል መልስ ሰጥቶኛል›› ሲሉ ለሰመጉ ገልጸዋል፡፡ የአጣሪ ቦርዱን ምላሽ በመያዝ ዋናው ኮማንድ ፖስት አዲስ አበባ ሲጠይቁ፤ ሻሸመኔ ለሚገኘው ኮማንድ ፖስት ሄደው እንዲያመለክቱ ተገልጾላቸው ነበር፡፡ በመቀጠልም "የሻሸመኔ ኮማንድ ፖስት ጉዳዩን ለቦረና ወረዳ ኮማንድ ፖስት አስተላለፈው" ሲሉ የደረሰባቸውን መጉላላት ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡ ለቦረና ኮማንድ ፖስት በአካል ሔጀ ሳመለክት ‹‹ለገላና ወረዳ በስልክ ነግረናቸዋል፣ እዛ ጠይቃቸው›› ብለው ወደ ገላና ወረዳ እንደላኩዋቸውና ማመልከቻውን ለማቅረብ በሔዱበት ከጥር 20 2009 ዓ.ም ጀምሮ ገላና ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ በእስር ላይ እንደሚገኙ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

19. **ህጻን መክሊት ታምሩ** ዕድሜ 12፣ ፆታ ሴት፣ አድራሻ ኮንሦ ወረዳ፤ ኅዳር 03 ቀን 2009 ዓ.ም ከምሽቱ በአምስት ሰዓት የሕፃን መክሊት ታምሩ ወላጆች ወደሚኖሩበት መኖሪያ ቤት የገቡት የመከላከያ ሠራዊት፣ የፌደራል ፖሊስና የክልሉ ልዩ ኃይል አባላት ‹‹ወላጆቻችሁ የት አሉ?›› ብለው በመጠየቅ ወላጆቻቸውን ፈልገው ሲያጡ የ12 ዓመት ሕፃን የሆነችውን መክሊት ታምሩን ወስደው ከሌሎች ዐዋቂ እሥረኞች ጋር በኮንሶ ቴክኒክና ሙያ ት/ቤት አሥረዋታል፡፡ ወላጅ አባቷ ለሰመጉ ባቀረቡት አቤቱታ እንደገለጹት ሕፃን መክሊት የተያዘች ዕለት ድብደባ ተፈጽሞባታል፡፡ ለእሥር በመዳረጓ ምክንያትም ከትምህርቷ ተስተጓጉላለች፡፡ ህፃን መክሊት የሰመጉ ምርመራ በሚካሄድበት ወቅት (ታህሣሥ 19 2009) እስር ላይ እንደነበረች ታውቋል፡

20. **አቶ መኮንን ጌታቸው ሙለታ**፡ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን መንዲዳ ወረዳ ነዋሪ ነው፡፡ የአቶ መኮንን ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ አልማዝ ቶላ በሚያዝያ 13 2009 ዓ.ም. ለሰመጉ በጻፉት ማመልከቻ፣ ባለቤታቸው ስለደረሰባቸውና አሁን ስለሚገኙበትም ሁኔታ እንደሚከተለው አስረድተዋል፡ "ጥቅምት 29 ቀን 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 4 ሰዓት ላይ የኦሮሚያ ፖሊስ አባላት

መጥተው ባለቤቱ፣ የወንድሜን መቃብር ሀውልት ከሚያሰራበት ቦታ ወስደው አስረውታል፡፡ ወንድሜ አቶ ነጋሽ ከበደ ዳምጤ መኖሪያ አድራሻው አዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ የነበረ መስከረም 22 ቀን 2009 ዓ.ም. የኢሬቻን በአል ለማክበር ቢሾፍቱ በተገኘበት ወቅት ተገድሎ አስከሬኑን ከምኒልክ ሆስፒታል ተረከብን፡፡ የቀብር ሥነሥርአቱም በትውልድ ቦታው ሰሜን ሸዋ አብቹና ናኦ ወረዳ ዶዬ ዳዊ ቀበሌ በመስከረም 25 2009 ዓ.ም. ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ተፈጽሟል፡፡ ጥቅምት 28 ቀን 2009 ዓ.ም. በቀብር ቦታው ላይ መታሰቢያ ሀውልት ማሰራት ጀመርን ሚቹ ወንድሜ መኖሪያ ቤት ጀምሮ ሳይጨርሰው ስለሞተ "አንተ የጀመርከውን እኛ እንጨርሳለን" የሚል ጥቅስ በመጻፉ ፖለቲካዊ ትርጉም ሰጥተው ባለቤቴን "ጥቅምት 29 ቀን 2009 ዓ.ም አሰሩት፡፡ የጥቅሱን ትክክለኛ ምክንያት ብናስረዳም የሚሰማን አጣን፡፡ ክስ ሳይመሰረትበት እስካሁን መንዲዳ ፖሊስ ጣቢ በእስር ላይ ይገኛል" ፡፡ ሰመጉ ሰሜን ሸዋ ዞን አብቹና ናአ ወረዳ መንዲዳ ፖሊስ ጣቢያ ስልክ ደውሎ አቶ መኮንን ፍርድ ቤት ሳይቀተርብ ለምን ይህን ያህል ጊዜ እንደታሰረ ላቀረበው ጥያቄ የተሰጠው መልስ እስረኛው የኮማንድ ፖስት እስረኛ መሆኑን፣ ክስ ለመመስረት ክሱን የሚመሰተርተው የዞን አቃቤ ህግ ነው ወይስ የወረዳ አቃቤ ህግ የሚለው ጉዳይ መመሪያ ተጠይቆበት ምላሽ እየጠበቁ መሆናቸው ነው፡፡

21. አቶ ዋሬ ሎሎ ዕድሜ 43፣ ጉጂ ዞን ኡራጋ ወረዳ 01 ቀበሌ የሚኖሩ የመድረክ አባል ናቸው፡፡ የሆቴልና የመድሃኒት መደብር ፈቃድ ስላላቸው በንግድ ስራ ይተዳደራሉ፡፡ ነገር ግን የወረዳው ባለስልጣናት ከመድረክ የፖለቲካ ፓርቲ አባልነታቸው ጋር በተያያዘ አላሰራ እንዳሉዋቸው፤ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከታወጀ በኋላ የጸጥታ ኃይሎች መኖሪያ ቤታቸው ድረስ ሊይዟቸው ሄደው ሲያጧቸው ከዚህ በታች የተገለፁትን የቤተሰባቸውን አባላት፡

    1. ወ/ሮ ብርቱካን ብርሃኔ (ባለቤት)
    2. ወ/ሮ ሎጤ ጆሎ (ሁለተኛ ባለቤት)
    3. ወጣት ደንቢ ሎሎ (ወንድሜ)
    4. አቢቲ ዋሬ (ልጅ)
    5. ከተወለደች 28 ቀናት ብቻ የሆናት ህጻን ልጃቸው
    6. ሙሉ በለጠ (የፋርማሲ ሰራተኛ)

    በመያዝ ከህዳር 27 ቀን 2009 ዓ.ም. ጀምሮ ለአንድ ወር ከ10 ቀን በኡራጋ ፖሊስ ጣቢያ እንዳሰሯቸው በታህሣሥ 12 2009 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡

    በግንቦት 02 2009 ዓ.ም ከአቶ ዋሬ ሎሎ ቤተሰብ በስልክ ለሰመጉ በተሰጠ መረጃ መሠረት፤ አቶ ዋሬ ሎሎ በሚያዝያ 24 2009 ዓ.ም. ወደ መኖሪያ ቤታቸው በመጓዝ ላይ እንዳሉ ከመንገድ ላይ ተይዘው፣ ይህ መግለጫ እየተጠናቀረ እስካለበት ጊዜ ድረስ ኡራጋ ፖሊስ ጣቢያ በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡

22. አቶ ዳንኤል ሺበሺ እድሜ 42፣ በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከ ወረዳ 02 ነዋሪ ናቸው፡፡ አቶ ዳንኤል ሺበሺ ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ሲሆኑ በቀድሞው የአንድነት ፓርቲ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ሆነው አገልግለዋል፡፡ ከዚህ ቀደም ሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም. በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው ታስረው ክስ ቀርቦባቸው ሲከራከሩ ከቆዩ በኂላ ግንቦት 1 ቀን 2008 ዓ.ም. በነጻ ተሰናብተዋል፡፡ በኂላ ላይ ደግሞ ህዳር 8 ቀን 2009 ዓ.ም. ከቀኑ 10 ሰአት አካባቢ አዲስ አበባ ውስጥ ልዩ ስሙ ካሳንቺስ ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ በመንግስት ታጣቂ ሃይሎች በቁጥጥር ስር ከዋሉ በኂላ በመጀመሪያ ገርጂ ማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ጣቢያ በኂላ ደግሞ ቦሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ታስረዋል፡፡



አቶ ዳንኤል የታሰሩበት ምክንያት ሳይታወቅ ከስድስት ወር በላይ ከቆዩ በኂላ ቀደም ሲል በነጻ የተሰናበቱበት የሽብር ክስ እንደገና እንዲንቀሳቀስ ተደርጎ የዋስትና መብታቸውን ተነፍገው በማረሚያ ቤት እንዲቆዩ ተደርገዋል። የቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆናቸው በእርሳቸው መታሰር ምክንያት ቤተሰባቸው ለችግር ተጋልጧል። ገርጂ ፖሊስ ጣቢያ በነበሩበት ጊዜም ሆነ ይህ መግለጫ በሚጠናቀርበት ወቅት ባሉበት የቦሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ቤተሰቦቻቸው መጽሃፍትና መጽሃፍ ቅዱስ ይዘውላቸው ወደ እስር ቤት ቢሄዱም ፖሊስ እንዳይገባ ከልክሏቸዋል። ስለሆነም የመረጃ ማግኘትና የእምነት ነጻነታቸው ተገፏል።

23. አቶ ማሙሸት አማረ ድልነሴ፡ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የቀድሞ አመራር ነበሩ። በአቶ ማሙሸት ላይ ስለደረሰው የመብት ጥሰት በተለያየ ጊዜ ለሰመጉ ያመለከቱት የቤተሰባቸው አባላት እንደገለጹት “አቶ ማሙሸት በተለያዩ ጊዜያት በስድስት የደህንነት አባላት በሚሄዱባቸው ሥፍራዎች ሀሉ ክትትል ይደረግባቸው ነበር። በመንግሥት በሚደርስባቸው ወከባም ምክንያት የደረሱበት ሳይታወቅ ቆይቶ ነበር”። ሆኖም ግን አቶ ማሙሸት ባደረባቸው ሕመም ምክንያት የጸበል ህክምና ለመከታተል ከጥር ወር 2009 ዓ.ም. ጀምሮ ምንጃር ሐገር ሸንኮራ በመሄድ የቅዱስ ዮሐንስ ጸበል ላይ እንደሚገኙ ለቤተሰብ በስልክ አሳውቀው ነበር። በመሆኑም ወንድማቸው አቶ ግዛቸው አማረ ድልነሴ ሸንኮራ ጸበል እየተመላለሰ ሲጠይቃቸው ቆይቷል። አቶ ግዛቸው ወንድሙ፣ አቶ ማሙሸትን እንደተለመደው ለመጠየቅ መጋቢት 19 2009 ወደ ሸንኮራ ሄዶ የነበረ ቢሆንም ለ4 ቀናት ከቤተሰብ ግንኙነት ውጪ ሆኖ ቆይቷል። በኂላም በመጋቢት 23 2009 ከምሽቱ 2 ሰዓት ላይ ሸንኮራ ጸበል ላይ እያሉ ከአቶ ማሙሸት ጋር በጸጥታ ኃይሎች ተይዘው አዲስ አበባ ወደሚገኘው ማዕከላዊ የወንጀል ምርመራ ቢሮ ተወስደው ታስረዋል። አቶ ማሙሸትና ወንድማቸው አቶ ግዛቸው ይህ መግለጫ እስከሚጠናቀርበት ጊዜ ድረስ በዚሁ በማዕከላዊ በእስር ላይ ይገኛሉ።

24. ተማሪ ደጋጋ ክፍሌ ዕድሜው 19፣ በምእራብ ወለጋ ቤጊ ወረዳ ቤጊ የመሰናዶ ት/ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪ ነው። ጥቅምት 23 ቀን 2009 ዓ.ም. ከቀኑ 10 ሰዓት አካባቢ ከሚማርበት ቤጊ የመሰናዶ ትምህርት ቤት ውስጥ ተይዞ ቤጊ የወታደሮች ካምፕ አሳድረውታል። በማግስቱ በጊምቢ ከተማ ከፖሊስ ጣቢያና ከማረሚያ ቤት ውጭ በከተማው አስተዳደር ጽ/ቤት ውስጥ ከሌሎች ሁለት ታሳሪዎች ጋር ሁለት ሳምንት ከታሰረ በኂላ ወደ ማእከላዊ እስር ቤት አዲስ አበባ ተወስዷል። ፍርድ ቤት እስካሁን አልቀረበም። ይህ ሪፖርት እስከሚጠናቀርበት ጊዜ ድረስ ተማሪ ደጋጋ በማእከላዊ የወንጀል ምርመራ እንደሚገኝ ቤተሰቦቹ ለሰመጉ አመልክተዋል።

25. አቶ ስንታየሁ ቸኮል ደጀኔ፡- አዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 4 ነዋሪ የሆነ የ36 ዓመት ሰው ነው። አቶ ስንታየሁ በቀድሞው የአንድነት ፓርቲ ውስጥ አባል ነበር። በተጨማሪም በማህበራዊ ሚዲያዎች እና በተለያዩ ጋዜጦች ላይ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ጽሁፎችን በመጻፍ ይታወቃል። ነሐሴ 14 ቀን 2008 ዓ.ም. የእለት ሥራውን አጠናቆ የቅርብ ዘመዶቹን ለመጠየቅ ወደ አዲሱ ገበያ ሲደርስ ሰባት ሰዎች ሁለቱ መሳሪያ የታጠቁ “ለጥያቄ እንፈልግሃለን” በማለት ወደ አራዳ ፖሊስ መምሪያ ወስደውታል።



አቶ ስንታየሁ ነሐሴ 16/2008 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የተወሰደ ሲሆን ከነሐሴ 17/2008 ዓ.ም. ጀምሮ ለአራት ወራት ያህል በማዕከላዊ የወንጀል ምርመራ ክፍል ከታሰረ በኂላ ታህሳስ 26/2009 ዓ.ም ከእስር ተለቋል። በማዕከላዊ የወንጀል ምርመራ በታሰረበት ጊዜ ከፍተኛ ድብደባና ዛቻ እንደተፈጸመበት ለሰመጉ አመልክቷል።

26. 26. አቶ መስፍን ብርሃኑ ዕድሜ 33 በዳንግላ ከተማ ቀበሌ 04 በግል ስራ የሚተዳደር ሲሆን ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ነው። የከተማው ፖሊስ አባላት ታሳሪውን ከሚሰራበት ቦታ ይዘው ከጳጉሜ 01/2008 ዓ.ም እስከ ህዳር 9/2009 ዓ.ም. ድረስ በዳንግላ ማረሚያ ቤት አስረውታል። ህዳር 9/2009 ዓ.ም. የወረዳው ፍርድ ቤት በነጻ ቢያሰናብተውም ፖሊስ መልሶ በመያዝ ለተሃድሶ በሚል ብርሸለቆ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ከህዳር 10/2009 ዓ.ም. -ታህሳስ 13/2009 ዓ.ም ድረስ በእስር አቆይቶታል። ከብር ሸለቆ ሲወጣ ኮሶ በር ላይ ታህሳስ 13/2009 ዓ.ም. በድጋሚ “ለጥያቄ ትፈለጋለህ” ተብሎ በፖሊስ ተያዞ ወደ ዳንግላ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰደ። አቶ መስፍን ከታህሳስ 13/2009 እስከ ታህሳስ 19/2009 ዓ.ም. በዳንግላ ፖሊስ በእስር ጣቢያ የቆየ ሲሆን ታህሳስ 16/2009 ዓ.ም. ወደ ዳንግላ መከላከያ ካምፕ ተወስዶ ከባድ ድብደባ ደርሶበታል። በነዚሁ ቀናት አባቱን ለመጠየቅ በ17/04/2009 ዓ.ም. ወደ ዳንግላ ፖሊስ ጣቢያ የሄደው የ11 ዓመቱ ታዳጊ ናትናኤል መስፍን በፖሊስ ባልደረባ ክፉኛ መደብደቡን ለሰመጉ ገልጿል። አቶ መስፍን ብርሀኑ ታህሳስ 19/2009 ዓ.ም. ወደ ዳንግላ ማረሚያ ቤት ተወስድው ታስረዋል።

27. አቶ ጌታቸው ሞላ ዕድሜ 28፣ ሥራ ባጃጅ ሾፌር ሲሆን ጥር 11/2009 ዓ.ም. ”በባጃጅ መኪናህ ላይ አርማ የሌለው አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለም ያለውን የኢትዮጵያ ባንዲራ ለጥፈሃል” በማለት የመንግስት የጸጥታ ሀይሎች ጥር 13/2009 ዓ.ም በደብረታቦር ፖሊስ ጣቢያ ያሰሩት ሲሆን አሁን ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ አልተቻለም።

28. መ/ር ዋለልኝ ማሬ ዕድሜ 28፣ በምዕራብ እስቴ ወረዳ ባጀራ ገዶ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት መምህር ሲሆን የደብረታቦር ዩኒቨርስቲ ለክረምት መርሃግብር ባደረገው የምዝገባ ጥሪ መሰረት ህዳር 29/2009 ዓ.ም. በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ በተገኘበት ቀን የዩነቨርስቲው ተማሪዎች “የብሄረሰብ ቀን አናከብርም” በማለት ሰላማዊ ሰልፍ በማድረጋቸው ምክንያት በግቢው ውስጥ ሲንቀሳቀሱ የተገኙ ተማሪዎች በመንግስት አካላት ሲታሰሩ መ/ር ዋለልኝ ማሬም ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ታስሯል።

በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት የታሰሩ እስረኞች በእስር ቆይታቸው ወቅት ያለፈቃዳቸውና እነርሱ ባልመረጧቸው ርዕሦች ላይ የመንግሥትን እይታና አቋም ብቻ ይገልጻሉ በተባሉ የሥልጠና መርሐ ግብሮች ላይ በግዴታ እንዲካፈሉ ከተደረጉ በኂላ የሚከተለውን ዓይነት የምሥክር ወረቀት እንደተሰጣቸው ለሰመጉ ምስክርነታቸውን የሰጡ ተፈቺዎች አስረድተዋል፣ አሳይተዋል።



## 5.3 ማቁሰል፣ ድብደባና ማሰቃየት

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 18(1) ‹‹ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢ- ሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው›› ተብሎ የተደነገገውንና በዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 5 ‹‹ማንም ሰው የማሠቃየት ድርጊት ሊፈጸምበት ወይም በጭካኔና ኢ. ሰብዓዊ በሆነ መንገድ ሊጉላላ ወይም ሊዋረድ አይችልም ወይም ሊቀጣ አይችልም›› እንዲሁም ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የአፍሪካ የሰዎችና ህዝቦች መብት ቻርተር አንቀፅ 5 እና 6 ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብር ያለው በመሆኑ ያላግባብ እንደማይታሰር፣ እንግልትና የማሰቃየት ድርጊት እንዳይፈፀምበት ይከለክላል፡፡ ኢትዮጵያ ተቀብላ የፈረመችው ማሰቃየትን፣ ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው፣ ሰብዓዊነት የጎደላቸውና አዋራጅ የሆኑ አያያዞችንና ቅጣቶችን ለማስቀረት በተደረገው ስምምነት ክፍል አንድ አንቀፅ 2 እያንዳንዱ ይህንን ስምምነት የተቀበለ ሀገር በግዛት ክልሉ ውስጥ በዜጎቹ ላይ በማናቸውም ሁኔታ የማሰቃየት ድርጊት መፈፀም እንደሌለበትና ይህንንም መከላከል እንዳለበት ስምምነቱን በፈረሙ ሀገራት ላይ ግዴታ ይጥላል፡፡ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 18(1) የተደነገገው ጭካኔ ከተሞላበት ኢ.ሰብዓዊ አያያዝ የመጠበቅ መብት፣ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅትም ጭምር በምንም ዓይነት ሁኔታ ሊጣስም ሆነ ሊገደብ እንደማይችል በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 93(4)(ሐ) በግልፅ ተደንግጓል፡፡ እነዚህን ስምምነቶችና በህግ የተደነገገውን በመጣስ ከዚህ በታች ስማቸው በተጠቀሱት ሰዎች ላይ ድብደባና ማሠቃየት ተፈጽሟል፡፡

1. **መምህርና ጦማሪ ስዩም ተሾመ፡** *ዕድሜ 35፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በወሊሶ ከተማ ነዋሪና በአምቦ ዩኒቨርስቲ ወሊሶ ካምፓስ መምህር ነው፡፡ መ/ር ስዩም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በራሱ ድረ ገጽ (www.ethiothinktank.com) እንዲሁም Hornaffairs.com ድረ ገፅ ላይ በተለያዩ ወቅታዊ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ፣ በተለይ ደግሞ በሀገሪቱ ባለው የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት አያያዞች ላይ በሚያወጣቸው ፅሁፎች ይታወቃል፡፡*

   *መስከረም 19/2009 ዓ.ም. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንና ሰራተኞች ሀገራዊ ስብሰባን በሚ.መለከት በጀርመን ከሚገኘው የዶቼቬሌ ራዲዮ የአማርኛ ፕሮግራም ጋር በነበረው ቆይታ "እዚህ ሀገር ሃሳብን በነፃነት መግለፅ ለእስር፣ ስደትና ሞት ሊዳርግ ይችላል" የሚል አስተያየት ሰጥቶ ነበር፡፡ በዚህ መልኩ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የመብት ጥሰት አስመልክቶ ሃሳብና አስተያየቱን በመግለፁ በማግስቱ አርብ መስከረም 20/2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 12፡30 ላይ በርካታ ፖሊሶች ወደ መኖሪያ ቤቱ በመምጣት "የጦር መሳሪያና አመፅ ቀስቃሽ ጽሁፎች ቤትህ ውስጥ አሉ" በማለት የፍርድ ቤት ማዘዣ ይዘው መጡ፡፡ ምንም እንኳን በማዘዣው ላይ የተገለፁት የጦር መሳሪያና አመፅ ቀስቃሽ ፅሁፎች በፍተሻ ባይገኙም፣ የግል ላፕቶፕ ኮምፒውተር፣ ስማርት ፎን (ስልክ)፣ ለህትመት ያዘጋጃቸውን ረቂቅ ጽሁፎችና ማስታወሻ ደብተሮቹን በመያዝ ወደ ወሊሶ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዷቸው፡፡*

   *ጦማሪ ስዩም ሰኞ መስከረም 23/2009 ዓ.ም በወሊሶ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርቦ በፖሊስ የአስር (10) ቀን ጊዜ ቀጠሮ ተጠይቆበታል፡፡ በዚህ መሃል መምሕር ስዩም በመስከረም 22 2009 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሊወስደው የነበረውን የዶክትሬት ትምህርት የመግቢያ ፈተና ሳይፈተን ቀርቷል፡፡ በዚህም በስንት ግዜ አንዴ የሚገኝ የትምህርት እድል እንዳመለጠው ለሰመጉ ተናግሯል፡፡*

   *በቀጠሮ መሰረት ጥቅምት 03/2009 ዓ.ም ፍርድ ቤት ሲቀርብ ለፖሊስ ተጨማሪ የሰባት (7) ቀናት ቀጠሮ የተሰጠ ሲሆን መ/ር ስዩም ያቀረበው የዋስ መብትም ውድቅ ተደረገ፡፡ በመጨረሻም የወረዳው ፍርድ ቤት ጥቅምት 10/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት አቃቤ ሕግ የምርመራ ውጤቱን ለፍርድ ቤቱ አቀረበ፡፡ ፍርድ ቤቱም ተከሳሹ በተከሰሰበት ወንጀል ነፃ መሆኑንና የክስ መዝገቡም ተዘግቷል ሲል ብይን ሰጠ፡፡ ሆኖም ግን የመጀመሪያው የክስ መዝገብ ከተዘጋ በኋላ ወዲያው "መ/ር ስዩም ተሾመ በወሊሶ ፖሊስ ጣቢያ እያለ መስከረም 29/2009 ዓ.ም ስለ አስቸኳይ ግዜ አዋጁ ፅሁፍ በመፃፉ ምክንያት አዋጁን ጥሷል" በሚል ሌላ የክስ መዝገብ ተከፈተበትና ጉዳዩ በኮማንድ ፖስት እንዲታይ መወሰኑን በችሎቱ ተነገረው፡፡*

   *በእርግጥ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የታወጀው መስከረም 28/2009 ዓ.ም ቢሆንም ዝርዝር ይዘቱ ይፋ የተደረገው ጥቅምት 01/2009 ዓ.ም ነበር፡፡ በወቅቱ ተከሳሹ በህግ ቁጥጥር ስር የነበረ ከመሆኑም በተጨማሪ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ገና ይፋ አልተደረገም ነበር፤ የተጠቀሱት ጽሁፎች፣ መ/ር ስዩም ስለ እለታዊ ክስተቶች ማስታወሻ የመያዝ ልማድ ስላለው የፃፋቸውና በኪሱ ያስቀመጣቸው መሆኑ፣ የፅሁፎቹ ይዘት በምንም አግባብ ቢሆን የአስቸኳይ ግዜ አዋጁን የሚጥስ እንዳልነበረ ለማስረዳት መሞከሩን ለሰመጉ ገልጧል፡፡ እንዲሁም ጉዳዩ*

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ

በኮማንድ ፖስት እንዲታይ የተላለፈው መመሪያ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከወጣ (ከመስከረም 28/2009 ዓ.ም) በኋላ የተያዙ ተጠርጣሪዎችን ብቻ የሚመለከት ቢሆንም፣ መስከረም 20/2009 ዓ.ም የታሰረው መ/ር ስዩም ጉዳዩ በአዋጁ መሰረት እንዲታይ ተወስኗል በሚል ወደ ጦላይ ተወሰደ።

ጥቅምት 16/2009 ዓ.ም ከሌሊቱ 5:00 መ/ር ስዩም አብረውት ከታሰሩት ሌሎች ስምንት (8) ሰዎች ጋራ ወደ ወሊሶ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ተወስዶ በ3x5 ሜትር በሆነ ክፍል ውስጥ ከሌሎች 48 ሰዎች ጋር ታሰረ። መ/ር ስዩም በዚያ ጠባብ ክፍል ውስጥ ይሄን ያህል ብዛት ያለው ሰው በመታሰሩ ምክንያት ሌሊቱን ሙሉ በንፁህ አየር አጥረት ሲሰቃይ እንዳደረ ገልጿል። ሁኔታውንም በሕይወቱ ካሳለፋቸው ሌሊቶች ሁሉ እጅግ የከፋ እንደሆነ ተናግሯል። በማግስቱ ጥቅምት 17/2009 ዓ.ም ከደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከተወጣጡ በመቶዎች የሚቆጠሩ እስረኞች ጋር ወደ ጦላይ የተሃድሶ ማዕከል ተወሰደ።

መ/ር ስዩም በጦላይ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ከሌሎች 5670 እስረኞች ጋር ለ56 ቀናት ታስሯል። ከእነዚህ ውስጥ 120 የሚሆኑት ታሳሪዎች ሴቶች ነበሩ። ወደ ጦላይ እንደገቡ 13x18 ሜትር ስፋት ባለው ክፍል በአማካይ አንድ መቶ ሰዎች (100) ጋር ታስረዋል። በተለይ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት በቂ ምግብ እንዳላገኙ፣ በባዶ እግራቸው እንዲሄዱ መደረጋቸውን፣ የግል ሰብዕና በሚነካ መልኩ በመቶዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ፊት ሜዳ ላይ እንዲፃዳዱ መደረጋቸውን ተናግሯል። በቦታው የነበሩ የፌደራል ፖሊሶች ክብርናና ስብዕናቸውን በሚነካ መልኩ ይሰድቧቸው፣ ያስፈራሯቸው፣ የወታደራዊ ስፖርት ቅጣት (ማኮብኮብ) ይቀጧቸው፣ እንዲሁም ያለ ምንም ጥፋት ይደበድቧቸው እንደነበር ለሰመጉ ገልጿል።

መ/ር ስዩም ጦላይ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የመጀመሪያ ሃያ (20) ቀናት በእስረኞች ላይ በርካታ የማሰቃየት ድርጊቶች ሲፈፀሙ መታዘቡን፤ ለምሳሌ ያህል፣ ባዶ እግር ግርፋት፣ እጅን በጆሮ አስይዞ ማኮብኮብና ምግብ መከልከል እንደነበር ጠቅሷል። ከሁሉም በላይ ደግሞ በአዋጁ መሰረት የተቋቋመው ኮማንድ ፖስት የወንጀል ምርመራ ሲጀምር ጦላይ ምድራዊ ሲዖል ይመስል እንደነበር ገልጧል። ከእያንዳንዱ የማደሪያ ክፍል በስተጀርባ እስረኞች እግራቸው ወደላይ ተሰቅሎ ወይም መሬት ላይ በደረታቸው ተኝተው እየተደበደቡ የስቃይ ምርመራ ይደረግባቸው እንደነበር ለሰመጉ ተናግሯል። በጦላይ ቅጥር ግቢ የእስረኞችን ለቅሶ፣ ልመና፣ ዋይታ፣ ሕመምና ስቃይ በአካል ተገኝቶ መታዘቡን ለሰመጉ የምስክርነት ቃሉን በሰጠበት ጊዜ አስረድቷል።

በተመሳሳይ መ/ር ስዩም በጦላይ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ሕዳር 02/2009 ዓ.ም ከፍተኛ ድብደባና ስቃይ ተፈፅሞበታል። በእለቱ ከቀኑ 8:00 ሰዓት ላይ ከማደሪያ ክፍሉ ተጠርቶ የፖሊሶች ዋና አዛዥ ወደሚገኝበት ክፍል የተወሰደ ሲሆን እስከ ቀኑ 10:30 ድረስ (ለሁለት ሰዓት ተኩል ያህል) ያለማቋረጥ መደብደቡን ተናግሯል። በድብደባ ብዛት መ/ር ስዩም ሦስት ጊዜ ራሱን እንደሳተና ቀዝቃዛ ውሃ እላዩ ላይ እየተደፋ እንደሚቀሰቀስ፣ በዚህ መልክ ድብደባው ይቀጥል እንደነበር ለሰመጉ ገልጧል።

ከዚህም ሌላ በሥፍራው የሚገኘው የፖሊሶች አዛዥ "እዚህ ግቢ ውስጥ አደራጅተሃል! እመን" ብሎ ግንባሩ ላይ ሽጉጥ እንደደቀነበት ለሰመጉ የምስክርነት ቃሉን ሰጥቷል። መምሕር ስዩም በሕዳር 02/2009 ዓ.ም በተፈፀመበት ድብደባ በግራ እግሩ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰበት በሰመጉ ቢሮ በአካል ተገኝቶ በእግሩ ላይ ያለውን ጠባሳ አሳይቷል።



በአጠቃላይ፣ በጦላይ ታስሮ በቆየባቸው 56 ቀናት፣ መ/ር ስዩም ተሾመ ሰብዓዊ መብቱን በሚጥስ መልኩ የስቃይ ምርመራ ተፈፅሞበታል። ከድብደባ በተጨማሪ በፖሊሶች ክብርና ስብዕናውን በሚነካ መልኩ ስድብና ዘለፋ እንደተፈፀመበት ተናግሯል። መምሕር ስዩም በወሊሶ ፖሊስ ጣቢያ ለ26 ቀናት፣ በጦላይ ደግሞ ለ56 ቀናት፣ በአጠቃላይ ለ82 ቀናት እስርና ስቃይ ከደረሰበት በኋላ ታህሳስ 13/2009 ዓ.ም. ከእስር እንደተለቀቀ ለሰመጉ በአካል ቀርቦ አመልክቷል።

2. **ተማሪ አይናለም ክፍሌ:-** ፆታ ወንድ፣ ዕድሜ 22፣ ምሥራቅ ወለጋ፣ ዲጋ ወረዳ ዲጋጋ ዲዴሳ ቀበሌ ነዋሪ ነው። ተማሪ ዓይናለም ስለደረሰበት የመብት ጥሰት ለሰመጉ እንደገለጸው፣ በየካቲት 29 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2 ሰዓት ላይ አርጆ ጉዳቱ ፖሊሰ ጣቢያ እንዲቀርብ መታዘዙን፣ በተባለው ቀንና ሰዓት ቢቀርብም እስከ 7 ሰዓት ድረስ በፖሊስ ጣቢያው እስር ቤት ቆይቷል። በቆይታው ወቅት ከፖሊሶች መካከል አንደኛው "ለሌላ የምርመራ ጉዳይ እንድትመሰክርልኝ እፈልጋለሁ" ብሎ እንደጠየቀውና ጥቂት ቆይቶም ለሌሎች ታሳሪዎች የመጣ ምሳ እንደ.ጋበዘው ገልጾአል። በማላውቀው ጉዳይ ለመመስከር ፈቃደኛ አለመሆኔን ስገልጽ "ይህ አባቱን ተጣልቶ የመጣ ነው አለኝና በዱላ ራሴ ላይ መታኝ። ለምን ትመታኛለህ ስለው ለምን ፈቃደኛ አልሆንክም?" ብሎ በድጋሚ በዱላና በጫማ ጥፊ ደበደበኝ። በጣም ተጎድቼ ራሴን ከመሳቴ በፊት "ሲመሽ ማታ አሳይሀለሁ" ብሎኝ በመሄድ ላይ እያለ ሁለት አቃቤ ህጎች ሌሎች እስረኞችን ሲጎበኙ እኔ በተዘጋብኝ ቤት ውስጥ ሆኜ ሳለቅስ ሰምተው "ማነው? አስወጡት" ብለው እንድወጣ አደረጉኝ። ይህንን ድብደባ የፈጸመብህን ፖሊስ ክሰስ ብለውኝ ለመክሰስ በተደጋጋሚ ጊዜ ፖሊስ ጣቢያው ተመላለስኩ። እኔንም የማቀርባቸው ምስክሮቼንም እያስፈራሩ "አርፈህ ተቀመጥ እያሉኝ ነው" በማለት በሚያዝያ 27 2009 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ ለሰመጉ አመልክቷል።



3. **ወጣት አዳነ በርሻ** ፆታ ወንድ፣ እድሜ 24፣ አድራሻ ኮንሶ ወረዳ ዶከቱ ቀበሌ፤ ወጣት አዳነ በርሻ ጥቅምት 08 2009 ዓ.ም የመከላከያ ሠራዊት አባላት አስረው እየደበደቡ እንደወሰዱት እና ለክልሉ ልዩ ኃይል እንዳስረከቡት፤ የክልሉ ልዩ ኃይል አባላትም ‹‹የኮንሶ ተወካዮች ነን የሚሉትን ታሳየናለህ›› በማለት ሌሊቱን ሙሉ ሲደበድቡት እንዳደሩና በድብደባውም ምክንያት ጀርባው እና እጁ ቆሳስሎ እንደነበር ለሰመጉ አመልክቷል። በተጨማሪም መጀመሪያ ወደ ኮንሶ ፖሊስ ጣቢያ ቀጥሎም ይርጋለም ወደሚገኘው አፖስቶ ፖሊስ ማሠልጠኛ አዛውረው ለሶስት ወራት ከታሠረ በኋላ መለቀቁን ገልጧል።

3. **ወጣት መሐመድ አብድርቃድር :-** ዕድሜ 18፣ ፆታ ወንድ፣ ነዋሪነቱ በአርሲ ዞን በሸርካ ወረዳ ሶሬ ፈረንቀላ ቀበሌ ነው። መስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሊሃዋ ቀበሌ ህዝብ ያደረገውን እና በሰላም የተጠናቀቀውን ሰላማዊ ሰልፍ ተከትሎ በእለቱ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ ወደ አሃዳ 01 ቀበሌ የመጡት የመከላከያ ሠራዊት አባላት እና የታጠቁ የመንግስት ኃይሎች በከፈቱት ተኩስ ወጣት መሐመድ ከደረቱ ከፍ ብሎ ተመቶ ጥይቱ በጀርባው በኩል ወጥቷል። መሐመድ በሸርካ ጤና ጣቢያ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና የተደረገለት ሲሆን ለተሻለ ህክምና ወደ አሰላ ሆስፒታል ተልኮ ለሶስት ወራት ህክምናውን ተከታትሎ ተመልሷል።



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

4. አብድራህማን ገቦ ፡ ዕድሜ 24፣ ጾታ ወንድ፣ ነዋሪነቱ በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ጎሜሳ 01 ነው፡፡ መስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም. የሲሃኖ ቀበሌ ህዝብ ያደረገውን እና በሰላም የተጠናቀቀውን ሰላማዊ ሰልፍ ተከትሎ በእለቱ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ ወደ አሃዳ 01 ቀበሌ የመጡት የመከላከያ ሠራዊት እና የታጠቁ የመንግስት ኃይሎች በከፈቱት ተኩስ ምክንያት በተነሳው ግርግር "ተመቷል" ተብሎ የተነገረውን ወንድሙን ለመፈለግ እንደሄደ በመከላከያ ሰራዊት አባላት በተተኮሰ ጥይት ጭንቅላቱ ላይ ተመቶ ሽርካ ጤና ጣቢያ የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ ተደርጎለታል፡፡ በመቀጠልም ለተጨማሪ ህክምና ወደ አሰላ ሆስፒታል ተልኮ ለ3 ወራት ሕክምናውን ሲከታተል ቆይቶ ተመልሷል፡፡
5. ታዳጊ ህጻን ናትናኤል መስፍን፣ እድሜው 11 ሲሆን በዳንግላ ከተማ ቀበሌ 04 ነዋሪ ነው፡፡ በታህሳስ 17/2009 ዓ.ም. የታሰረ አባቱን ለመጠየቅ ወደ ዳንግላ ፖሊስ ጣቢያ የሄደው የ11 ዓመቱ ታዳጊ ናትናኤል መስፍን በፖሊስ አባል ኩላሊቱ ላይ በእግር ተረግጦ ጉዳት ደርሶበታል። አቶ መስፍን ብርሃኑ ከታህሳስ 13/2009 እስከ ታህሳስ 19/2009 ዓ ም በዳንግላ ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ የነበረ ሲሆን፤ ታህሳስ 19/ 2009 ዓ.ም. ወደ ዳንግላ ማረሚያ ቤት ተወስዷል፡፡

## 5.4 ሌሎች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

1. አቶ ካምቢሮ አይላቴ ጉዳኖ፡ የኮንሶ ሕዝብ ካነሣው በዞን የመደራጀት ጥያቄ ጋር በተያያዘ በወረዳው የሚገኙ የመንግሥት የጤና ተቋማት በመዘጋታቸው የእርሳቸው የግል ንብረት በሆኑት ‹‹ፋሮ መካከለኛ ክሊኒክና የመድኃኒት መደብር›› ለሕዝቡ አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ አቶ ካምቢሮ ለሰመጉ ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት፣ ኅዳር 04 ቀን 2009 ዓ.ም የክልሉ ልዩ ኃይልና የፌደራል ፖሊስ አባላት ከሌሎች ‹‹የሲቪል ልብስ›› ከለበሱ ሁለት ሰዎች ጋር በመሆን ወደ ክሊኒካቸው በመሄድ ለታካሚዎች አገልግሎት መስጠታቸውን እንዲያቋርጡ አድርገዋል፡፡ በዚያው ዕለት ከቀኑ በሰባት ሰዓት ተኩል በዞኑ የጤና ተቆጣጣሪ ከሆነ ግለሰብ ጋር ሆነው በድጋሚ ወደ ክሊኒኩ በመሄድ ‹‹ክሊኒኩን ዝጉ፤ ኋላ ላይ እንነጋገራለን›› የሚል የቃል ትዕዛዝ ሰጥተዋቸዋል፡፡ ከዚህ የቃል ትዕዛዝ በቀር ምንም ዓይነት ምክንያት ሳይሰጣቸው ክሊኒካቸውንና የመድኃኒት መደብራቸውን እንዲዘጉ ተገድደዋል፡፡ በክሊኒኩና በመድኃኒት መደብሩ ውስጥ ያለው ግምቱ ከ200 ሺ. ብር በላይ የሚሆን ንብረት እየተበላሸ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለሰገን አካባቢ ሕዝቦች ዞን የጽሑፍ አቤቱታ ቢያቀርቡም ‹‹ከኮማንድ ፖስት ጋር እንነጋገርበታለን›› ከማለት በቀር ምላሽ አለማግኘታቸውንና በእርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸውና በሠራተኞቻቸው ላይ የኢኮኖሚ ችግር መድረሱን ለሰመጉ ባቀረቡት አቤቱታ ገልጸዋል፡፡
2. በጥቅምት ወር 2009ዓ.ም በኮንሶ ወረዳ የሚገኙ ወፍጮ ቤቶች በመንግሥት ታጣቂዎች እንዲዘጉ በመደረጋቸው ምክንያት ወደሌላ አካባቢ በመሄድ ለቀለብ የሚሆን እህል አስፈጭተው ይመለሱ የነበሩ ዜጎች የያዙትን የተፈጨ እህል የደቡብ ክልል ልዩ ኃይል አባላትና የመከላከያ ሠራዊት አባላት ደፍተውባቸዋል፣ ወደ ዜጎች መኖሪያ ቤቶች በመግባት የበሰለ ምግብ ውስጥ አመድ ጨምረዋል፣ መመገቢያ ቁሳቁሶችን ሰባብረዋል ይህንንም የአካባቢው ነዋሪዎች ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሠንጠረዦች የሚያሳዩት ሰመጉ ባለው ውሱን አቅምና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ባካሄደው ምርመራ መሠረት፣ በዚህ 142ኛ ልዩ መግለጫ ውስጥ የተካተቱትን ዋና ዋና የመብት ጥሰት ዘርፎች ማጠቃለያ ነው።

**ሠንጠረዥ 12: የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀ በኋላ የተፈጸመ በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት**

| የመብት ጥሰቱ አይነት | የተገደሉበት ቦታ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | አማራ | ኦሮሚያ | ደቡብ | ድምር |
| ሕገ ወጥ ግድያ | 1 | 15 | 3 | 19 |

**ሠንጠረዥ 13: አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀ በኋላ የተፈጸመ ህገ-ወጥ እስራት**

| የመብት ጥሰቱ አይነት | ድምር | የተያዙበት ቦታ | | | | | | የታሰሩበት ቦታ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እስራት | | አማራ | ኦሮሚያ | ደቡብ | አፋር | አዲስ አበባ | ያልታወቀ | አማራ | ኦሮሚያ | ደቡብ | አፋር | አዲስ አበባ | ያልታወቀ |
| | 22525 | 640 | 8778 | 5769 | 1 | 411 | 6926 | 606 | 13260 | 5764 | 2355 | 430 | 110 |

**ሠንጠረዥ 14: አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀ በኋላ የተፈጸመ ማቁሰል፣ ደብደባና ማሰቃየት**

| የመብት ጥሰቱ አይነት | የመብት ጥሰቱ የደረሰበት ቦታ | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| ማቁሰል፣ ደብደባና ማሰቃየት | አማራ | ኦሮሚያ | ደቡብ | |
| | 1 | 3 | 3 | 7 |

## 6. ማጠቃለያ

በዚህ የሰመጉ 142ኛ ልዩ መግለጫ የተካተቱት የሞት፣ የአካል ጉዳት፣ የእሥራት፣ የደረሱበት የማይታወቁና ሌሎች ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የአስቸኳይ ግዜ አዋጁ ከታወጀበት ከመስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የተፈፀሙትን እና ሰመጉ በውስን አቅሙ ለማጣራት የቻለውን ብቻ ነው። ይህ ልዩ መግለጫ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል እንዲሁም በአዲስ አበባና በዙሪያው ባሉ ከተሞች በሚገኙ በ18 ዞኖች፣ በ42 ወረዳና ክፍለ ከተሞች የተፈፀሙትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የሚያካትት ነው።

በዚህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት የተፈፀሙት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በዚህ መግለጫ ከተገለፀው ዓይነትና ቁጥር በላይ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። በአንዳንድ አካባቢዎች የአስገድዶ መድፈር፣ የንብረት ዘረፋ እና የጅምላ እስራት እንዲሁም በርካታ ሰዎች በሚደርስባቸው ጫና ምክንያት ከአካባቢያቸው እንደተፈናቀሉና ቤተሰብና ንብረታቸውን ጥለው በመሰደድ በሐገር ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ከሐገር ውጭም ለመኖር መገደዳቸውን በርካታ ዜጎች ለሰመጉ ባለሙያዎች በቃል ገልጸዋል። ሆኖም በወቅቱ በተለይ ድርጊቶቹ ተፈጸሙ በተባሉባቸው ቦታዎች በነበረው አስጊና አስፈሪ ሁኔታ እንዲሁም በሰመጉ የአቅም ውሱንነት ምክንያት ደረሱ ስለተባሉት የመብት ጥሰቶች ተጨባጭ ማስረጃ ለማግኘት አልተቻለም። ይሁንና ወደ ፊት እነዚህን ጉዳዮች ለማጣራት ሰመጉ ጥረቱን አጠናክሮ ይቀጥላል።

ሰመጉ በዚህ ሪፖርት ይፋ የተደረጉትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በሚያጣራበት ወቅት በርካታ አስቸጋሪ ሁኔታዎች አጋጥመውታል። በሐገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በተለይም በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በደቡብ የህዝቡን ጥያቄ ተከትሎ መንግስት የወሰደው አላስፈላጊ የኃይል እርምጃ በህዝቡ ላይ ከፍተኛ ፍርሃት ፈጥሯል። በሐገሪቱ ላይ ያንዣበበው አስፈሪ የፖለቲካ ድባብ፣ በየአካባቢዎቹ የሰፈረው እና የሚንቀሳቀሰው ከፍተኛ መጠን ያለው

የመከላከያ፣ የፖሊስና የልዩ ኃይል የሰመጉ ባለሙያዎች እንደአስፈላጊነቱ እንዳይንቀሳቀሱና የየአካባቢው ህብረተሠብ መረጃ ለመስጠት ፍርሃት ውስጥ እንዲወድቅ አድርጎታል።

ስለሆነም የተጎጂዎች ቤተሰቦች፣ ተጎጂዎች እንዲሁም ለሰብዓዊ መብት መከበር የምትቀረቀሩ ዜጎች ሁሉ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለሰመጉ እንዲደርስ በማድረግ የበኩላችሁን ድጋፍ በማድረግ የዜግነትና የሰብዓዊነት ግዴታችሁን እንድትወጡ ሰመጉ በአክብሮት ጥሪውን ያስተላልፋል።

## 7. ማሳሰቢያ

ዜጐች ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፍ የማድረግ፣ ጥያቄዎቻቸውን በሰላማዊ መንገድ የማቅረብ መብት እንዳላቸው የኢፌድሪ ህገ መንግስት በግልፅ ይደነግጋል። መንግስት ህዝቡ የሚያቀርብለትን ጥያቄዎች ለማስተናገድ ክፍት እና ግልፅ መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል። ህዝቡ ጥያቄዎቹን ለመንግስት የሚያቀርብበት መድረክ ማጣቱ፣ መንግስትም በማናቸውም መንገድ የቀረቡለትን ጥያቄዎች ለማስተናገድ አለመቻሉ እና የኃይል እርምጃን በመፍትኄነት መምረጡ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ቀውስ አስከትሏል።

የተቃውሞ ሰልፎች ብዙውን ጊዜ የሚካሄዱት በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ መነጋገር ሳይቻል ሲቀር፣ እንዲሁም የሀገራችን ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ግለሰቦችና ቡድኖች ከመንግስት ጋር በሀገር ጉዳይ ላይ ተቀምጠው ፍላጎታቸውን ለህዝብ የሚያሳውቁበት መድረክ ሲያጡ ነው። በመጨረሻም

- መንግስት ዜጎች የሚያነሱትን ማንኛውም አይነት ጥያቄና ቅሬታ ከማፈንና በሕግ ስም ከመገደብ ይልቅ በዲሞክራሲያዊ፣ በሰላማዊ፣ በሕጋዊና በሰለጠነ መንገድ ብቻ እንዲመልስ፣
- የቅርቡን ጊዜ ጨምሮ በሐገራችን የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ነጻ፣ ገለልተኛና ሣይንሳዊ በሆነ መንገድ አጣርቶ ችግሮችን በተጨባጭና በአስተማማኝ ሁኔታ ለማሳየት እንዲሁም ኃላፊነት የተሞላበትና ገንቢ የመፍትሔ ሀሳብ ለማቅረብ ከሚረዱት መንገዶች አንደኛው ሐገር በቀል፤ አንጋፋና ነጻ የሆነውን የሰብዓዊ መብቶች አስከባሪ ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔን - ሰመጉን በነጻነት፣ በስፋትና በሙሉ አቅሙ የሚሰራበትን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ምህዳር ማስፋት ነው። በመሆኑም መንግስት ለሰመጉ ተገቢውን እውቅና፣ የመሥራት ነጻነት፣ ድጋፍና ጥበቃ እንዲያደርግለት፣
- በአጠቃላይ የደረሰውን የህይወትና ንብረት ጥፋት ነጻና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ለማጣራት ጥያቄ ላቀረቡ የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ጽ/ቤት፣ የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽንና ለሌሎችም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማት በጥያቄአቸው መሠረት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ምርመራ ለማድረግ እንዲፈቀድላቸው፤
- ሕገወጥ ግድያና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ተጎጂዎችና ቤተሰቦች ተገቢው ካሣ እንዲከፈል፣
- ከህግና ከዲሞክራሲ አግባብ ውጭ በዜጎች ህይወትና አካል ላይ ጥፋትና ጉዳት የፈፀሙና ያስፈጸሙ የመንግሥት አካላትን ለሕግ በማቅረብ ተጠያቂ እንዲያደርግ፣

በመጨረሻም ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የቆማችሁ ዜጎች፣ ሐገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማትም መንግሥት የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲያከብር፣ እንዲያስከብርና እንዲያሟላ ከዚህ በታች በተገለጹት አድራሻዎች በመጻፍና ስልክ በመደወል ጥያቄና ግፊት እንድታደርጉ ሰመጉ ይጠይቃል።

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት**
  ፖ.ሳ.ቁጥር :- 80001፣ ኢ-ሜል:- national.parliament@ethionet.et፣
  ፋክስ :- (+251) 011 155-0400፣የስልክ ቁጥር :- (+251) 011 124-1000፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር :- 20122/1000፣ ኢ-ሜል :- kumashih@gmail.com
  ፋክስ :- (+251) 011 124-1208/011 124-2308፣
  የስልክ ቁጥር :- (+251) 011 122-3322፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 23698፣ ፋክስ ፡- (+251) 011 551- 8656፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-8186፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት :-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡-1031፣ ፋክስ፡- (+251) 011 122-6292፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 124-1155፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለአስቸኳይ ጊዜ ኮማንድ ፖስት ሴክሬቴሪያት**
  ስልክ ቁጥር +251-0125512777 የውስጥ መስመር (EXT)186
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢፌዴሪ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻፀም አጣሪ ቦርድ**
  ስልክ ቁጥር +251-111225754
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ**
  ስልክ ቁጥር +251 115541868
  ፋክስ +25115517775
  ኢሜይል MOJMO@ETHIONET.ET
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 5608፣ ኢ-ሜል፡- mofatr1@yahoo.com፣
  ፋክስ፡-(+251)011 551-1200፣
  የስልክ ቁጥር፡-(+251) 011 515-3204፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም:**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 2459፣ ኢ-ሜል፡ ombudsmaneth@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 553-2073፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 543-336፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን:**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1165፣ ኢ-ሜ፡ hrcom@ethionet.et፣
  ፋክስ፡ (+251) 011 550-4125፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 550-4031፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀነራል ጽ/ቤት:**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 199፣ የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-2744፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለሶማሌ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:**
  ፖ.ሳ.ቁጥር 392፣ ፋክስ፡- (+251) 25 775-3429፣
  የስልክ ቁጥር፡ (+251) 257 75 34 29
  ጅግጅጋ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኦሮሚያ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769፣ ኢ-ሜል፡- oromiawiev@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 551-3642 / (+251) 011 551-9633፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 552-4247፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1324፣ ፋክስ፡- (+251) 058 220-2511፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-2659፣
  ባሕርዳር፣ ኢትዮጵያ
- ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1546፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 221-4778/ 046 220-5848፣
  ሐዋሳ፣ ኢትዮጵያ
- ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 44፣ ፋክስ፡- (+251) 057 775-0814፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 055 7775-0109፣
  አሶሳ፣ ኢትዮጵያ
- ለትግራይ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 291፣ ፋክስ፡- (+251) 034 441-6564፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 034 441-6563፣
  መቀሌ፣ ኢትዮጵያ
- ለጋምቤላ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 25፣ ፋክስ:- (+251) 046 220-2408፣
  ጋምቤላ፣ ጋምቤላ
- ለሐረሪ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 952 ፋክስ፡- (+251) 025 666-2530፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1723 / 025 666-1746
  ሐረር፣ ኢትዮጵያ
- ለአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
  ስልክቁጥር(+251) 0336660056
  ሰመራ ኢትዮጵያ
- ለድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት
  የስልክ ቁጥር፡ (+251) 025 11 11 358
  ፋክስ፡ (+251) 025 11 19 805
- ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት
  ስልክ ቁጥር (+251) 0118591363

ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!!

ሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤
የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣
የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባል፣
የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት
(DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council